መስከረም

STANFORD LIBRARIES

HOOVER
MAR - 5 1986
INSTITUTION

- የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ጽንሰ ሐሳብ
  አስተዳደግና መሠረተ ሐሳቦች
- የአርሶ አደሩና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር
  በኢትዮጵያ—አንዳንድ ገጽታዎች
- ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ
- የፓርቲ ዲሲፕሊን

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 6 ቁጥር
መስከረም 1978

23

Digitized by Google

Digitized by Google

Meskerem ET 50171P



መስከረም

ቅጽ 6 ቁጥር 23
መስከረም 1978

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

● ሳይንስም ወደ መስክ 3

● የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ጽንሰ ሐሳብ
አስተዳደግና መሠረተ ሐሳቦች 5
—ተፈራ አሰፋ

● የአርሶ አደሩና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር በኢትዮጵያ
— አንዳንድ ገጽታዎች 35
—አበበ ወርቁ

● ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ 47
—ታረቀኝ አዴቦ

● የፓርቲ ዲሲፕሊን 59
—የቆየ መንገሻ

● ከዝግጅት ለአንባብያን 71

● የአርዕስት ማውጫ 74
—ስምዖን ተክለ ሃይማኖት

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google



ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

ሳይንስም ወደ መስክ

በዕድገት ጉዳና ላይ እርምጃችንን በማፋጠን ለተሻለ ሕይወት እንበቃ ዘንድ
መፍትሔው ተግቶ መሥራት ብቻ ነው። ሥራ የምንመኘውን ሊያስገኝልን የሚችለውም
በዕውቀት ሲደገፍ ነው ። ዕውቀት ደግሞ በጥናት ወይም በትምህርት እንጂ በፍላ
ጎት ብቻ የሚጨበጥ አይደለም ። ስለዚህ ዕውቀትን ለመሻት ለሚደረግ ማናቸውም
ጥረት የቱን ያህል ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንዳለበት የሚያጠያይቅ አይደለም ።

ጥናትና ምርምር ወይም ትምህርት በበኩሉ የሚጠበቀውን ዓይነት ዕውቀትና
ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልክ ሲካሄድ ብቻ
ነው ። ዩኒቨርሲቲዎቻችንና ልዩ ልዩ የማሰልጠኛ ተቋሞቻችን ከመቼውም ይልቅ ዛሬ
ይህንን በሚገባ ማጤን ይጠበቅባቸዋል ። ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ከተግባር ፣ በተ
ለይም ከአገር ልማትና ከአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ጋር ማጣመር ይኖርባቸዋል ።
በጋራ ለመሥራትና የተሻለ ውጤት ለማሳየት ሁኔታዎች በተመቻቹበት በአሁኑ ጊዜ
በንድፈ ሐሳባ ዐዋቂነት የተግባር ሰዎችን በመተቸት ለመወሰን መሞከር ቦታ የለ
ውም ። ይልቁንም የዐዋቂነት አንዱ ዓቢይ መለኪያና የሐቀኛ ዜግነት ማረጋገጫ
ሚዛን የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል እራስን ማሰለፍ ነው ።

ከዚህ አኳያ በቅርቡ ብዛታቸው ወደ 25 ሺህ የሚጠጋ የከፍተኛ ትምህርት
ተቋሞች ተማሪዎች ፣ መምህራንና ሠራተኞች በተፈጥሮ ችግር የተጉዱ ወገናችች
ን መልሶ ለማቋቋም ወደመስክ በመዝመት ያደረጉት ተሳትፎ በእርግጥ በቀላሉ
የሚታይ አይደለም ። ዘማቾቹ ተልዕኳቸውን በመወጣት ተጨባጭ አስተዋጽኦ ከማ
ድረጋቸውም በላይ ከመላው ኅብረተሰብ ያተረፉት የአለኝታነት ግምት በጣም አበ
ረታች ነው ። ከዚህም በተጨማሪ ዘማቾቹ እራሳቸውም የአገሪቱን ዕውነታ በመ
ዳሰስ ለወገን የመቀርቀር ስሜታቸው በይበልጥ መቀስቀሱ ሊላው የላቀ ግምት የሚ
ሰጠው ጉዳይ ነው ።

ዘማቾቹ ጊዜያዊ ችግርን ለመቋቋም ብቻ ሳይሆን ዘላቂ መፍትሔን ለማስገኘ
ትና እናት አገራችንን ከኋላቀርነት ለማላቀቅ ኢሠፓ የቀየሰውን ትልምና የአብዮ
ዊውን መንግሥት የአፈጻጸም ፖሊሲ ካድሬዎችና ልዩ ልዩ ሠራተኞች በአስቸጋ
ሁኔታ ውስጥ በመወጣት ላይ መሆናቸውን ከጉናቸው በመሰለፍ በእውን ለማረጋ
ገጥ ችለዋል ። በአጠቃላይ አብዮታችን የቀመለተ ሕዝባዊ ዓላማ እንደምን በተግባር
በመተርጉም ላይ እንደሚገኝ በመጠኑ ለማስተዋል ችለዋል ። ስምሪታቸው የተግባ
ርን ሂደት የመቃኘት ሳይሆን በውስጡ ተፈትኖ የማለፍ ነበርና በአስተሳሰባቸውና
በስሜታቸው ላይ የተወሰነ ምልክት እንዳሳረፈ ጥርጥር የለውም ። በዚሁ መሠረት
በተፈጠረው አዲስ ሁኔታ በአገራችን ምሁሮች መካከል ለበለጠ ኃላፊነትና ለላቀ
ተግባር የመነሣሣት ስሜት እየዳበረ እንደሚሄድ ይታመናል ።

Digitized by Google

ተደጋግሞ እንደሚስተጋባው የፍሬያማ ትምህርትና ዕውቀት መተማመኛ መሠረት ተግባር ነው ። በተለይ ለእኛ ትምህርትና ዕውቀት ሕይወትን ማዳኛ ፣ ለህልውናችንና ለዕድገታችን አስፈላጊ የሆነውን መሠረት መጣያ እንጂ ውጤት አልባ የአዕምሮ መፈተኛ ሊሆን ስለማይችል በፍጹም ከተግባር ለይተን ልንመለከተው አይገባም ። ስለዚህ ምሁራንና የሚያሠለጥኗቸው ተማሪዎች እራሳቸውን ከኅብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር በቀርብ ማቀራኘት ይኖርባቸዋል ። በቅድሚያ ትምህርት ከዚያ ተግባር ወይም መጀመሪያ ሥልጠና ከዚያ ሥራ የሚለው አመለካከት ሥርነቀል ለውጥ ሊታይበት ይገባል ።

የትምህርት ተቋሞች የንድፈ ሐሳብና የተግባር መናኸሪያ ከመሆንም በላይ በምርት ተግባርም ተሳታፊ መሆንና እጅግ ቢያንስ የእራሳቸውን ፍላጐት መደጐም የሚጠበቅባቸው እንደመሆናቸው በዚህ ረገድ አሁንም በበለጠ እራሳቸውን መለወጥና ማመቻቸት ይኖርባቸዋል ። እርግጥ አንዳንድ አስተዳደራዊ ዕንቅፋቶች ሊኖሩባቸው ይችሉ ይሆናል ። እነዚህ ችግሮች ግን መሠረታዊ እክሎች ስላልሆኑና በቀላሉ ስለሚወገዱ ወደኋላ ሊሉ አይገባም ።

ዛሬ ስለሥልጠና ስናወሳ አጠቃላይ ያውም ንድፈ ሐሳባዊ የሆነ ዕውቀት ማስጨበጥ ማለት ሳይሆን በየመስካቸው ከተግባር ጋር የተዛመደ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ማፍራት ማለት ነው ። ስለዚህ በማናቸውም ረገድ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን አዘጋጅቶ ለማውጣት አንዱ የትምህርት ማዕድ የእውነታው መስክ መሆን ይኖርበታል ። ይህ ሁኔታ ከሥልጠና አንጻር ብቻ ሳይሆን ለልማት ተገቢ መፍትሔዎችን ለማስገኘት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የመስክ የምርምር ሥራዎችንም በስፋት ከማካሄድ አኳያም በበለጠ ሊገፋበት የሚገባ ነው ። ለተሟላ ሥልጠናም ሆነ አስፈላጊ የምርምር ውጤቶችን ለማስገኘት በዚህ መልክ ወደመስክ የማተኮር አዝማሚያ በበለጠ የዘመናዊ ምርት አስተማማኝ ማንቀሳቀሻ በሆነው በሳይንስና ቴክኖሎጂ በስፋት ለመጠቀም ያስችለናል ።

ፍትሕ ፣ እኩልነትና ብልጽግና የሰፈነበት አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት አስፈላጊዎችን ቅድመ ሁኔታዎች በሚገባ አመቻችተናል ። ይህም ተግባር ቁርጠኝነትና ከፍተኛ መሥዋዕትነት ጠይቆናል ። ከፊታችን የተዘረጋው የግንባታ ተግባር ደግሞ እጅግ ውስብስብ እንደመሆኑ ጥልቅ ዕውቀት ይሻል ። ስለዚህም ሳይንስን በሚገባ ጨብጦ በየመስኩ መገልገያችን ለማድረግ ያልተቋጠበ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል ።

ይህም የሳይንስን ዕውቀት ተከና የመስክ ላይ መገልገያ የማድረጉ ጥረት ከአጠቃላዩ የአዲስ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ዓላማችን አኳያ ጠቀሜታው ሰፊና ሁሉን አቀፍ ነው ። ንድፈ ሐሳባዊ ዕውቀትን ወደተግባር ከማሸጋገርም በላይ ምሁሩን ከሌላው ሠርቶ አደር ሕዝብ ፣ ሠራተኛውን ከገበሬው ፣ ኢንዱስትሪን ከግብርና ፣ ከተማን ከገጠር ለማስተሳሰር ያስችላል ። በአጠቃላይም ለእናት አገራችን መልማትና መታፈር ዋስትና የሆነውን የአብዮቱን መሠረት የማይናወጥ ፣ የዕድገት እንቅስቃሴውንም የተቀሀደ ያደርገዋል ። ስለዚህ ራሳችንን ለመቻል ባለን ጽኑ ፍላጐት መሠረት ዛሬ በየአቀጣጫው የሚታየውን ርብርብ ወደቋሚ ባህል በመለወጥ ለበለጠ ዕውቀት ፣ ተግባርና ውጤት እንትጋ ።

Digitized by Google

የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ጽንሰሐሳብ

አስተዳደግና መሠረተ ሐሳቦች

ተፈራ አሰፋ

መግቢያ *

የማኔጅመንት(የሥራ አመራር)ጥያቄ በተለይ በአሁኑ ዘመን ከመሠረታዊና ከዋናዋና ማኅበራዊ ጉዳዮች አንዱ ነው ። ይሁንና የማኔጅመንት ንድፈሐሳብ አሁንም ቢሆን ገና በማደግ ላይ ያለ የዕውቀት መስክ ነው ።

ከማኔጅመንት ሳይንስ ዘርፎች መካከል አንዱ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ነው ። የአንድን አገር ኢኮኖሚ መቆጣጠርና መምራት የማኔጅመንት የመሠረት ድንጋይ ነው ። የኢኮኖሚ ማኔጅመንት በአጭር አገላለጽ የሰው ልጅ ኢኮኖሚያዊ ተግባራትንና የምርት እንቅስቃሴን የኢኮኖሚ ሕጎች በሚጠይቁት መሠረት ማደራጀት ማለት ነው ። በሌላ አነጋገር ነባራዊ የሆኑትን የኢኮኖሚ ሕጎችን በመመርመርና በማስተዋል የኢኮኖሚ ዕድገትን መምራት ማለት ነው ። ይህንንም ለማድረግ በየደረጃው ለምርት ዕድገት ፣ በምርት ሂደትና አደረጃጀት ላይ ተፅዕና የሚያደርጉ ልዩ የምርት ሁኔታዎችን ሁሉ ማጤንና ካለፉትና ከወደፊቱ የምርት ዕድገት ሁኔታዎች ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል ። ማኔጅመንት እነዚህንና ሌሎች መሰል ግንዛቤዎችን መሠረት በማድረግ የምርት ዕድገት አቅጣጫን የመቀየስ ተግባርን ያጠቃልላል ።

ይህ ሁሉ ተግባርም የሚያተኩረውና ማተኮር ያለበት የምርቱን ሥርዓት ትክክለኛ አቅጣጫ በማስያዝ የምርት ኃይሎችን ዕድገት በማስገኘትና በማዳበር ላይ ነው ።ለምርት ተግባር ተገቢ አመራር ለመስጠት መቻልን ወይም አለመቻልን ለመለካት የሚያስችለውም ይኸው ነው ።

በሶሻሊስት ማኔጅመንት በመጀመሪያ ትኩረት የሚሰጠው ለብሔራዊ የኢኮኖሚና የምርት እንቅስቃሴዎች ነው ። ቀዳሚዎቹ

---

* ይህ ጽሑፍ በወሉ ከ'ሀ ኢሠፓ ኮሚቴ አግካይነት ለመስከረም ዝግጅት የቀረበ ነው ።

Digitized by Google

የማኔጅመንት ጥያቄዎቹም በጠቅላላው ማኅበራዊ ምርት በሚደራጁበት ሁኔታ ላይ የሚያተኩሩና በአንድ ማዕከላዊ ፕላን እየተመራ ስለሚያድግበት ፤ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች መሃል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ፤ ብሔራዊ የምርት ውጤትና ሥርጭት ቁጥጥር ስለሚደረግበት ሁኔታ ፤ ወዘተ የሚመለከቱ ናቸው ።

ይህ አጠቃላይና በብሔራዊ ደረጃ የሚቀየሰው የኢኮኖሚ አመራር ስልት ለተከታዩ ዝርዝር የማኔጅመንት አፈጻጸም ሁኔታዎች መሠረት ነው ። ስለሆነም ተከታዩ ተግባር ወደታች ዝቅ በማለት በእያንዳንዱ የማምረቻ ተቋም ውስጥ የምርት (የኢኮኖሚ) ተግባርን በመመርመር የሥራውን ሂደት ማጥናትና አመራር መስጠት ነው ። ለምሳሌ የጥሬ ዕቃ አቀራረብን ፤ አያያዝንና አጠቃቀምን መቆጣጠር ፤ የምርቱን ፕላን ወደተግባር ለመለወጥ የወጣው የጊዜ ፕሮግራም መጠበቁን መከታተል ፤ ይህንም ለማድረግ ሚያስችሉ ዘዴዎችን የመቀየስ ፤ የምርት ሂደት እንቅፋቶችን ሁሉ አስቀድሞ መከላከል ፤ ወዘተ . . . የእያንዳንዱን የማምረቻ ድርጅት የምርት ሥራ አመራር ኃላፊነት የሚረከቡ ሥራ መሪዎች ሁሉ መሠረታዊ ተግባራት ናቸው ።

በመነሻው እንደተጠቀመው ምንም እንኳ አሁንም ገና በማደግና መልክ በመያዝ ላይ ያለ ቢሆንም የማኔጅመንት ሥርዓት በኅብረተሰብ ውስጥ ከጊዜ ወደጊዜ በሚመዘገበው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገት ላይ በመመሥረት እየዳበረ መጥቷል ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የማኔጅመንት ተግባርን አነሣሥ ፤የጽንሰሐሳቡን ፍቺና በተለያዩ ሥርዓቶች የሚኖረውን ዓላማና አገባብ ፤ በመጨረሻም በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ አዲስ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ የተደረጉ ጥረቶችን ለማየት ይሞከራል ።

የማኔጅመንት አጀማመር

የማኔጅመንት ሳይንስ ከካፒታሊዝም አነሣሥና ወደከፍተኛ ደረጃ ማደግ ጋር የመጣና በሱም ውስጥ ተወልዶ ያደገ ነው ። ይሁንና ይህ አባባል የሚያመለክተው ማኔጅመንት እንደሳይንስ ተለይቶ የወጣበትን ፤ በግልጽ በታወቁ መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ በሥርዓት በተቀናጁ ንድፈ ሐሳቦች መግለጽ የጀመረበትን ዘመን ብቻ ነው ። ሥርዓትና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ አይሁን እንጂ የማኔጅመንት ተግባርን ማከናወን ከካፒታሊዝም መስፋፋት ብዙ ቀደም ብሎ የነበረ ነው ።

ማኔጅመንት የሚለው ቃል መነሻ «ማኑስ» (MANUS) የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ቀጥታ ትርጉሙ «እጅ» ማለት ነው። ቃሉ በመጀመሪያ አገባቡ «ፈረስ መግራት» ማለት ነበር ።[1] ከዚሁ የተገኘው ቃል ፤ ማኔጅመንት ከዚህ ከተገለጸው አገባቡና አጠቃቀሙ ተወስዶ በአንድ ኅበረተሰብ ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ሲውልም ካንድ የታቀደ ግብ ላይ ለመድረስ ሲባል የሚከናወን ቁጥጥርን አመራርን ፤ ማደራጀትን ወይም የመግራት ተግባርን እንደሚያመለክት ሆኖ ነው ። የማኔጅመንት ተግባር በዚህ አኳያ ሲታይ በማንኛውም የዕድገት ደረጃው የሚገኝ ኅብረተሰብ ሁሉ ውስጣዊና መሠረታዊ ጠባይ ነው ። ይህም ሁለንተናዊነቱ የሚመነጨው ከሰው ልጅ የምርት ተግባር ፤በአጠቃላይ ከሰብአዊ ሥራ በባሕርዩ ማኅበራዊ መሆን ፤ እና ኅብረተሰቡም በተፈጥሮው አንድ የተወሰነ ሥርዓትን ተከትሎ የተቀናጀ ከመሆኑ ነው ።

የሰው ልጅ ፍላጐቶቹን ለማርካት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማግኘት ያመርታል ። ነገር ግን ይህን የማምረት ተግባር የሚካሄደው በተናጠል አይደለም ። ጥንታዊ ሰው ማኅበራዊም ሆነ ግላዊ ፍላጐቱን በማርካት ከተፈጥሮ ሊያገኝ የሚችለውን ሁሉ

Digitized by Google

መለገስ (ፍራፍሬ መልቀም ፣ ሥራሥር መንቀል) ነበረበት ። ተፈጥሮ ልታደርስበት ከምትችለው ቁጣም ሆነ በአካባቢው ከሚኖሩት ግዙፍ አራዊት ራሱን መጠበቅና መከላከል ነበረበት።ይህን ሁሉ ለማድረግ የሰው ልጅ በወቅቱ በነበረበት በጣም ዝቅተኛ የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ በጋራ (በቡድን) ከመሥራት ሌላ አማራጭ አልነበረውም ። ስለሆነም ሥራ ከመሠረቱ ማኅበራዊ ነው ። የጋራ ወይም የቡድን ሥራ ሁሉ ደግሞ አንድ ዓይነት ቅንጅትና ቅንብር አንደሚጠይቅ ግልጽ ነው ። ምክንያቱም የቡድን ሥራው ራሱ የሚካሄድበት የሥራ ክፍፍል ይኖራል ፤ በቡድን ሥራው አማካይነት የሚገኘው ውጤት ክፍፍል ጥያቄም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው ። ስለዚህ በጣም በግርድፉ ወይም በዝቅተኛ ደረጃ ይሁን እንጂ በሰው ልጅ የመጀመሪያ የዕድገት ደረጃ ወቅት እንኳ ማንኛውም ሥራ ፣ ማንኛውም ዓላማ ያለው ሰብአዊ የተግባር እንቅስቃሴ አንድ የተወሰነ ሥርዓትና ቅንብር ሳይኖረው ፣ በአንድ ቃል ፣ ያለ ማኔጅመንት የሚካሄድ አልነበረም ። ለዚሁም ነው ማኔጅመንት በሁሉም የኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃዎች አለ የሚባለው ።

የጥንቱ የማኔጅመንት ተግባር በጅምር መልኩ ያለ ነበር ቢባልም ዓላማና ውጤቱ በቅድሚያ የተለየ የነቃ የማኔጅመንት ተግባር ለመጀመሪያ ጊዜ መታየት የጀመረው ከእደ ጥበብ ምርት መስፋፋት ጋር ነው ። የእደ ጥበብ ምርት የተጀመረው በጥንታዊ የጋርዮሽ ኅብረተሰብ ማክተሚያ ላይ ነው። ይህ ወቅት የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ለሚያድርገው ትግል መገልገያ የሚሆኑትን መሣሪያዎቹን ከብረታብረት መሥራት የጀመረበት ፣ የእደ ጥበብ ሙያ (ሽመና ፣ ሸክላ ሥራ ወዘተ ...) መዳበር የታየበትና በመጨረሻም ሁለተኛው ከፍተኛ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል (እደ ጥበብ ራሱን የቻለ የሥራ መስክ መሆን) የተከሰተበትና በአጠቃላይ የእደጥበብ ሙያዎች የተስፋፉበት ወቅት ነው ።

የዕደጥበብ የሙያ ዘርፍ /የምርት መስክ/ አንዱ ልዩ ባሕርይ ከልውውጥና ከንግድ ተግባር ውጪ ሊኖር የሚችል ተግባር አለመሆኑ ነው ። የእደጥበብ ባለሙያው ፣ ለምሳሌ፣ እንደገበሬ ራሱ ያመረተውን በቀጥታ ለራሱ ግልጋሎት አውሎ ሊኖር አይችልም። የራሱን የምርት /የጉልበቱን/ ውጤት በሽያጭ ሰጥቶ በለውጡ የምግብ ውጤቶችንና ሌላም የሚያስፈልጉትን ውጤቶች በግዥ ማግኘት የግድ አለበት ። ስለዚህ የእደ ጥበብ ምርት ማደግና መስፋፋት ለልውውጡ/ለንግድ/ ማደግና መስፋፋት ፣ የልውውጥ ማደግና መስፋፋት ደግሞ መልሶ ለእደጥበብ ምርት ማደግና መስፋፋት ሁኔታውን እያዘጋጀ በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ሥርዓቶች ውስጥ እያደጉ መጥተዋል ።

የእደ ጥበብ ምርት በዚህ ዓይነት ከግደጉም ጋር የምርቱን ዓይነት ምርጫ ፣ ምርቱ የሚካሄድበትን ሁኔታ የመወሰን ፣ ምን ያህል መመረት እንዳለበት ፤ ለማን መሸጥ እንዳለበት ፣ ምን ዓይነት ቴክኖሎጂን በመጠቀም መመረት እንዳለበት ወይም ማምረት እንደሚቻል የመወሰን ጥያቄዎች ሁሉ የሚነሡናቸው ። ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሥራን ማስተባበርና ማቀናጀት አስፈላጊ ነው ። ይህም ተግባር የማኔጅመንት ቅርጽ (መልክ) ይይዛል ። የማኔጅመንት ተግባር ምልክቶች ለይተው መታየት ጀመሩ ማለት ነው ። በጥንታዊት የሮማ ግዛት ለምሳሌ ለሮም የጦር ኃይል መሣሪያ የሚያመርቱ ተቋሞች ፣ የሸክላ ፣ የመስተዋትና የሽመና ሥራ፣በሰፋፊ ይዞታዎች ላይ የሚካሄድ የግብርና ሥራና አንጥረኝነት በአንድ ወጥ የማኔጅመንት ሥር እንዲሰባሰቡ ተደርጉ ነበር።[2]

የእደ ጥበብ ምርቱ ይካሄድ የነበረው ባለሙያዎቹ ፣ በመሬት ባለቤቶችና በባሪያ ጌቶች ቁጥጥር ሥር ሆኖ ነበር ፤ የሚሠራውም ሥራ ትኩረት በአመዛኙ የባሪያ አሳዳሪዎችንና የፊውዳል ጌቶችን ፍላጐት ለማርካት እንጂ በሚያስገኘው ትርፍ ላይ የነበረ

Digitized by Google

ባለመሆኑ የሥራ ዕቅድ አደረጃጀትና ክትትል ጥያቄዎች ይህን ያህል የሰፉና የተወሳሰቡ አልነበሩም። [3] በሌላ አነጋገር የማኔጅመንት ጥያቄ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ ይገኝ ነበር ። ከዚህም በኋላ በፊውዳሊዝም ውስጥ እስከ ካፒታሊዝም መጠንሰስ ድረስ የእደ ጥበብ ምርት እያደገ የመጣ ቢሆንም እንኳ የማኔጅመንት ተግባር ውሱን እንዲሆን ያደረጉ አያሌ ሁኔታዎች አሉ ። ለምሳሌ በቅድመ ካፒታሊስት ኅብረተሰብም የኅብረተሰቡ አባላት በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሚሠማሩ መሆኑ ባይካድም የሥራ ክፍፍሉ የጠለቀና የሰፋ አልነበረም ። እያንዳንዱ የእደጥበብ ባለሙያ /አምራች/ ምርቱን በተመለከተ ሁሉንም ተግባር ያከናውናል ። ስለ ሥራው ሁኔታ የሚደረገውን ጥናትና ክትትል ራሱ ያደርጋል ። የምርቱን ተግባር ከምርት ሥራ አመራሩ ተግባር ጋር አጣምሮ ያካሂዳል ። የማኔጅመንት ተግባር ለብቻው ተለይቶ ባለሙያዎች የሚሠሩበት መስክ አልነበረም ።

በአጠቃላይ ከካፒታሊዝም በፊት ማኔጅመንት ነበር ሲባል እንደምርቱ ዕድገትና እንደአስፈላጊነቱ አንዳንድ የማኔጅመንት ዘርፍ የሆኑ ተግባራትን ማከናወን መጀመሩን ብቻ የሚያመለክት መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት ። ማኔጅመንት ሥርዓት እየያዘ የመጣው ከካፒታሊዝም ማደግ ጋር ነው ። በቅድመ ካፒታሊዝም የምርት ዕድገት ውስጥ የምርት አመራርን የሚመለከቱ ነገር ግን ገና መልክ ይዘው ያልወጡ ተግባራት እያደር በማኔጅመንት ሥር ተጠቃለሉ ።

የካፒታሊስት ሥርዓት መስፋፋትና የማኔጅመንት ዕድገት

የማኔጅመንት ባሕርያትና ዘዴዎቹ ከካፒታሊስት ስልተምርት ጋር እየተለዋወጡ መጥተዋል ። ይህንንም ቀጥለን ደረጃ በደረጃ ለማየት እንሞክራለን ።

ከጐጆና ከእደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ወደካፒታሊስት ኢንዱስትሪ የተደረገው ሽግግር ከፊውዳላዊ ሥርዓት ወደ ካፒታሊስታዊ ሥርዓት ከተደረገው ሽግግር ጋር የተያያዘ ነው ። የሥርዓቱ ሽግግር የምርት ኃይሎችን ዕድገትና የምርት ተግባርን ማኅበራዊ ፣ ኤኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና የአመራሩን ዘዴ ለውጦታል ። ማለትም በአሮጌው ፊውዳል ኅብረተሰብ ውስጥ ከእደ ጥበብ ኢንዱስትሪ ወደ ካፒታሊስት ኢንዱስትሪ መሸጋገሪያው መሠረት ሲጣል የምርት ሁኔታ እየተለወጠ ፣ እየተስፋፋና እየተወሳሰበ በመምጣቱ የግድ የተወሰነ ሥርዓት የያዘ የማስተባበር ተግባርንና ሥራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ሥራው ስለሚካሄድበት ሁኔታና ስለሂደቱ ቅደም ተከተልም ሆነ ስለ ውጤቱ ግልጽ የሆነ ሐሳብ መኖርን የሚጠይቅ እየሆነ መጣ ።

ካፒታሊዝም ሦስት የዕድገት ደረጃዎች አሉት ። እነዚህም ቀላል የካፒታሊስት የኅብረት አሠራር ፣ የመጀመሪያው ደረጃ የፋብሪካ ሥራና የኢንዱስትሪ ወይም የማሽን ምርት ደረጃዎች ናቸው ። ቀላል የካፒታሊስት የኅብረት አሠራር. . .በአንድ ካፒታሊስት ቁጥጥር ሥር በተለያዩ ቦታዎች በዛ ያሉ ሰዎች የተለያዩ የምርት ሥራዎችን የሚያከናውኑበት ሂደት ነው ። [4]

ከቀላል የካፒታሊስት የኅብረት አሠራር በፊትም ቢሆን በኅብረተሰብ ውስጥ በሙያ ዘርፍ አኳያ/ግብርና ፣ እርሻ ፣ እደጥበብ/ የሥራ ክፍፍል የነበረ ቢሆንም የሥራ ክፍፍል እያንዳንዱ የምርት ተግባር በተለያዩ ባለሙያዎች የሚሠራ አልነበረም ። በቀላል የካፒታሊስት የኅብረት አሠራር ውስጥ ባለሙያዎች ይጠቀሙ የነበረውም በዚያው በእደ ጥበብ ቴክኖሎጂአቸው ነበር ። ይህም በመሆኑ ምንም እንኳ ባለሙያዎቹ በንግድ ካፒታሊዝም የግል ሀብት ሥር ቢሰባሰቡም ከዚህ ላይ ባለሙያዎቹ ሁልጊዜ በአካል በአንድ የሥራ አመራር ሥር አልነበሩም ። የእደ ጥበብ ሙያውና ችሎታው ያላቸው ባለቤቶቹ በመሆናቸው የምርት ሥራ ሂደቱንም ይቆጣ

Digitized by Google

ጠራሉ ። በሌላ አነጋገር ካፒታሊስቱ ገና የሥራው ሂደት ዋናው ተቆጣጣሪ አልሆነም ማለት ነው ። ይሁንና የምርት ሁኔታው በመለወጡ ፣ ማለትም የአምራቾች በአንድ ላይ ተሰባስበው እንዲሠሩ መሆናቸው የምርት ሥራቸው መያያዝ ብቻ ራሱ ለማኔጅመንት ችግሮች መስፋፋትና አዲስ መልክ መያዝ መሠረት ጥሏል ። ምክንያቱም ይህ ብዙ ባለሙያዎችን በአንድ ላይ አድርጐ የማሠራቱ ተግባር ፣ አምራቾች በኅብረት እንዲያመርቱ ማድረግ ፣ በአሠሪው በኩል ተገቢ የሥራ ቦታ የመስጠትን ፣ የሥራውን ሂደት ሥርዓት ለማስያዝ ጥረት የማድረግን ፣ ምን መመሪት እንዳለበት፣በማን መመሪት ያለበት መሆኑን፣ ምን ያህል መመሪት እንዳለበት የመወሰንን፣ እና የመሳሰሉትን ተግባራት የሚጠይቅ ነውና ነው ። [5] ይህንንም ለማድረግ የታቀደውን ተግባር በቅድሚያ በሐሳብ ደረጃ ግልጽ አድርጐ ማስቀመጥና ማየት መቻልን ፣ የማደራጀትና ቀጥሎም ይህንኑ ወደተግባር ለመለወጥ የተወሰነ የማስተባበር ሥራን ይጠይቃል ። ይህም የማኔጅመንት ሥራ ነው ።

በካፒቲሊዝም የዕድገት ሂደት ውስጥ ሁለተኛው ደረጃ የሆነው የፋብሪካ ሥራ የፈጠረው የሥራ ክፍፍል የማኔጅመንትን ተግባር የበለጠ አስፋፋው ። ይህ የዕድገት ደረጃ ባንድ በኩል ሠራተኛው በቀጥታ በካፒታሊስት ተቀጥሮ ባንድ ጣራ ሥር ተሰባስቦ የሚሠራበትና ካፒታሊስቱም እንደማናቸውም የማምረቻ መሣሪያዎች የሠራተኛውም ጉልበት ባለቤት የሆነበት ፣በሌላ በኩል የሥራ ክፍፍል ስፋትና ጥልቀት ያገኘበትና በአንድ ውሱን ሙያ የበለጠ በሳል መሆን (Specialization) እየተስፋፋ የመጣበት ደረጃ ነው ።

በዚህ ደረጃ የሠራተኛ አቀጣጠርና ሥምሪት ሁኔታ ማዕከላዊነት ባለው መንገድ እንዲካሄድ በመደረጉ ለሥራ አመራር /ለማኔጅመንት/ አስፈላጊው መሠረት ተጣለ ። [6] ባለሙያዎች በተወሰኑ የምርት ተግባራት እንዲሠለጥኑና መሣሪያዎችም በዚሁ ዓይነት እንዲሠሩና እንዲሻሻሉ ተደረገ ። በዚህም የማኅበራዊ ሥራ የማምረት ዐቅምና ምርት አደገ ። ከዚሁ ዕድገት ጋር የሥራ በካፒታል ቁጥጥር ሥር መሆን የበለጠ ተጠናከር በዚሁ ወቅት በአእምሮ ሥራና በጉልበት ሥራ መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ሄደ።በሌላ አነጋገር ስለሥራ ሂደት የሚደረገው ጥናትና የሐሳብ ቅንጅት በራሱ በአምራቹ ሳይሆን በሌላ አካል የሚሆንበት ሁኔታ እያመዘነ መጣ ። የምርት ማከናወኛዎች ባለቤትነት ከሠራተኛው ወደ ካፒታሊስቱ ሲሸጋገር ምርትንና ሥራን የመቆጣጠሩ ኃላፊነትም አብሮ ከአምራቹ ወደአሠሪው መሸጋገር ጀመረ ።

በእነዚህ ለውጦች ምክንያት ሥራን ለመቆጣጠር እንዲቻል የተለያዩ የፋብሪካ ደንቦች ወጥተዋል ። የፋብሪካ ደንቦች የሚያተኩሩት ፣ መደበኛ የሥራ ሰዓት ለመወሰን ፣ የሠራተኛውን ባህርይ ለመቆጣጠርና ምርትን ለማሳደግ በሚቻልበት ዘዴ ላይ ሲሆን በመጀመሪያ የተነደፉትም ካፒታሊዝም በቅድሚያ በተስፋፋበት በእንግሊዝ ሀገር ኢንዱስትሪ ውስጥ ነበር ።

በፋብሪካ ውስጥ የማኔጅመንት ተግባር የሚከናወነው በፋብሪካው ባለቤት ነበር ። የምርት ሂደትን ፣ የጥሬ ዕቃ አቀራረብን ፣ የሥራ ኃይል ድልድልንና ቅንጅትን ፣ የምርት ውጤቶች ሽያጭን ወዘተ... በተመለከተ ሁሉ የሚያሻውን የማደራጀት ሥራን ያካሂዳል ። በአጭሩ ምርትን አጠቃሉ ይመራል።

የማኔጅመንት ችግሮች በጉልህ መታየት የጀመሩት በካፒታሊዝም 3ኛ የዕድገት ደረጃ ማለትም የካፒታሊስት ኢንዱስትሪ የበለጠ ባደገበት ከሥራ ክፍፍሉም መስፋት ጋር ካፒታሊስቱ የሥራ ኃይልን በነጻ ገበያ እየገዛ ባቋቋመው ፋብሪካ ውስጥ ከሚሠራበት ደረጃ ሲደርስና የጠቅላላው የምርት ሂደቱን የመቆጣጠሩ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ከሠራተኛው ወደ ካፒታሊስቱ ሲተላለፍ ነው ። አምራቹ ከምርት ማከናወኛው ሲነጠ

Digitized by Google

ልና ጉልበቱን ሽጦ ማደር ሲገደድ ካፒታሊ
ስቱ የካፒታሉ ባለቤት በመሆኑ ብቻ የማኔጅ
መንት ተግባሩ ባለቤትም ሆነ ። የማኔጅመ
ንት ሥራ ከምርት ማከናወኛዎች ባለቤትነት
ተንጠለና ሠራተኛው ሳይሆን ካፒታሊስቱ
የሥራ ሂደቱ ተቆጣጣሪ ሆነ ።

ካፒታሊስቱ በነጻ ገበያ የሚያገኘውን
ሠራተኛ በፈቃደኝነት ኮንትራት ውስጥ በማ
ስገባት ይቀጥራል ። ሁለቱን ወገኖች የሚያገ
ናኛቸው የጋራ ጥቅም ኖሮ ሳይሆን ሠራተ
ኛው ከረሀብ ሲሸሽ ካፒታሊስቱም ትርፍ
ሊፈልግ ነው ። ተፃራሪ ጥቅም ኖሮአቸው
ሳለ አንዱ ካለሌላው ሊኖር የማይችልበት
ሁኔታ ነው ያገናኛቸው ። ስለሆነም በበለጠ
ማምረት ፣ ማከማቸትና ካፒታሉን ማሳደግ
ይሻልና፥ቅጥር ጉልበትን ተጠቅሞ የሚያሠ
ራው ካፒታሊስት ፣ ያለምርት የምታልፍ
ሰዓት የምታስከትለውን ወጪ በጥንቃቄ አስ
ልቶ ይቆጣጠራል ። ባንጻሩ ደግሞ ሠራተ
ኛው ከምርት ዕድገት ውስጥ የሚያየው የተ
ሻለ ተስፋ ባለመኖሩ ራሱን ከመደገፍ የሚ
ያልፍ ምርት ለማምረት አይገፋፋም ። በዚ
ህም ምክንያት ካፒታሊስቱ ሠራተኛው የተ
ቻለውን ያህል ምርታማ እንዲሆን ፣ ከምንጊ
ዜውም በበለጠ እንዲያመርት ማስገደጃ ዘዴ
ዎችን መቀየስ አለበት ።

ከቅጥር ሠራተኞቹ ጉልበት የሚቻለውን
ሁሉ ጨምቆ ለማውጣት ይችል ዘንድም
ከፍ ያሉ የምርት ጥራት ደረጃዎችን ፣ በእያን
ዳንዱ የምርት ጊዜ የሚወጣውን የምርት
መጠን ከፍ አድርጐ መወሰን ፣ የሠራተኛ
ውን እንቅስቃሴና የምርትን መቀዝቀዝ ወይ
ም መቋረጥን ወይም ማንኛውም የፋብሪካ
ዲስፐሊን መጓደል የሚያስከትሉ አድራጐ
ቶችን ሁሉ በጥብቅ መቆጣጠር ይጀምራል።
ይህም የማኔጅመንት ተግባርን ይበልጥ ውስ
ብስብ እየሆነ እንዲሄድ ያደርጋል ፣ አድርጐ
ታልም ።

በዚህ የከፍተኛ ደረጃ ማሽን ኢንዱስትሪ
ግቡብ በጀመረበት ወቅት /ማለትም ከ1860
በኋላ/ ካፒታሊስቱ በዓይነትም ሆነ በስፋት
ይበልጥ የተወሳሰቡ የማኔጅመንት ችግሮች
ገጠሙት ። ለችግሮቹም እልባት ለማግኘት
የማኔጅመንት ጽንሰሐሳብ አንድ የተቀናጀ
ንድፈ ሐሳባዊ መልክ መያዝ ጀመረ ። ይህም
ወቅት ማዕከላዊነት እጅግ ጠብቆ የታየበት
ባንፃሩ ግን የካፒታሉ ባለቤት የማኔጅመ
ንትን ተግባር ራሱ ማካሄድ ማስፈለጉ ያበቃ
በትና በምትኩ ሥራው ለቅጥር ማኔጀሮች
የተተወበት ወቅት ነበር ።

ይህ ዕድገት ቢታይም እስከ 20ኛው ምዕት
ዓመት መግቢያ ድረስ የማኔጅመንት ተግባ
ር በአመዛኙ ይከናወን የነበረው ከትውልድ
ወደትውልድ ሲሸጋገሩ በመጡና ካለፈው
ልምድ በተገኙ ዘዴዎች አማካይነት ነበር ።
የማኔጅመንት ተግባር ሳይንሳዊ ባሕርይ
ባላቸው መርሆዎች ላይ እየተዋቀረና መርሆ
ዎቹም ሳይንሳዊ በሆኑ ንድፈሐሳቦች መልክ
መቀነባበር የጀመሩት ካፒታሊዝም ወደሞኖ
ፖል ደረጃው መሸጋገር ሲጀምርና የሥራ
ክፍፍሉ እጅግ ሰፍቶ የምርት ሥራ በበለጠ
ማኀበራዊ በሆነበት ወቅት ነው ።

የ19ኛው ምዕት ዓመት ማብቂያና
የ20ኛው ምዕት ዓመት መግቢያ ካፒ
ታሊዝም በዕድገቱ ወደከፍተኛ ደረጃ መሸጋ
ገር የጀመረበት በመሆኑ በጣም ግዙፍ እየ
ሆነ በማደግ ላይ በነበሩ የካፒታሊስት የም
ርት ተቋሞች ውስጥ የሚካሄደውን ሥራ
/በአጠቃላይ ምርትን/ የሚመለከቱ ውስብ
ስብ ችግሮችን ለመፍታት ሳይንሳዊ ዘዴዎ
ችን በመጠቀም ሙከራ ማድረግ የተጀመረ
በት ወቅት ነበር ። በመሠረቱ በዚህ ጊዜ የነ
በረውን የካፒታሊዝምን ዕድገት በመመርመ
ር በማኔጅመንት ሳይንስ ፣ ዘዴዎችና በሥራ
አደረጃጀት ጥበብ ዕድገት ላይ ያስከተለውን
ለውጥ /ተፅዕኖ/ እንደሚከተለው ለማየት
ይቻላል ።

የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዕድገት አንቀሳ
ቃሽ ኃይል ውድድር ነው ። በዚህም ውድ
ድር ውስጥ ጥቂት የካፒታሊስት የማምረቻ

Digitized by Google

ተጽዋች እየከሠሩ እየተንኮታኮቱ ሲሄዱ በአሸናፊነት የወጡት ደግሞ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ ። አሸናፊዎቹ የአመራረት ቴክኒኮችንና ዘዴዎችን አከለው በማሻሻል የበለጠ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ ። ይህ ዕድገት በተለይ ጉልህ ለውጥ ያሳየው በ19ኛው ምዕት ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በተለይም በማከተሚያው ላይ ነው ።

ለውጡ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል። አንደኛ የምርት ኃይሎችን ባሕርይ በተመለከተ የታየው ለውጥ ነው ። በዚህ ዘመን የኤሌክትሪክ ሞተሮች ተሠሩ ። ውስጠ ነደድ ሞተሮች (Internal Combustion Engine) ተፈልስፈው በኢንዱስትሪና በትራንስፖርት አገልግሎቶች ውስጥ ተስፋፉ ፤ አዳዲስ የብረት ማጣሪያና የኬሚካል ማምረቻ ዘዴዎች ተገኙ ። በእንፋሎት የሚሠሩ ሞተሮችም ተፈለሰፉ ። የምርት ኃይሎች በከፍተኛ ደረጃ ዕድገት አሳዩ ። ከዚህ የምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር በቀላል ኢንዱስትሪና በከባድ ኢንዱስትሪ መሐል ያለው ግንኙነት ባሕርይም ተለወጠ ። የታዳጊው የነፃ ውድድር ካፒታሊዝም መሰያ በነበሩት ቀላል ኢንዱስትሪዎች ፋንታ ሚዛኑ ለከባድ ኢንዱስትሪ ዕድገት እያደላ በታዳጊነታቸው የላቁት ከባድ ኢንዱስትሪዎች ተስፋፉ ።

በዚህ ጊዜ በአንድ በኩል አዳዲስ ቴክኖሎጂና የምርት ዘዴዎችን መጠቀም መቻሉ የምርትን ሥራ ሲያፋጥንና ሲያቀላጥፍ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምርትን መጠን፣ ስፋትና የመሰባሰብ ዝንባሌን በሰፊው አስከትሏል ። ይህ ግዙፍ ለሆኑ የምርት ተቋሞች መፈጠር፣ ለሞኖፖሎች መስፋፋት አመቺ ሁኔታዎችን አዘጋጀ ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት ማከተሚያ ላይ የሣኔጅመንት መሠረተ ሐሳቦች በሥርዓት እየተቀናጁ ሳይንስን በመጠቀም ላይ የተመሠረተ ማኔጅመንት መታየት ጀመረ ። አጀማመሩም ከነዚህ ከላይ ከተገለጹት በካፒታሊዝም ዕድገት ሂደት ውስጥ ከታዩት ለውጦች ጋር የተያያዘ ነው ። ይህም ባንድ በኩል ከሞኖፖሎች መፈጠር ጋር የባሰ አስከፊ እየሆነ ከሄደው ካፒታሊስት ውድድር ለመዳን ፤ ተወዳዳሪን ለመርታት ፤ ካፒታሊስት ትርፍን በተቻለ ሁሉ ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ቴክኒኮችን መጠቀም ብቻ ሳይሆን ሳይንሳዊ የሆነ የሥራ አደረጃጀትና ማኔጅመንት መኖር የግድ አስፈላጊ እየሆነ በመምጣቱ ነው ። ሞኖፖሎች ሲፈጠሩና የምርት መሰባሰብ በከፍተኛ ደረጃ ሲከናወን የማምረቻ ድርጅቶችም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን በሥራቸው ሲያሠማሩ ፤ በብዙ ሚሊዮን ገንዘብ የሚገመት መሣሪያ ሲያንቀሳቅሱ ፤ ሸቀጣቸውን ከሀገር ደረጃ አልፎም በዓለም ገበያ ማሠራጨት ሲችሉና ሲጀምሩ የሥራ ሂደትን በጥቅሉ ሳይሆን በዝርዝሩ በረቀቀና በተሟላ ሁኔታ መቆጣጠርና የማምረቻ ተቋሞችንም የተለያዩ ዘርፎች ማስተባበርና ማቀናጀት እንዲሁም የምርት ወጭውንም ሆነ ገቢውን በሚገባ መቆጣጠር የግድ አስፈላጊ ሆነ ። በአጭሩ ጠቅላላው የውሳኔ አሰጣጥና የማደራጀት ተግባር ሁሉ በጥንቃቄ የተመረጡ ግቦችን ሊያስገኝ በሚችል ሁኔታ መካሔድ ያለበት መሆኑ በጣም አንገብጋቢ እየሆነ መጣ ማለት ነው ።

ካፒታሊዝም በተለይም በዚህ በኢምፔሪያሊስት ደረጃው የሰብአዊ ሥራን የማምረት ዐቅም በከፍተኛ በማሳደግ ዓይነቱን በማስፋትና በማወሳሰብ እንዲሁም መልሶ በማስተባበር ማኅበራዊ ቁጥጥርን የበለጠ አስፈላጊ አድርጎታል ። ከሁሉ በላይ ደግሞ የሥራ ቅልጥፍናን በመጨመርና የሥራ ምርታማነትን በማሳደግ ፣ የሠራተኛውን ጉልበት በሚቻለው መንገድ ሁሉ በመበዝበዝ ትርፍን የማሳደግ ፍላጐት እየጨመረ መምጣት ለሳይንሳዊ የማኔጅመንት ንድፈ ሐሳቦች መስፋፋት ዋነኛ መነሻ ነበር ።

በሌላ አባባል ከተጠቀሰው ለውጥና ዕድገት ጋር ቁጥጥር ወይም ሰፋ ባለው አገላለጽ ሥርዓት የያዘ ማኔጅመንት የብዙዎ

Digitized by Google

ችን ትኩረት መሳብ ጀመረ ፤ ብሎም እያ
ሌና ዝርዝር የኢንዱስትሪ ማኔጅመንት
ሥነ፡ዓቶች እንዲወጡ ጋበዘ ። [7]

በቡርዧ ሥነ ጽሑፍና ኢንዱስትሪ
ውስጥ የሳይንሳዊ ማኔጅመንት ጽንሰ ሐሳ
ብን ያስፋፋው ፍሬዴሪክ ዊንስላው ቴይ
ለር የሚባል አሜሪካዊ መሐንዲስ ነው ።
ንድፈ ሐሳቡ ወይም ዘዴው ቴይለሪዝም
በመባል ይታወቃል ። ቴይለር ዓላማው
ምርታማነት ሊያድግ የሚችልበትን ሁኔታ
መንደፍና በተግባር ማዋል ስለነበር ምኞቱ፣
ሙከራውና ጥናቱ የሚያተኩረው የሥራ
ሂደት አደረጃጀትን መሠረታዊ ሐሳቦች፡፡
በመለየትና የሚፈለገውንም ነገር ለማስ
ደረግ እንዲቻል የሠራተኛውን ጠባይ
(Behaviour) ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር
የሚያስችሉ ዘዴዎችን በመንደፍ ላይ ነበር ።
በአጭሩ የትኩረቱ ነጥቦች የሥራና የም
ርት ሂደት አደረጃጀት ሁኔታዎች ነበሩ ።
ጥናቱም ከዚህ በፊት እንደነበረው ካለፈው
ልምድ ላይ ብቻ ተመሥርቶ የሚካሄድ
ሳይሆን ሳይንሳዊ የምርምርና የሙከራ ዘዴ
ዎችን በመጠቀም የሚካሄድ የምርት አደ
ረጃጀትንና የክፍያ ዘዴን መፍጠር ነበር።

ጥናቱ ተሳክቶ በ20ኛው ምዕት ዓመት
መጀመሪያ ላይ በአሜሪካ የማምረቻ ተቋ
ሞች ውስጥ በሥራ ላይ መዋል ጀመረ ።

በዚህ የምርት ስደረጀጀትና የክፍያ ዘደ
መሠረት የብርቱና የፈጣን ወዝስደሮች
የሥራ እንቅስቃሲና ስንድን ሥራ ለማከ
ናወን የሚወስድባቸውን ጊዚ ለተወሰነ
ወቀት በመመዝገብና በማጥናት የስደረጀ
ጀትና የስከፋፈል ደረጀ ይወስናል ።
ከዚህ በኋላ ወዝስደሮች ይህን በስዲስ
የተወሰነውን ደረጀ መሠረት በማድረገ
ስንዲያመርቱ ይደረጋል ። በዚህ ደረጀ ለማ
ምረተ ያልቻሉተ የክፍያቸው ምጣኔ ዝቀ
ስንዲል ይደረጋል ። [8]

በቴይለር አመለካከት አንድ ሰው በአንድ
የምርት ቀን ወይም በአንድ የምርት
ሰዓት ምንያህል ያመርት እንደሆነ

ወይም ማምረት እንዳለበት የሚወሰነው
ባለፉት የምርት ዘመናት ሲመረት የነ
በረበትን በማገናዘብ ሳይሆን ሳይንሳዊ
በሆነ መንገድ የጊዜና የእንቅስቃሴ ጥናት
(Time and motion study) ተደርጐ
በመሆኑ ሥርዓቱ በባሕርዩ ሳይንሳዊ ይዘት
ጭምር ያለው ነው ። ይህንኑ ሌኒን «የቴይ
ለር ቅንብር ከፍተኛ የሳይንስ ዕድገትን
የሚገልጽ ፤ የምርትን ሂደት በብልሃት የሚ
መረምርና ወደከፍተኛ የማኅበራዊ ሥራ
ውጤታማነት ዕድገት የሚመራ መሆኑን
ለአንድ ደቂቃ እንኳ ልንዘነጋ አይገባም»[9]
ሲል በአድናቆት ተናግሮታል ። ለመጀመ
ሪያ ጊዜ «ሳይንሳዊ ማኔጅመንት » የሚለ
ውን ቃል የተጠቀመበትም ቴይለር ነው።

ይሁን እንጂ የቴይለሪዝም ንድፈ ሐሳብ
ዓላማ ቅጥር ጉልበትን (የሥራ ኃይልን) የመ
ቆጣጠር ጥያቄ ነው።በቴይለር አመለካከት
ማሰብና ሥራን መሥራት ለየብቻ መከናወን
ያለባቸው ነገሮች ናቸው ። የማሰቡ ሥራ
የማኔጅመንት (የአሠሪው አካል) ተግባር
ነው ። ሥራን መሥራት ደግሞ የሠራተ
ኛው ነው ። ስለእያንዳንዱ የሥራ እንቅስ
ቃሴ ዝርዝሩ በማኔጅመንት ተጠንቶ ይወ
ሰናል ፤ ለእያንዳንዱ ሠራተኛ እያንዳንዱን
ሥራ ለማከናወን የሚያደርገው እንቅስ
ቃሴ ሁሉ ተሰፍሮ ይወሰናል ። ሠራተ
ኛው ለማሰብ ጊዜ ሳያጠፋ እያንዳዱንን
ሥራ እንደተወሰነለት ያከናውናል ። እያ
ንዳንዱን የምርት ውጤት ለማምረት
የሚፈጀው ሁሉ በዕውቅ የተመረጡ ሰዎ
ችን የማምረት ዐቅምና የምርት ማነስ
ደረጃ መሠረት አድርጐ ፣ እያንዳንዱን
የምርት ውጤት ለማምረት የሚፈሰው ጥሬ
ዕቃ ወይም በአጠቃላይ ወጪው የሚ
ወሰነውም እጅግ ጥንቁቅና ቆጣቢ በሆነው
ሠራተኛ ምሳሌነት ስለሆነ ወጪን ለመቀ
ነስ፣የሥራ ቅልጥፍናንም በማሳደግ ምርታ
ማነት እንዲያድግ ለማድረግ የሚቻልበት
ሁኔታ ሁሉ ይዘጋጃል ።

በቴይለር ገምት ማኔጅመንት በሠራተ
ኛው ውስጥ የመሥራት ፣ የመጣጣርና የመ

Digitized by Google

ትጋት ፍላጐትንና ስሜትን በመፍጠር ባሕርዩን በሚፈልገው መንገድ ፣ ለመገራት የሥራ ሂደቱን ለመቆጣጠርና የምርታማነት ዕድገትን ከፍ ለማድረግ የሚደረግ ጥረትና ሙከራ ፍሬ ቢስ ነው ። ስለዚህ ማኔጅመንት ምርታማነትን የማሳደግን ተግባር ለሠራተኛው ፍላጐትና ጥረት ትቶ ይህን ፍላጐት ፣ በሠራተኛው ውስጥ ለመፍጠር በመታገል ፈንታ ስለሥራው ያለውን ዝርዝር ዕውቀት በቁጥጥር ሥር በማምጣትና ሥራውን በአዲስ ዓይነት በማደራጀት ሠራተኛው ያለማሰብ እንደመኪና የሚሠራበትና ፣ ማኔጅመንት ደግሞ ሙሉውን የሥራ ሂደት የሚቆጣጠርበት ሁኔታ መፍጠር አለበት ነው የሚለው ።

የቴይለር ሳይንሳዊ ማኔጅመንት ሥርዓት ምንም እንኳ በማኔጅመንት ጽንስ ሐሳብ ውስጥ ዞር ዞር ማዕከላዊ ቦታ የሚይዘው ቁጥጥር ቢሆንም ፣ ብዙ በመበዝበዝ ትርፍን ለማሳደግ የሚደረግ በጣም አስከፊና ርኅራሄ የለሽ የቁጥጥር ዘዴዎችን የሚያቅፍ ነው ። ስለዚህ ቴይለር ትክክለኛ የሒሳብ አያያዝና የቁጥጥር ዘዴዎችን ወዘተ . . . በማስተዋወቅ ጉልህ ሥራ የሠራ ቢሆንም የዘዴው ሌላ ገጽታ የዘመኑ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፍሬ እጅግ አስከፊ ለሆነ የብዝበዛ ተግባር የዋለበት ነበር ። ይህንኑ ሁለት ተቃራኒ ገጽታዎች የሚያሳየውን ዕድገት ሌኒን በግልጽ እንደሚከተለው አስቀምጦታል ። «የቴይለር ቅንብር . . . የቡርዧ ብዝበዛ አስከፊ ጭካኔ ባንድ በኩልና በሌላ በኩል ደግሞ በሥራ ወቅት የሚደረግ አካላዊ እንቅስቃሴን በመተንተን ፣ አስፈላጊና ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴን በማስወገድ ትክክለኛ የሥራ ዘዴዎችን በማብራራት ፣ ምርጥ የሒሳብ አያያዝና ቁጥጥር ሥርዓት በማስተዋወቅ መስክ የተመዘገቡ ሳይንሳዊ ግኝቶች ድብልቅ ነው ።» [10]

የቴይለር የሳይንሳዊ ማኔጅመንት ንድፈ ሐሳብ ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን ያዘለና የሚያንፀባርቅ ነበር ማለት ነው ። ይህም ባንድ በኩል ስለሥራው ባሕርይና አደረጃጀት የሚደረገው ጥናትና ውሳኔ ሳይንሳዊ ዘዴዎችን በመጠቀም በመሆኑ ሳይንሳዊነት ሲኖረውና በዚህም በኩል የሰው ልጅ በዕድገት እንዳስገኘው የሥራ ውጤት የሚታይ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ነባራዊ የኢኮኖሚ ሕጎችን ዐውቆና ተረድቶ ሳይሆን ባለው ሁኔታ የሠራተኛውን አድራጐትና ጠባይ ካፒታል በሚፈልገው አኳያ መግራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ብቻ የሚያተኩር በመሆኑ ፣ ለሰው ልጅ የተሟላ ዕድገትና ብልጽግና ሲባል የምርትና በአጠቃላይም የማኅበራዊ ዕድገትን ሂደት ለማፋጠን ሳይሆን ሥራን በሙሉ ተቆጣጥሮ ለቡርዧው ከፍተኛ ትርፍ የማምጣት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የታቀደ በመሆኑ ኢሳይንሳዊ ይዘት አለው ።

«ቴይለሪዝም በካፒታሊስት ስልተ ምርት ውስጥ ወዝአደሩን ለመበዝበዝ የሚያስችል ዓይነተኛ መሣሪያ ይሁን እንጂ ሳይንሳዊነት ያለው የሥራ አደረጃጀትና የምርታማነት ማሳደጊያ ዘዴም በመሆኑ በሶሻሊዝም ውስጥ ከሠራተኛው እንክብካቤ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ የሕዝቡን ፍላጐት ለማርካት» [11] አስተዋጽኦ ሊያደርግ መቻሉ አሌ የማይባል ሐቅ ነው ።

የምርት በበለጠ መሰባሰብና የካፒታሊስት ማኔጅመንት ሥልት ያሳየው ለውጥ

የካፒታል የበለጠ መማከልና መሰባሰብ የምርትን ማኅበራዊነት በበለጠ ያሳድገዋል ። በዚህ ሂደት ውስጥ በየጊዜው እየሰፋ የሚሄደው በቡርዧ ኅብረተሰብ ወደ በለጠ የሞኖፖሎች ውኅደት ያመራል ። ይህም እያደገ ሲሄድ የግል ሞኖፖሎችና የመንግሥት ውኅደትን ፈጠረ ። መንግሥቱ ብዙ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎችን መቆጣጠርና ማስተናበር ጀመረ ። በዚህ ሂደት ውስጥ መንግሥትም ራሱ የበለጠ በሞኖፖል ቡርዧው ቁጥጥር ሥር ስለሚሆን ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠርና ለመም

Digitized by Google

ራት መንግሥታዊ ሞኖፖል ተፈጠረ ማለት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ዓይነቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው የምርት መሰባሰብና ማኅበራዊ ባሕርይ መያዝ በአንፃሩ የላቀ ማኅበራዊ ማኔጅመንትና ቁጥጥር እንዲኖር መጠየቁ የሚታወቅ ነው ። ስለሆነም በሞኖፖል ካፒታሊዝም ልዩ የሆኑና የረቀቁ መንግሥታዊ የቁጥጥርና የማስተባበሪያ ድርጅታዊ መዋቅሮች ተዘረጉ ። የምርት ጊዜን ለመቆጠብ ፣ የሥራ ምርታማነትን ለማሳደግ ፣ ምርትን በቀለጠፈ ሁኔታ ለማደራጀት ፣ የምርት ተግባርን በብቃት ለመቆጣጠር ወዘተ . . . . የሚረዱ አዳዲስና የላቁ ዘዴዎችም ተፈጠሩ ። ስለዚህ ካፒታሊዝም በዕድገት ሂደቱ ውስጥ የምርት ኃይሎችን በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻልና የምርትን መሰባሰብ ከፍ በማድረግ የረቀቁ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ዘዴዎችን እየያዘ መጥቷል ማለት ነው ። ይህም በእያንዳንዱ የምርት ተቋም ደረጃ ብቻ ውሱን የሆነ ሳይሆን በብሔራዊ ደረጃ ምርትን በዕቅድ ለመምራትና ለመቆጣጠር በሚደረገው ሙከራም ጭምር የሚታይና የሚገለጽ ነው ።

ይህን ሐቅ መነሻ በማድረግ የካፒታሊስት ማኔጅመንትን ውስጣዊ ባሕርይ ያልሆነውን አስመስለው ለማቅረብ የሚጥሩ የቡርዧ ምሁራን ብዙ ናቸው ። እነዚህ ምሁራን ኢምፔሪያሊዝም ወይም ካፒታሊዝም በሞኖፖል ደረጃ ሲደርስ ልዩ «ሕዝባዊ» አቋምና ባሕርይ ይዞ እንደመጣ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። ግጭትና ውድድር የተወገደበት ሥርዓት ይዞ ወደተደራጀና ውስጣዊ ቅንብሩን በገዛ ራሱ ወደሚቆጣጠር ካፒታሊዝም የተደረገ ዕድገት ነው ይላሉ ።

ይህንኑ መሠረት በማድረግና አንዳንድ የሠራተኛውን ማኅበራዊና ሥነልቡናዊ ፍላጎቶች የማርካት አስፈላጊነትን የሚቀበሉ የማኔጅመንት ስልቶችንም በማንግትና በመስበክ ሠራተኛው በምርት ማኔጅመንት ውስጥ የመካፈል ሰፊ ዕድል አግኝቷል ይላሉ ። ለዚህ አንዱ ምሳሌ ከ1935 ከኋላ በቡርዧ ሥነ ጽሑፍ ተስፋፍቶ የሚታየው የሰብአዊ ግንኙነቶች ንድፈ ሐሳብ (Human Relations Theory) ነው ።በዚህ ንድፈ ሐሳብ የቡርዧው ማኔጅመንት ከምንጊዜውም የበለጠ ዲሞክራሲያዊ እንደሆነ ተደርጎ ይቀርባል ።

ይሁንና አንድ ነገር መዘንጋት የለበትም። ይኸውም በማንኛውም መደባዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ማኔጅመንት የሚያገለግለው ዞር ዞር በሥልጣን ላይ ያለውን መደብ ነው። በመሠረቱም መደባዊ ነው ። ስለሆነም በቡርዧ ኅብረተሰብ ውስጥ ማኔጅመንት ፣ሥራንና ምርትን የመቆጣጠር ተግባርና የሚቀየሱ ዘዴዎች ሁሉ መሠረታዊ ዓላማ የቡርዧውን መደብ ጥቅምና ፍላጎት ማርካት ነው ።«የሠራተኛውን መደብ በመበዝበዝ ተረፈ እሴትን ማሳደግ በካፒታሊዝም ውስጥ ዋነኛውና የዘለቄታው (ultimate) የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ግብ ነው» [12] ይህም ባለው የምርት ግንኙነት የሚወሰን በመሆኑ የካፒታሊዝም ወደ መንግሥታዊ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ማደግ የካፒታሊስት ማኔጅመንት የብዝበዛ ባሕርይን ሊለውጥ የሚችል አይደለም ። እጅግ የበዛ ማዕከላዊነት ከተጫነውና ቢሮክራሲያዊ ከነበረው ማኔጅመንት «ዲሞክራሲያዊ» ወደሆነ ማኔጅመንት የተደረገው ማዘንበልና በቡርዧ ማኔጅመንት ውስጥ ለሠራተኛው ሰብዕና አንዳንድ ግምቶችን ለመስጠት ሲደረግ የሚታየው አዝማሚያም ቢሆን አንደኛ፣ በሠራተኛው መደብ የትግል እንቅስቃሴ እያየለ መምጣት በመገደድ ፣ ሁለተኛ ፣ በ1917 ሶሻሊዝም በሩሲያ ድል ካደረገ በኋላ የታዩት አዲስ ሁኔታዎች በቡርዧው በኩል አዳዲስና ለዘብ ያሉ የትግል ሥልቶች ካልተቀየሱ በቀር እንደተቀድሞው ነገሮች ሊቀጥሉ ባለመቻላቸው የመጣ እንጂ በካፒታሊስት ሥርዓት ባሕርይ መለወጥ ወይም

Digitized by Google

ለሠራተኛው በመቆርቆር አይደለም ። የቡርዧው አስተምህሮ ፍሬ ነገር [13] በአሠሪውና በሠራተኛው መሐል መንፈሳዊ አንድነት ለመመሥረት በዚህም ሠራተኛን የቡርዧው ታዛዥ ማድረግ ፣ በዘመናችን የካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የካፒታሊስቶች ፍላጐት እንዲሟላና የካፒታሊዝም ሥርዓትም ማኅበራዊ ተቀባይነት እንዲያገኝ መጣር፣ሠራተኛውም ለኢኮኖሚ ጥቅም ማግኘት ገድ እንዳይኖረው ለማደንዘዝና በመሥራቱ ብቻ ተደሳች እንዲሆን መገፋፋት፣ካፒታሊስቱና ሠራተኛው ተመሳሳይ የጋራ ጥቅም ያላቸው አስመስሎ ማቅረብ ነው ። የቡርዧ ምሁራን ይህን ቢሉም ሠራተኛውም የጥንቱ ተመዝባሪ ፣ ቡርዧውም እንደበፊቱ በዝባዥ ናቸው ። ስለሆነም ይህ የሠራተኛውንና የቡርዧውን ፍላጐት ለማመሳሰል የሚደረገው ጥረት የማይታረቀውን ለማስታረቅ መሞከርና የሠራተኛውን የመደብ ትግል ለማለዘብ የታቀደ ነው ።

በእርግጥ የካፒታሊዝም መዳበር ለሶሻሊዝምና ለሳይንሳዊ ማኔጅመንት መሠረት የሚጥል መሆኑ አይካድም ። የካፒታሊዝምን ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት ፣ ቀውስንና ሥራ አጥነትን ለመቋቋም ጥረት ይደረጋል ። ገብታዊ የማኔጅመንት ሁኔታዎችን ለመግታትና በካፒታሊስቱ ንቁ ተሳትፎ ኢኮኖሚውን በፕላን ለመምራትም ሲሞከር ይታያል ። ይሁንና የግል ይዞታ እስካለ ድረስ በካፒታሊዝም ውስጥ የኢኮኖሚ ዕድገትን በብሔራዊ ደረጃ ለማቀድ በአጠቃላይም በማዕከላዊ ማኔጅመንት ሥር ለማምጣት ፈጽሞ የማይቻል ነው ። ካፒታሊዝም የግል ይዞታ የሰፈነበት በመሆኑ ሸቀጥ አምራቾች ምርትን በመቆጣጠር ሙሉ በሙሉ በራሳቸው ነፃ ፍላጐት ብቻ የሚመሩ ናቸው ።

ስለዚህ ምንም እንኳ በእያንዳንዱ የማምረቻ ተቋም ደረጃ ምርትን ለማቀድ ቢሞከርና ቢቻልም በብሔራዊ ደረጃ የካፒታሊስቶችን ውድድርና የምርት ሥርዓት አልባነትን ማስወገድ ፈጽሞ አይቻልም ። የካፒታሊስት ሥርዓት የሥራ ክፍፍልን እጅግ በማስፋትና ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ምርትን ማኅበራዊ በማድረግ ለሳይንሳዊ ማኔጅመንት ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ቢሆንም ሳይንሳዊ የምርት ማኔጅመንት በሙሉ ቅርጹ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በሶሻሊዝም ብቻ ነው ።

የኢኮኖሚ ማኔጅመንት በሶሻሊዝም

ቀደም ሲል እንደተጠቀመው በካፒታሊዝም ዕድገት ውስጥ የምርት ኃይሎች በከፍተኛ ደረጃ ያድጋሉ ፣ ምርትም እንዲሁ በከፍተኛ ደረጃ እየዳበረ ይሄዳል ። በዚሁ ሂደት ውስጥ የታየው የሳይንስ ዕድገትም አዳዲስ ቴክኖሎጂን ለማስገኘት አስችሏል ። ይህም ደግሞ በተራው የምርታማነትንና በአጠቃላይም የምርት ዕድገትን አስገኝቷል ። የምርት ዕድገት መገኘትም ደግሞ ኅብረተሰቡ ለሳይንስ ምርምር ከምንጊዜውም የበለጠ ከፍ ያለ የማቴሪያል፣ የገንዘብና የሰው ኃይል እንዲያውል ስለሚያስችለው አሁንም እንደገና ለበለጠ አዳዲስ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ሥራዎች ማበብ ሰፊ ዕድል ከፍቷል ።

ከዚህ ዕድገት ጋር የማኔጅመንት ተግባርም ይበልጥ እየረቀቀ መጥቷል ። ቴክኒካዊ በሆነው አኳያ ከተመለከትን ሶሻሊዝምም ሊጠቀምባቸው የሚችል ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ልምዶች ተከማችተዋል ። ብዝበዛን ለማስወገድ የሚታገለው ሠርቶ አደር ሕዝብ ሕዝባዊ ይዞታን ከመመሥረት ቀጥሎ ፣ ከሚጠብቁት መሠረታዊ ተግባራት መካከል አንዱ ነባራዊ የሆኑትን የኢኮኖሚ ሕጎች በመረዳት ላይ የተመሠረተ የምርታማ ማኔጅሚንት ሥርዓት መመሥረት ፣ ማኅበራዊ ምርት (ኢኮኖሚው) ሳይንሳዊ በሆነ ማኔጅመንት ሥር የሚመጣበትን ሥርዓት መዘርጋት ነው ።

ሳይንሳዊ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት የሚያቅፈው መሠረታዊ ድርጊት የኢኮኖሚ ሕጎ

Digitized by Google

ችን መሠረት አድርጐ የኢኮኖሚ ዕድገትን መምራትንና አቅጣጫ ማስያዝን ነው። በሶሻሊዝም የምርት ማኔጅመንት መሠረታዊ ነጥብ የሥራ ምርታማነትን ማሳደግን ግብ በማድረግ ምርትን ማደራጀትና ሂደቱንም በማስተዋል መቆጣጠር ነው ተብሎ ሊጠቃለል ይችላል። ምክንያቱም ዓላማው የሥራ ምርታማነትን በማሳደግ የኅብረተሰቡን ጥቅም ማራመድ ነውና ነው። የሥራ ምርታማነቱን ለማሳደግ ደግሞ የኅብረተሰቡን የሰውና የማቴሪያል ሀብት በሚገባና በብቃት መጠቀም ያሻል። ይህን ተግባራዊ ማድረጊያው መንገድም በወቅቱ ያሉትን የምርት ሁኔታዎች በማጤን ምርትን በማደራጀትና ሂደቱንም በማስተዋል በመቆጣጠር ብቻ ነው።

በሶሻሊዝም ኢኮኖሚውን በዚህ ዓይነት ለመምራት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ተሟልተው ይገኛሉ። በፖለቲካው የሠራተኛው ሕዝብ ሥልጣን መያዝ የመንግሥት ባሕርይ መሠረታዊ ለውጥ ሲሆን ፣ በኢኮኖሚው ደግሞ የምርት ማከናወኛዎች በሕዝብ ይዞታ ሥር መጠቃለል ነው። ስለዚህ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ አባላት በትግላቸው የተመሠረተው የሕዝባዊው ሀብት የጋራ ባለቤቶችና የኢኮኖሚ የበላይ በመሆናቸው አመራሩንም ይቆጣጠራሉ። ሕዝባዊ ይዞታ በመስፈኑ የገበያው የምርት ተቆጣጣሪነት ያበቃል። በቦታውም በዕቅድ የሚመራ የተመጣጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ሕግ መሥራት በመጀመሩ ኢኮኖሚውንና የምርት ዕድገትን በአንድ ወጥ ማዕከላዊ ማኔጅመንት ሥር ለማምጣት ይቻላል።

የምርት ማከናወኛዎችን በቁጥጥር ሥር ያደረገው ሠራተኛው ሕዝብ በሚወክለው መንግሥት አማካይነት የኢኮኖሚ ሕጎችን በመረዳትና በማገናዘብ ፣ የምርት ማኔጅመንት ተግባራቱን ሁሉ ሳይንሳዊ መሠረት ላይ በማስመርኮዝ የምርት ዕድገት አጣቅሚውንም በማዕከላዊና ብሔራዊ ፕላን ላይ በመመሥረት ከምንጊዜውም በተሻለና በበለጠ ሁኔታ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ቁጥጥር ለማድረግና ዕድገቱን እየተቆጣጠረ ለመምራት ይቻለዋል። የተስተካከለ የምርት ማኔጅመንት ማለትም እነዚህ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው።

በሶሻሊዝም ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ዕድገት ሳይንሳዊ የሆነ አመራር መስጠት በሶሻሊስት አብዮት መካሄድ ምክንያት የሚቻል ብቻ መሆን ሳይሆን የግድ አስፈላጊው ነው። ይህም ከሶሻሊስት ኢኮኖሚ ልዩ ባሕርይና ከሶሻሊስት ምርት ዓላማ የሚመነጭ ነው። ሶሻሊስት ምርት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ በራሱ እየተመራ የሚካሄድ ሲሆን ዓላማውም የሶሻሊስት ኅብረተሰብ አባላትን ፍላጐት ማርካትና የተሟላ ደህንነታቸውንና ዕድገታውን ማረጋገጥ ነው። ጥረት የሚደረገውም ይህን ለመቀዳጀት እንዲቻል በመሆኑ ዋንኛው የምርቱ እንቅስቃሴ ትኩረት የምርት ዕድገት ይሆናል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ አንዱ ዋና መንገድ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሶሻሊስት የማኔጅመንት ሥርዓት መመሥረት ነው። በሱም አማካይነት ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የምርት ሁኔታዎችን በቁጥጥር ሥር በማምጣት ፣ ለኢኮኖሚው ዕድገት ተገቢና ሳይንሳዊ የሆነ አመራር ይሰጣል።

የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ሶሻሊዝም በዚህ በኩል ከካፒታሊዝም ይልቅ ያለውን ጥቅምና በሱም ላይ ያለውን የበላይነት አይቀበሉም ፤ የራሳቸው የሆነ መሠረት የሌለው ትርጉምም ይሰጡታል። በተደጋጋሚ ከሚቀርቡት ውግዘቶች ውስጥ አንዱ ሶሻሊስት ማዕከላዊ የምርት ማኔጅመንት (Centralized Production Management) « ቢሮክራሲያዊ» ነው ፤ የማኔጅመንት ተግባር ሲባልም የሚወጡ ፕላኖች በተግባር መተርጐም ወይም በጭፍኑ መመሪያዎችን « መቀበል » ሲሆን የሠራተኛው ተግባር ደግሞ «ትዕዛዝ መፈጸም» ብቻ ነው በማለት የሚቀርበው አስተያየት ነው። ሐቁ

Digitized by Google

ግን ይህ አይደለም ። የግል ይዞታ መኖሩት
የለው በሰው ብዝበዛን አስወግዷል ። ይህም
የብዝበዛ ግንኙነቶችን በጓዳዊ ግንኙነቶች
ተክቷቸዋል ። በመሆኑም የሶሻሊስት ኅብ
ረተሰብ አባላት በጋራ ሥራቸው በጋራ የሚ
ጠቀሙ ናቸው ።

የምርት ግንኙነት በተራው የማኔጅመንት
ባሕርይ የሚወስን በመሆኑ በሶሻሊዝም በጓ
ዳዊ ትብብርና የጋራ መረዳዳት ላይ የተመሠ
ረተው ማኔጅመንት በባሕርዩ በዝባዥ ሊሆን
አይችልም። በቡርዥው ኅብረተሰብ ግን እን
ደምርት ግንኙነቶቹ ሁሉ የማኔጅመንት ግን
ኙነቶችም ተፃራሪ ናቸው ። ማኔጅመንት
/ሥራ አስኪያጁ ፣ በአጠቃላይ የሥራ መሪው
አካል/ እና ሌላው ሠራተኛ በተፃራሪነት የተ
ሰለፉ ናቸው ። ምክንያቱም ማኔጅመንቱን
የሚመሩት ሥራ አስኪያጅ ግለሰቦች የካፒታ
ሊስቶችን መሠረታዊ ጥቅም አስከባሪ ሆነው
የተሰለፉና ብዙኀኑ ሠራተኛ ደግሞ ከዚህ
በተቃራኒ የሚቆም በመሆኑ ነው ። ስለሆ
ነም አመራሩን በሚሰጡትና በሚፈጽሙት
መሀል ተፃራሪ ቅራኔ አለ ። ይህን የሚያስ
ወግደው ሶሻሊዝም ብቻ ነው ።

በሶሻሊዝም የእያንዳንዱ የኅብረተሰብ
አባል ፍላጐትና ዓላማ ከጠቅላላው ከኅብረተ
ሰቡ አባላት ጥቅምና ዓላማ ጋር ይጣጣማል።
ምክንያቱም አባላቱ ማኅበራዊ ፣ ርዕዮተዓለ
ማዊ ፣ ፖለቲካዊ አንድነት አላቸውና ነው ።
በዚህም የተነሣ የወል ወይም የጋራ ግብ ነው
ያላቸው ። ስለሆነም ፓርቲውና በሱም አመ
ራር ሥር የተለያዩ የመንግሥት አካላት ለም
ርት የሚሰጡት አመራርና የሚያደርጉት ቁጥ
ጥር የሠራተኛውን ጥቅም በማራመድ ላይ
ያተኰረ ነው ። የሚሰጡትን አመራርና የሚ
ያደርጉትን ቁጥጥርም የሚያካሂዱት በሶሻሊ
ስት ኅብረተሰብ አባላት ዲሞክራሲያዊ ተሳ
ትፎ ላይ በመመሥረት ነው ። ስለሆነም በማ
ንኛውም ደረጃ በማኔጅመንትና በሠራተኛ
ው መሀል ያለው ክፍፍል የሥራ ክፍፍል
ብቻ ነው ።

ሶሻሊስት ማኔጅመንት በዓላማው ብቻም
ሳይሆን በዘዴዎቹና በተግባሩ ጭምር ከካፒ
ታሊስት ማኔጅመንት የተለየ ነው ። ይህን
ነጥብ ዘርዘር አድርገን እንመልከተው ።

የሶሻሊስት የምርት ማኔጅመንት ዓላማና ተግባራት

በሶሻሊስት ኅብረሰተብ ውስጥ የኢኮኖሚ
ማኔጅመንት ዓላማና ግብ ከራሱ ከሥር
ዓቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕርይ የሚ
መነጭ ሲሆን ከሁሉ በላይ የፓርቲውን
የኢኮኖሚ ፖሊሲ ወደተግባር በመለወጥ
ላይ የሚያተኩር ነው ። በሶሻሊዝም ውስጥ
የሶሻሊስት ምርት አመራር የመንግሥት
ተግባር ነው ። የመንግሥትና የመላ ኅብረ
ተሰቡ መሪ ፣ የፖለቲካ ሥልጣን ማዕከል
ደግሞ ፓርቲው ነው ። ስለሆነም የፓርቲው
የኢኮኖሚ ፖሊሲ በትክክልና ያለማቋረጥ
ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ የመላው መን
ግሥታዊ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሥርዓቱ
ዓይነተኛ ተግባር ይሆናል ።

ከዚህ ሌላ ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ማኔጅመ
ንት የሚያተኩርባቸው ዝርዝር ዓላማዎች
አሉ ። እነዚህም ፣ የኢኮኖሚውን በከፍተኛ
ደረጃና ባለማቋረጥ እየጨመረ በሚሄድ
መጠን ማደጉን ማረጋገጥ፣ የሥራ ምርታማነ
ትንና የምርትን ቅልጥፍና ማሳደግ ፣በተጠና
መንገድ የምርት ወጪን መቀነስ ፣ የሳይን
ስና ቴክኖሎጂ ዕድገትን አቅጣጫና ፍጥነት
በመከተል በምርት ተግባር ውስጥም የዘመ
ናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማስፋፋት የ
ምርትን ደረጃና ጥራቱን መጨመር ፣ በአጠ
ቃላይ ለኢኮኖሚው የተፋጠነ ዕድገት ጠቃ
ሚ የሆኑትን አመቺ ሁኔታዎችን ሁሉ ማመ
ቻቸትንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ። በተ
ጨማሪም በምርቱ ሥራ ሂደት በሠራተኛው
ላይ ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ የተሻለ
ውን የሥራና የምርት ክንውን ወይም በአጠ
ቃላይ የኅብረሰተቡን ኢኮኖሚያዊ ሕይወት
የሠመረ አደረጃጀት ማረጋገጥም የሶሻሊ

Digitized by Google

ሉት ማኔጅመንት ዓላማ የማይነጠል አካል ነው ።

ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ማኔጅመንት አዲሱን ሥርዓት በመገንባትም ሆነ ሥርዓቱን በማጠናከሩ ሂደት ወቅት የሰው ፣ የገንዘብ፣ የማቴሪያል ሀብትን አሰባስቦ በአንድ አቅጣጫ በቁጠባና በብቃት መምራት ላይ ያተኮረ ነው ። ዘወትር የሚያተኩረው በተቻለ ሁሉ የላቀ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና የሥራ አደረጃጀትን በማረጋገጥ ላይ ነው ።

የሶሻሊስት ኢኮኖሚ በመጀመሪያ ደረጃ ቢፓርቲውና በመንግሥት አመራር የሚካሄድ ነው ። ፓርቲው የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴና ዕድገት አቅቂጣጫና ትኩረት በሚነድፈው ፕሮግራም ይተልማል ፤ ለዚህ ፕሮግራም ተግባራዊነት ለመንግሥታዊና ሕዝባዊ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት አካላት በሚሠጠው አመራር መላውን ኢኮኖሚና የምርት ተግባር ሁሉ ያንቀሳቅሳል ። በማዕከላዊና በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት ባለሥልጣን ተቋሞችም የኢኮኖሚ ማኔጅመንትን ተግባራዊ አፈጻጸም ይከታተላሉ ፤ ይመራሉ ።

የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሥራ አንዱ ሌላውን የሚከተሉ የተለያዩ ፣ ነገር ግን ደግሞ የዚያው የአንዱ የኢኮኖሚ አመራር ሥራው ሂደት ውህድ አካላት በመሆናቸው አንዱ ከሌላው ተገንጥለው ሊታዩ የማይችሉ ደረጃዎችን ወይም የማይነጣጠሉ ተግባራትን /ክንዋኔዎችን/ ይይዛል ።

እነዚህ ተግባራት የማኔጅመንት ሥራ የት ጀምሮ ፣ የት እንደሚያበቃና መልሶም እንደገና እንደሚጀምር በሚመለከት ሂደቱን በሙሉ ገጽታው እንድንገነዘበው የሚያስችሉን ሲሆን የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ፍሬ ሐሳብም እነዚህን መሠረታዊ ተግባራት መፈጸም ነው ። የማኅበራዊ ምርት ማኔጅመንት የሚሸፍናቸውን ዋና ዋና ተግባራትን እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል ።

1. የማኅበራዊ ምርቱን ዓላማ ፣ ግብና አቅጣጫ ለይቶ መወሰንና መቀየስ ፣

በማኔጅመንት ውስጥ ዓላማና ግብን መለየት ዓይነተኛ ተግባር ነው ። ምርት በአጠቃላይ ዓላማ ያለው የሰው ልጅ ተግባር ነው። ይህም እስከሆነ ድረስ በማናቸውም የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚካሄድ ምርትን የመምራት ተግባር ሁሉ የሚጀመረው በዚያ በተወሰነ የዕድገት ደረጃና ሁኔታ የምርቱን በአጠቃላይና የተለያዩ ዘርፎችን ዓላማ ግብ በመጣል ነው ።

ለምርት አመራር የመስጠቱ ተግባር የሚጀመረው የምርት እንቅስቃሴ ዓላማን በመወሰንና ለአመራር ስጭም አካል የወቅቱን ተግባራቱን ለይቶ በማስቀመጥ ነው ። ፓርቲው በማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባው ለምሳሌ የኢኮኖሚ ዕድገትን በተመለከተ ውሳኔ ያሳልፋል ። በዚሁ አቅጣጫ የተለያዩት የኢኮኖሚ መሥሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ የኢኮኖሚ አስተዳደር ተቋሞች ሁሉ መመሪያዎችን ፣ ዓዋጆችን ፣ ሰርኩላሮችን ያወጣሉ ፤ ያስተላልፋሉ ። በተመሳሳይ መንገድ እያንዳንዱም ማኔጀር የሚመራውን የማምረቻ ድርጅት ዓላማ በመለየትና ግቡን በመወሰን ሥራውን ይጀምራል ። አንድ ማምረቻ ድርጅት ፣ ለምሳሌ ፤ በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ የምርት ጥራቱን ማሳደግ የወቅቱ ዓይነተኛ የትኩረት ነጥቡ አድርጐ ግቡን ሊወስን ይችላል ። እንዲህ እያለም ይቀጥላል ።

ሌላው በዚህ ረገድ መነሣት ያለበት ጉዳይ በሶሻሊዝም ግቦች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚነደፉ ፣ ተጨባጩን የምርት ሁኔታና በምርቱ ሂደት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ሁሉ በተቻለ መጠን የሚገነዘቡ መሆናቸው ነው ። መፈጸም አለመፈጸማቸው ፣ በምን ዓይነት ብቃት ተግባራዊ እንዲሆኑ ለመቆጣጠር እንዲቻልም

Digitized by Google

ተጨባጭነት ባለው ሁኔታ የሚገመገሙ ናቸው ።

2. ከተወሰኑ ግቦች ላይ ለመድረስ ፣ የምርትን ዓላማ ለማሳካት እንዲቻል የምርት ሂደት ፕላኖችን መንደፍና ማዘጋጀት (planning)

የምርቱን ዓላማና ተግባር ከመለየት ቀጥሎ የሚመጣው የአፈጻጸም ጥያቄ ነው ። በዚህ ጥያቄ ውስጥ በቅድሚያ የኢኮኖሚ ዕድገትን በተመለከተ የተተለመው ጉዳይ ወደ ተግባር እንዲለወጥ ከሚያስችለው ዐቅምና ሁኔታ ጋር መጣመር አለበት። ይህም የሚሆነው በሶሻሊስት ፕላን አማካይነት ነው ። «ማቀድ (planning) በኢኮኖሚ ማኔጅመንት ውስጥ እምብርት የሆነ ጉዳይ ነው ። ምክንያቱም ከኢኮኖሚ ማኔጅመንት አደረጃጀት ጋር የተያያዘ ነውና ነው ። አጠቃላይ የማኔጅመንት ንድፈ ሐሳብ እንደዋነኛው የማኔጅመንት ተግባር አድርጐ በመውሰድ ማቀድን በውስጡ ጨምሮ ይይዛል ።» [14]

ከላይ እንደተጠቀሰው የምርት ማኔጅመንት የምርቱን ሂደት በማስተዋል ማደራጀት ፣ መቆጣጠርና መምራት ማለት ነው። ይህም ሲጠቃለል በምርቱ ሂደት ውስጥ መኖር ያለባቸውን ግንኙነቶች መፍጠር ማለት ነው ። የዚህ ተግባር ዓላማም ከፍተኛ የሥራ ምርታማነትን ማስገኘት ነው ። ስለዚህ የሶሻሊስት የምርት ማኔጅመንት መሠረታዊ ነጥብ የሚሆነው የአገሪቱን የሰው ፣ የገንዘብና የማቴሪያል ሀብት በብቃትና በቁጠባ ተጠቅሞ ለኅብረተሰቡ ከፍተኛ ምርት ፣ ከፍተኛ ጥቅም ማስገኘት ነው ።

የኅብረተሰቡን የሰው ፣ የገንዘብና የማቴሪያል ሀብት በግልጽና በቅድሚያ የታወቀ ዓላማን መሠረት አድርጐ በቁጠባና በብቃት ለመጠቀም ደግሞ ሰፊ ዕድል የሚናረው ምርትንና የኢኮኖሚ ዕድገትን በፕላን ለመምራት ሲቻል ብቻ ነው ። በዚህም ምክንያት ምርትን በፕላን አማካይነት ማደራጀትና መምራት ዋነኛው የማኔጅመንት ተግባር ይሆናል ። ሶሻሊስት ፕላን የፓርቲና የመንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊነት የሚያገኝበት መሣሪያ ነው ። አመጣጥና ዕድገቱም ከሶሻሊስቱ ስልተ ምርት አነሣሥና ዕድገት ጋር የተያያዘ ነው ።

በካፒታሊዝም ዕድገት ሂደት ውስጥ የምርት ኃይሎች በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ ምርትም ማኅበራዊ እየሆነ ቢመጣም ምርትን በማዕከላዊ ፕላን ለመምራትና አንድወጥ የሆነ ማዕከላዊ የማኔጅመንት ሥርዓት ለመዘርጋት ሳይቻል ቀርቷል ። ለዚህም ምክንያቱ የግል የንብረት ይዞታ ሰፍኖ መገኘት ነው ። የግል የንብረት ይዞታ ሲወገድና ሶሻሊስት ስልተምርት መዋቅር ሲጀምር ሁኔታው ሁሉ ይለወጣል ። የኢኮኖሚ ዕድገት በግብታዊ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር ከወደቀበት ሥርዓት ፣ ነባራዊ የኢኮኖሚ ሕጎችን በማስተዋልና በመጠቀም ላይ ወደተመሠረተ የኢኮኖሚ ዕድገት አመራር ሽግግር ይደረጋል ። ምክንያቱም በሶሻሊስት የንብረት ይዞታ በመመሥረቱ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታ ተፈጥሯልና ነው ።

እላይ እንደተጠቀሰው የሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ዕድገት ዓላማ የመላ ኅብረተሰቡንና የእያንዳንዱን አባል ፍላጐትና የተሟላ ዕድገት ማረጋገጥ ነው ። የሥርዓቱ የምርት አደረጃጀትም ይህንኑ የሚፈቅድ በመሆኑ ሠራተኛው ሕዝብ ፍላጐቱን ካለው ዐቅም (የገንዘብ ፣ የማቴሪያል ፣ የሰው ኃይል)ጋር በማነፃፀር የሚመራበት አደረጃጀት የግድ ያስፈልገዋል ። በአጭሩ በአንድ ማዕከልና በሠራተኛው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ በሚነድፍ ማዕከላዊ ፕላን የሚመራ መሆን አለበት ማለት ነው ። ሶሻሊስቱ መንግሥትም ፕላን የማውጣትንና ክትትል የማድረግን ተግባርን እንደዋነኛው ኢኮኖሚያዊ ተግባሩ ይቆጥረዋል ።

Digitized by Google

3. ፕላኖች ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ምርትን ማደራጀት ፤

ይህ አደረጃጀት ከሁለት አቅጣጫ ሊታይ ይችላል ። አንደኛው ፤ የኢኮኖሚውን ወይም የሚመለከተውን የማምረቻ ተቋም መዋቅር (Struoture) መዘርጋትንና የኃላፊነት ተዋረድንና የሥራ ድርሻ ክልሎችን እያደዘ መወሰንን የሚመለከት ነው ። በኢኮኖሚው ወይም በአጠቃላይ በማኅበራዊ ምርቱ ሂደት ውስጥ የተወሰነ ግብ ወይም የተነደፈ ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን ቅይድመ ሁኔታው መደላደል አለበት ። ይህም በቀላል አባባል ዕቅዱን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የሥራ ክፍፍል ማድረግ ፤ የኃላፊነት ወሰኖችን መከለል ወይም ደግሞ የማኔጅመንት መዋቅርን መዘርጋት ማለት ነው ።

ሁለተኛው ደግሞ የአመራር ሰጪ አካልም (Subject of Management) ሆነ የአመራር ተቀባይ አካል (Objct of Management) እንቅስቃሴ በተወሰነው ግብ ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ማስተባበርን የሚመለከት ነው ።

የኢኮኖሚ አመራር ሰጪውን አካልና አመራር ተቀባዩን እንዲሁም በመሃላቸው የሚኖረውን ግንኙነት አንድ የተወሰነ ሥርዓት ማስያዝና ማቀናጀት አስፈላጊ ነው ። በሥርዓት የተደራጀውን የምርት ሂደትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከመፋለስ መጠበቅ ፣ የተደራጀና የተቀናጀ አካሄዱን ማጠናከርና ተገቢ ማሻሻያዎችን እያደረጉ ሂደቱን ፈር አስይዞ መምራት ቸል ሊባል የማይገባው ጉዳይ ነው ። በምርት ሂደትና በአመራሩም ውስጥ አንዴ የተደራጀና የተቀናጀ ስለሆነ እንዳለ ይዘልቃል ማለት አይቻልም ። በውስጥ ወይም በውጭ ወይም በሁለቱ ላይ ለውጥ ይፈጠራል ፤ ምርቱ በምን ሁኔታ ውስጥ እንደሚካሄድ ለመገምገም ቀደም ሲል በተደረገ ሙከራ ላይ እክል ሊኖር ይችላል፡ከግንዛቤ ያልገባ ነገር ያጋጥማል ፣ ወዘተ. . . ። እነዚህ ሁሉ በማኔጅመንቱ ሥርዓት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ ። ስለዚህ የሁኔታዎችን ለውጥ በመከተል ተገቢውን መሻሻልና ለውጥ በማድረግ የሥርዓቱን መልክ የያዘ ቅንጅት መጠበቅ አስፈላጊ ነው ።

4. መከታተልና መቆጣጠር ፤

በዚህ መስክ ውስጥ ሁለት ዓይነተኛ ተግራት አሉ ። የመጀመሪያው የታቀዱ ተግባራትና የተላለፉ ውሳኔዎች መፈጸማቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችለውን የማረጋገጫ ሥርዓት የመዘርጋት ተግባር ነው ።

ቀደም ሲል እንደገለጽነው በኢኮኖሚ ማኔጅመንት ተግባር ውስጥ የመጀመሪያው ሥራ ግብ መወሰን ፤ ዓላማን ግልጽ ማድረግ ነው ። በተከታታይ የሚፈጸሙት ተግባራት ሁሉም በዚህ በተወሰነው ግብ ላይ ያተኩሩ ይሆናሉ ። እነዚህ ዓላማዎች በሶሻሊዝም ተግባራዊ የሚሆንባቸው ዘዴዎች ኢኮኖሚያዊና ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ዘዴዎችን ያጠቃልላሉ ። የትርፍና ኪሣራ ስሌት (Cost Accounting) ዋነኛውን ቦታ የሚይዘው ዘዴ ነው ። ይህ ዘዴ የታቀደ የኢኮኖሚ ዕድገት እውን በሆነበት ሁኔታ ውስጥ የዋጋ ሕግን መሠረት በማድረግ የኢኮንሚ ማኔጅመንትን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ለኢኮኖሚው አመራር ለመስጠት ያስችላል ።

በሶሻሊዝም የተወሰነ ተግባር ፤ ኃላፊነትና ግብ ያላቸው ራሳቸውን የቻሉ በርካታ የማምረቻ ተቋሞች ይገኛሉ ። እያንዳንዱ ተቋም ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ የሚሆኑ የተወሰኑ የምርት ውጤቶችን እንዲያመርት በመንግሥት ኃላፊነት የተጣለበትና ለዚህም ተግባር በመንግሥት የተደራጀ በመሆኑ የተወሰኑና የታወቁ ፍላጎቶች አሉት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝባዊው ሀብት አካል እንደመሆናቸው ዓላማና ግባቸው ከመላው የኅብረተሰቡ ዓላማ ፣ ግብና ፍላጎት ጋር የተስማማ ነው ።

Digitized by Google

የሶሻሊስት የማምረቻ ተቋሞች የምርት እንቅስቃሴ በማዕከላዊ አመራር (centralized direction) ሥር የሚካሄድ ነው ሲባል በመሠረቱ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያመለክተው በማዕከላዊው ዕቅድ መሠረት የሚካሄድና መካሄድም ያለበት መሆኑን ነው ። የኅብረተሰቡን ፍላጐቶች መሠረት በማድረግና ካለውም ዐቅም ጋር በማነፃፀር የኢኮኖሚ ፕላኑ ተገቢዎቹን የኢኮኖሚ መጠን ግንኙነቶች (economic proportions) ይወስናል።ከዚህም በላይ አጠቃላይ አመልካች ገቦች (control figures) ተዘርዝረው ለእያንዳንዱ የማምረቻ ተቋም ገብ (quota) ይሰጣል ። የማምረቻ ተቋሞችም ገቡን ተከትለውና ከገቡ ጋር የሚሄዱ ግዴታዎችን ጠብቀው የማምረት ግዴታ አለባቸው ።

በሌላ በኩል በዕቅዱ በተወሰነው መሠረት የማምረቻ ተቋሞቹ እንዲያመርቱ የሚያስችላቸውን የምርት መከናወኛዎች ከመንግሥት ያገኛሉ ። በነዚህ በአገባቡና በብቃት ለመጠቀማቸውም በመንግሥት ተጠያቂዎች ናቸው ።

የማምረቻ ተቋሞች አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነት የሚጐናጸፉ መሆናቸው በሶሻሊዝም ዋነኛው የኮስት አካውንቲንግ መርሕ ነው ። በዚህ መርሕ መሠረት የማምረቻ ተቋሞች በይዞታቸው ሥር በሚገኙ ቋሚና ተዘዋዋሪ ንብረቶች በሙሉ ይበጃል በሚሉት መንገድ የመጠቀም ነፃነት አላቸው ። ምርትን ቀናና የበለጠ ነው በሚሉት መንገድ ሊያደራጁ ይችላሉ ። ተቋሞቹ የሕግ ሰውነት ይኖራቸዋል ፤ በፍርድ ራሳቸውን ችለው ሊጠይቁ ወይም ሊከሰሱ ይችላሉ ።

የምርት ተግባራቸውን በራሳቸው የማደራጀት መብት የተሰጣቸው በመሆኑ ራሳቸውን ችለው ሠራተኞች ይቀጥራሉ ፤ ለምርት የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ይገዛሉ ፤ የምርት ውጤታቸውን ይሸጣሉ ። ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውም በመሆኑ ከባንክ የመበደር ፣ ወይም ለወቅቱ የማይገለገሉበትን ገቢ በባንክ የማስቀመጥና እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋር የኮንትራት ውል የመግባት ነፃነት አላቸው ። ስለሆነም በሶሻሊዝም የማምረቻ ተቋሞች ምርትን በማደራጀትም ሆነ በመምራት ረገድ ሰፊ የሆነ ነፃነት አላቸው ።

ይሁንና ሁሉም ተቋሞች በየራሳቸው ፍላጐት ብቻ የሚራመዱና እንደፈቀዳቸውም የሚሄዱ እንዳልሆነ መዘንጋት የለበትም። ነፃነታቸው አንፃራዊ ነው ። አንፃራዊነቱም ከላይ እንደተወሳው ብሔራዊ ፕላኑን በሚመለከት ረገድ ነው ። የምርት አደረጃጀቱንና አካሄዱን በመወሰን ፣ ከሌሎች የማምረቻ ተቋሞች ጋርም በሚያደርጉት የኢኮኖሚ ኮንትራት ውል ረገድ እንደአንድ የሕግ ሰው ነፃ ሆነው የሚፈጽሙት ቢሆንም የሁለቱም ተግባሮቻቸው መሠረት ብሔራዊ ፕላኑ ይሆን ዘንድ የግድ ነው ። ነፃ ድርጊቶቻቸው ከማዕከላዊ ቁጥጥሩና አመራሩ ጋር ተጣጥመው መሄድ አለባቸው ። እጅግ የበዛና ዝርዝር የሆነ ማዕከላዊ ቁጥጥር ፍላጐትንና የፈጠራ ተሰጥኦን ሊቀንስ ይችላል ። ያለልክ የሰፋ የማምረቻ ተቋሞች የአፈጻጸም ነፃነት ደግሞ ዕቅዱን በማፋለስ ለጠቅላላው የምርት ሂደት የማይፈልግ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል ።

ከዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ የማምረቻ ተቋሞች የአፈጻጸም ነፃነት ወይም የሕግ ሰውነት ያላቸው መሆናቸው ጠቀሜታው (ፋይዳው) ከምን ላይ ነው ? የሚለው ነው። ይህን ማብራራት አስፈላጊ ነው ።

ሶሻሊስት የማምረቻ ተቋሞች ራሳቸውን የቻሉ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ቢሆኑም በአንድ በኩል ከመንግሥት ያገኟቸውን ንብረቶች በተሟላ ፣ በቀለጠፈና በቁጠባ በምርት ተግባር ላይ ስለማዋላቸውና በፕላኑም መሠረት ለመሥራታቸው ለመንግሥት ተጠያቂዎች ናቸው ። በሌላም በኩል እነዚህ

Digitized by Google

ተቋሞች የሕግ ሰውነት ያላቸው በመሆኑ ደግሞ ከሌሎች ተቋሞች ጋር በምርት ልውውጥና በመሳሰሉት ውል መግባት ይችላሉ። ውሉ አንዱ ለሌላው ግዴታ የሚገቡበት በመሆኑ የምርቱን ውጤት ዓይነት ፥ ብዛት፥ መጠን ፥ ጥራት ፥ ዋጋ ፥ የማስረከቢያ ቀን፥ የክፍያ መጠን ፥ የአከፋፈል ሁኔታ ፥ ወዘተ . . . የመሳሰሉት ሁኔታዎችን በተመለከተ በሚነሡ ጉዳዮች ሁሉ ሕጋዊ ግዴታ አለባቸው ። ይህ ባይከበር አጥፊው ይከሰሳል። ቅጣትም ይበየንበታል ። ውል ተቀባይ ለውል ሰጭው በገባው ግዴታ በሕግ ተጠያቂ ነውና ። የበላይ አካሉ ለበታቹ ፥ የበታቹም ለበላዩ የማምረቻ ተቋሙ ዕዳ ተጠያቂ አይደለም ።

በውሉ መሠረት ግዴታውን ባላከበረ ተቋም ላይ የሚጣለው ቅጣት የምርት ወጭውን ያንረዋል ። ይህ ደግሞ የተቋሙን ትርፍ የሚቀንስ ፥ ገቢውን የሚያዳክም ይሆናል ። ስለዚህ ተቋሞች የገቡትን ግዴታ መወጣት ዘወትር ፍላጐታቸው ይሆናል ። ለምሳሌ ዳቦ አቅራቢው ፋብሪካ ውሉን ባለመጠበቅ ፥ በተወሰነው ብዛት ባለማቅረቡ ሲጠየቅ በቂ ዱቄት ባለመቅረቡ እንደሆነ ሲያመካኝ ፥ ዱቄት አቅራቢው ሲጠየቅ በስንዴ እጥረት እንደሆነ ሲያሳብብ ፥ ስንዴ ማቅረብ ያለበት እርሻ በጀንያ አቅራቢዎች ደካማነት ሲያመካኝ በመሐሉ የሚባክን የአገር ሀብት እንዳይኖር ተጨባጭ የሆነ መከላከያ ተዘርግቷል ማለት ነው ።

ሶሻሊስት የምርት ተቋሞች ለመንግሥትና ለአምሳያ ተቋሞች የገቡትን ግዴታ ባለማክበራቸው ምክንያት የሚደርሰባቸውን ቅጣት ለመሸሽ ሲጥሩ ነው የሚያደጉት ፥ የሚዳብሩትም ማለትም አይደለም ። በመሠረቱ ሶሻሊስት የማምረቻ ተቋሞች በምርታቸው ዕድገት ተጠቃሚዎች ናቸው ። የምርት ወጪአቸውን ከገቢአቸው ማገናዘብ አለባቸው ። የምርት ውጤቶቻቸውን ሸጠው የሚያገኙት ገቢም ወጪአቸውን የሚሸፍን ብቻ ሳይሆን ትርፍም ማስገኘት አለበት ።

ትርፋማነታቸው በመሠረቱ የምርት ብቃታቸውና ቅልጥፍናቸው መለኪያ ነው ። በተደጋጋሚ ቢከስሩ ህልውናቸው ከኢኮኖሚጥቅም አኳያ ትርጉም ያጣል ። ወጪአቸውን ብቻ እየሸፈኑ መንገዳገድ ቢደጋግማቸውም ምርትን ለማስፋፋት ፥ ለማሻሻል ፥ሠራተኛውን በቁሳዊ ማበረታቻዎች ለማነቃቃት ወዘተ ... አቅም ስለማይኖራቸው የሚፈቅዱት ሁኔታ አይሆንም ። የተቋሙ ትርፍ ያደገ እንደሆነ ግን ምርትን ለማስፋፋትና ለማሻሻል ፥ ለሠራተኞች የሥራ ማነቃቂያና ሌሎችንም ማኅበራዊ ጥቅሞች ለመስጠት የሚችል ይሆናል ።

የምርት ተቋሙ የጠቅላላው የኅብረተሰቡ ሀብት አካል እንደመሆኑ ትርፋማነቱ በአጠቃላይ ለኅብረተሰቡ የሚጠቅም ነው ። ትርፋማ በመሆኑ ተቋሙ ሌሎች ግዴታዎችን ሁሉ /ለመንግሥትና ለ ሌላ ውል ሰጪዎች/ ተወጥቶ ተራፊ ገንዘብ ስለሚኖረው እንደገና ተቋሙም ሆነ በውስጡ የሚሠሩት ሠራተኞች ይጠቀማሉ ። የኅብረተሰቡ በአጠቃላይ የፋብሪካውና የፋብሪካው ሠራተኛ ፍላጐቶች በተሳሰረና በተጣጣመ ሁኔታ ይሟላሉ። ስለሆነም ቁሳዊ ማበረታቻ በሚያገኙበ መልክ ሶሻሊስት ተቋሞች መደራጀታቸው ዓይነተኛ ጉዳይ ነው ።

ይሁንና ቁሳዊ ማበረታቻ ከሞራል ማበረታቻ ጋር ካልተጣመረና ካልተቀናጀ ውጤቱ የተሟላ አይሆንም ። በገንዘብ ወይም በዓይነት ፥ በነጠላም ሆነ በወል ከሚሰጡ ማበረታቻዎች በተጨማሪ ብልጫ ላሳዩ ሠራተኞች የምሥጋና ደብዳቤዎችና የማረጋገጫ ሠርተፊኬቶችን ፥ ኒሻንና ሜዳሊያዎችን በመስጠት ፥ ወዘተ... የሞራል ማበረታቻ ማድረግ ተገቢ ነው ።

ሌላው ፥ የማምረቻ ተቋሞች በአንድ በኩል በማዕከላዊነት ቁጥጥር የሚደረግባቸውና በሌላ በኩል ደግሞ ራሳቸውን በራሳቸው ገቢ ደግፈው የሚተዳደሩ ነፃ ተቋሞች መሆናቸው የሚገለጽበት ሁኔታ የሚከሰተው

Digitized by Google

በሶሻሊስት የማምረቻ ተቋሞች ላይ በሚደረገው የገንዘብ ቁጥጥር ነው ።

ሶሻሊስት የምርት ተቋሞች የአፈጻጸም ነፃነታትና ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለሆኑ ከባንክ የመበደር መብት አላቸው ። ነገር ግን በሌላ በኩል ደግሞ ብድርን መንግሥት የማምረቻ ተቋሞችን ለመቆጣጠር ይጠቀምበታል ። በሶሻሊዝም ባንኮች በመንግሥት ይዞታ ሥር ናቸው ። ፓርቲውና መንግሥትም የማምረቻ ተቋሞች በፕላኑ መሠረትና በአጥጋቢ ሁኔታ የምርት እንቅስቃሴያቸውን እንዲያካሂዱ ባንኮቹ በሚነድፉት የብድር ፖሊሲ አማካይነት ተጽዕኖ ያደርጋሉ ። ባንኮች ብድር ሲሰጡ የተፈቀደውን ገንዘብ ለማምረቻ ተቋም ፍላጐትና ለተጠየቀለት ተግባር መዋሉን ይቆጣጠራሉ። በማምረቻ ተቋሞች መሃል የሚካሄደውን የንግድ ግንኙነት ሲያስፈጽሙ የፕላን ግባቸውን የሚመቱ ፣ ዕድገት የሚያሳዩ የማምረቻ ተቋሞች ተስማሚ በሆነ ሁኔታ ብድር እንዲያገኙ ይደረጋል ፤ ሌላው ቀርቶ አስቀድሞ ላልታሰቡና ተመሳሳይ ድንገተኛ ወጪዎች ጭምር ብድር እየተፈቀደላቸው ይታገዛሉ። ድክመት በሚያሳዩት ላይ ደግሞ ጠበቅ ያለ ክትትል ይደረጋል ። እየባሰባቸው የሚሄድ ከሆነም ብድር ሊከለከሉ ይችላሉ ። በሚመለከታቸው አካላት በኩል ሁኔታውን ለመለወጥና ለማሻሻል ተገቢ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ። ሁሉም ካልተሳካ ግን ባንኩ በብድር ያወጣውን ወጪ በሚያስመልስበት መንገድ ላይ ይወሰናል ።

በሌላ በኩል የማምረቻ ተቋሞች በየጊዜው የምርት ወጪአቸው እየናረ ከሄደ ምርታቸውን ማስፋፋትና ሠራተኞቻቸውን ማንቃቃት ቀርቶ ገቢአቸው ስለሚቀንስ ከባንኮች የተበደሩትን መክፈል ፣ ወይም ለገዙት ዕቃ ክፍያ ለመፈጸም ፣ ወዘተ ...የሚሳናቸው እንደሚሆን አያጠራጥርም ። ይህን አስከፊ ሁኔታ ስለማይሹት ዘወትር የፕላን ግባቸውን ለመምታት ፣ ምርታማነታቸውን ለማሳደግና ገቢአቸውን ለማዳበር ጥረት ያደርጋሉ። ድርጊቱም ለመላው ኅብረተሰብ ጭምር የሚበጅና የሚፈለግም ነው ።

የሶሻሊስ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ዋና ዋና መርሆዎች

የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ዋና ዋና ተግባራት ከላይ ተጠቁመዋል ። የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሲባልም በመሠረቱ እነዚህን መሠረታዊ ተግባራት ማከናወን ማለት እንደሆነ ተመልክቷል ።

ይሁንና እነዚህ ተግባራት ሊከናወኑ የሚችሉበት ሁኔታ ሊለያይ ስለሚችል ምን ያህል በብቃት መከናወን ወይም አለመከናወናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ። በመሠረቱ የሶሻሊስት የምርት ማኔጅመንት ተግባር በሙሉ ብቃት ሊከናወን የሚችለው ተገቢ የሆኑ ዘዴዎችን በመጠቀም የሶሻሊስት ምርት ማኔጅመንት መርሆዎችን ተከትሎና ጠብቆ መሄድ ሲቻል ብቻ ነው ። ምንም እንኳ የምርት ማኔጅመንት እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩ የአደረጃጀት ቅርጾች ሊኖሩት እንደሚችል የሚታወቅ ቢሆንም ሁሉም የሚመሠረቱት በተመሳሳይ መርሆዎች ላይ ነው ። ከእነዚህ ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

1. ነባራዊና ተጨባጭ ፤

የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ነባራዊ ነው።ይህም ማለት ነባራዊ የኢኮኖሚ ሕጎችን መረዳትንና በኢኮኖሚ ማኔጅመንት ክንውን ውስጥ መጠቀምን ይመለከታል። በመሠረቱ የማኔጅመንት ተግባር ተገቢ ዓላማውን መምታት አለመምታቱ ወይም ዓላማውን የሚመታበት ደረጃ የኢኮኖሚ ሕጎችን ለመረዳትና ለማወቅ ፣ ተረድቶና ዐውቆም በኢኮኖሚ ማኔጅመንት ተግባር ውስጥ ለመጠቀም በተቻለበት ደረጃ የሚወሰን ነው ። ማለትም የኢኮኖሚ ሕጎችን በትክክል ለመረዳት ባልተቻለበት ሁኔታ እነዚህን የኢኮኖሚ ሕጎች መጠቀም አይቻልም። የኢኮኖሚ ሕጎችን መጠቀም ባል

Digitized by Google

ተቻለበት ሁኔታ ደግሞ ብቁ የሆነ የማኔጅመንት ሥራ ተሠራ ለማለት አይቻልም ። በአንፃሩ እነዚህን ሕጎች ጠንቅቆ መረዳትና ማወቅ ሲቻል ግን የሚወሰዱ ውሳኔዎች ሁሉ በበለጠ ነባራዊው ማኅበራዊ ዕድገት ከሚጠይቀው እርምጃ ጋር የሚስማሙ ይሆናሉ ። ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ ከእውነት የራቁ ፣ የግለሰቦችን ወይም የቡድኖችን ፍላጐት ብቻ የሚያንፀባርቁ ተስፈንጣሪ ወይም ኋላቀር ውሳኔዎች አይሆኑም ማለት ነው ።

በመሠረቱ የኢኮኖሚ ሕጎችን በትክክል በመገንዘብ ወይም በነባራዊ ባሕርይ ተመርሥቶ የሚካሄድ ማኔጅመንት የኢኮኖሚውን ዕድገት የሚያመለክቱ በአጠቃላይ ተግባራትንና ግቦችን የሚያሳይ ነው ። ይሁን እንጂ የአንድን ብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚመለከቱ አጠቃላይ አሠራሮችንና ግቦችን ማሳየት ብቻ በራሱ የኢኮኖሚውን ማኔጅመንት ሳይንሳዊ አያደርገውም። ሕጎች በየኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃዎች ፣ አካባቢዎች ፣ ወቅቶች በአጭሩ እንደየተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆኑበት አሠራር ግልጽ መሆን አለበት ። በሌላ አነጋገር የኢኮኖሚው ማኔጅመንት የኢኮኖሚውን ሕግ ከዝርዝር ሁኔታዎችና መረጃዎች ጋር አገናዝቦ የሚካሄድ መሆን አለበት ። የዚህ መርህ ተግባራዊ መሆን የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ማኔጅመንትን ተጨባጭነት የሚገልጽ ነው ።

ተጨባጭ ማኔጅመንት በብሔራዊ ደረጃ ለሚደረገው የሥራ አመራር ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ የማምረቻ ተቋም ከሚገኝ ከማንኛውም የምርት ሥራ መሪ የሚጠበቅ ነው። የሚመራውን ዘርፍ ወይም ድርጅት አሠራር፣ የሥራ ሁኔታ ፣ የዕድገት አቅጣጫ በሚገባ ማወቅ አለበት ። በየጊዜው ችግሮች ሲነሡ ብቻ የሚሯሯጥ፣ጊዜያዊ ለሆኑ አጋጣሚዎች ተገዥ በመሆን የሩቅን ዕቅድ የሚዘነጋ ፣ ከዕውነታ የማይጣጣሙ ውሳኔዎች የሚሰጥ መሆን የለበትም ። ለዚህም ነው ሌኒን «ማኔጅመንት ብቃትን ፣ እስከመጨረሻው ዝርዝር ተግባር ድረስ ስለምርት ሁኔታዎች ሁሉና ስላለህበት የምርት ዘርፍ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ዕውቀት እንዲኖርህ ማስፈለጉን ያመለክታል ፤ የተወሰነ ሳይንሳዊ ዕውቀት ሊኖረን ይገባል» [15] ሲል የገለጸው ።

2. የተቀላጠፈ አሠራርና ውጤታማነት *

የተቀላጠፈ አሠራርና ውጤታማነት (optimality, efficiency) መርህ በቁጥጥር ሥር ያለን ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብትን ያለብክነት በመጠቀም ለሚያጋጥሙ ችግሮች እልባት መስጠትንና መሰል ተግባራትን ያጠቃልላል ። በኢኮኖሚ ማኔጅመንት ውስጥ ቆጣቢ መሆንና እያንዳንዱን የንብረት ዓይነት በታቀደው መሠረት በጥቅም ላይ በማዋል በአጠቃላይ በምርት ሂደትም ሆነ በፍጆታ ብክነትን ማስወገድ አስፈላጊ ነው ።

3. ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሶሻሊስት ማኔጅመንት መሠረታዊ መርህ ነው ። ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በዚህ አግባቡ የምርት ተግባር ማዕከላዊ አመራርና በምርት ተግባር ውስጥ የበታች የምርት ሕዋሶችና አካሎች እንዲሁም የእያንዳንዱ ሠራተኛ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ቅንጅትን የሚያመለክት ነው ።

የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ከሁሉ በላይ የግል ይዞታ የተወገደበት እንደመሆኑ መጠን ከፍተኛ መሰባሰብና ማኅበራዊነት የሚታይበት ነው ። እንደቡርዧ ኢኮኖሚ የግለኛ ሸቀጥ አምራች ድርጅቶች ድምር ሳይሆን እርስ በርሳቸው የተያያዙና የተሳሰሩ ድርጅቶችን የሚያቅፍ የተደራጀና በብሔራዊ ደረጃ የሚካሄድ ምርት ነው።በዚህም ምክንያት ጭፍን

ይህ መርህ ከዚህ በላይ ስለክትትልና መቆጣጠር ተግባራት ውስጥ በሰፊው የተገለጸ ስለሆነ እንደገና በዝርዝር አናየውም ።

Digitized by Google

በሆኑ የገበያ ግንኙነቶች አማካይነት የሚንቀሳቀስ ሳይሆን እንደ አንድ አካል በአንድ ማዕከላዊ ፕላን የሚመራ ሲሆን ከሚገባው በላይ የምርት ዘርፎች ሁሉ እንቅስቃሴና ምርት ተግባር ሂደትም በማዕከላዊነት መደራጀት ያሻዋል ። ማለትም የምርት ማከናኛዎችና የሥራ ማኅበራዊ ባህርይ እየያዘ መምጣት ታሪካዊ ሂደት በአንድ ማዕከላዊ ፕላን የሚመራ የወል ይዞታ እንዲመሠረት የሚጠይቅ ሲሆን ፣ ይኸው ሂደት ራሱ ማኔጅመንትም ከአንድ ማዕከል እንዲካሄድ የሚያስፈልገበትን ሁኔታ ይፈጥራል ። በሶሻሊስት ምርት ውስጥ ማዕከላዊነት በየማምረቻ ተቋሞም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ አካላት ሁሉ ለአንድ ዓላማና ግብ የሚሠሩ መሆናቸው ማረጋገጫ ነው ። ስለዚህ ማዕከላዊነት የሶሻስት ማኔጅመንት መሠረታዊ መርህ አንዱ ዋና ገጽታ ነው ።

ይሁንና ይህ ማዕከላዊ አሠራር በሶሻሊዝም ዲሞክራሲያዊ አሠራር /ተሳትፎ/ ላይ መመሥረት አለበት ። ስለሆነም የሶሻሊስት ምርት ማዕከላዊ የሥራ አመራር እያገኘ በሶሻሊስት ሠራተኞችና የማምረቻ ድርጅቶች ሰፊ ተሳትፎ ላይ ተመሥርቶ የሚካሄድ ነው። የዲሞክራሲ ማበብም ሰፊውን ሠራተኛ ሕዝብ በሶሻሊስት ምርት ማኔጅመንት ተግባር ውስጥ ለማሳተፍ ካለው ነባራዊ ግዴታ የሚመነጭ የሶሻሊዝምን ይዘትና ፍቺ የሚያገፀባርቅ ነው ።

ምርትን በመቆጣጠር ረገድ የሠራተኛው ተሳትፎ—የሶቭዬት ኅብረት ልምድ

በሶቭዬት ኅብረት ጠቅላላው የምርት ማኔጅመንት የሚከናወነው ማዕከላዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ነው።በውይይት ወቅት ዲሞክራሲ የበላይነቱን ሲይዝ ከውይይቱ በኋላ የሚተላለፈውን ውሳኔ በተግባር በመተርጐም ላይ ማዕከላዊነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።ማለትም በፕላን ንድፎች ወይንም በሌሎች ጉዳዮች ላይ ውይይት በሚደረገበት ወቅት እያንዳንዱ ሠራተኛ ወይም ሕዝቡ በአጠቃላይ በውይይቱ መሳተፍ መብቱ ከመሆኑም በላይ ግዴታውም ጭምር ነው ። ነገር ግን አንድ ጊዜ ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ይህን የማስፈጸም ኃላፊነት በማምረቻ ደረጃ የአንድ ሰው ብቻ ፣ በአገር አቀፍ ደረጃም ከሆነ የሚመለከተው የበላይ አካል ብቻ ነው ። ምክንያቱም ውይይቱ በማስፈጸሙ ተግባር ላይ ሁሉ ይቀጥል ቢባል ውጤቱ በዕቅድ መሠረት ሥራን ማከናወን ሳይሆን ምስቅልቅል ስለሚሆን ነው ።

ሠራተኛውን በምርት ሥራ አመራር ውስጥ በማሳተፍ ሶቭዬት ኅብረት ሰፊ ልምድ አላት ፤ ይህም የተጀመረው ፣ የጥቅምቱ አብዮት እንደፈነዳ ነበር ፤ የግል ድርጅቶች ገና በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከመምጣታቸው በፊት በእያንዳንዱ የማምረቻ ተቋም የሠራተኛ የቁጥጥር ኮሚቴዎች ተቋቁመው ለመንግሥት ሊገባ የሚገባውን ገቢ ያስቀሩትን ፣ የማምረቻ ተቋሞችን የምርት እንቅስቃሴ በማቀዝቀዝ ፣ ጥሬ ዕቃ በመደበቅ ፣ የተፈላጊ ሸቀጦች እጥረት ሆን ብለው በማስከተል ፣ ከሰርን በማለት ድርጅታቸውን በመዝጋትና ሥራ አጥነት እንዲስፋፉ ያደረጉትን ፣ የሠራተኛውን ደመወዝ በማዘግየትና ጭራሹንም በመከልከል ፣ ጨቅላውን መንግሥት ውጥረት ላይ ለመጣልና ለማንበርከክ ይጥሩ የነበሩትን ቡርዧዎችና የወደቀው ሥርዓት ወኪሎች አሻጥር አጋልጠዋል ፤ ተዋግተዋል ። የመነሻ የምርት ክታዎችን በመወሰን ፣ የጥሬ ዕቃዎችንና የምርት ውጤቶችን ክምችትንና ክፍፍልን ፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ሠራተኞች ሥራን ፣ የድርጅት፣የፋይናንስና በአጠቃላይ የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጉዳዮችን በመከታተልና በመቆጣጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አስመዝግበዋል ። የኮሚቴውን ሥራ ለማደናቀፍ ከበዝባዦች የሚተበተበውን ሤራ ሁሉ በማከሸፍና በአንድ በኩል ካፒታሊስቶችን ለአዲሱ ሕዝባዊ ሥልጣን / ለሶሻሊስቱ መንግሥት/ ቁጥጥር ተገዥ እንዲሆኑ በማድረግ፣

Digitized by Google

በሌላ በኩል ደግሞ ዋና ዋና የማምረቻ ተቋሞችን ወደሕዝብ ለማዛወር የሚቻልበትን በማመቻቸት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ዋና ዋና የማምረቻ ተቋሞች ወደሕዝብ ይዞታነት ከተዛወሩም በኋላ ከዚሁ ከመውረሱ ተግባር በኋላ የፊውዳሉችንና የካፒታሊስቶችን ማኔጅመንት በአዲስ በሠርቶ አደሩ በሚካሄድ ማኔጅመንት መተካቱ ወሳኝ በመሆኑ ትኩረቱ በዚሁ ላይ ሆኗል። ምክንያቱም ዕድገት እንዲኖር ከተፈለገ አሮጌውን ከማፍረሱ ጋር የአዲሱን ግንባታ አብሮ ማካሄድ ግዴታ ነበር ። የአብዮቱን ድሎች ለመጠበቅ አዲስን ብሔራዊ ኢኮኖሚን መገንባት፣ምርትን በአዲስ መልክ ማደራጀትና ማኔጅመንትንም በአዲስ መልክ መዘርጋት ያስፈልጋል ማለት ነው ። ይህም በመደረጉ ሠራተኛው ምርትን ለመቆጣጠር ያደረገው ትግል ለፍሬ በቅቷል ።

በሶቭዬት ኅብረት ሠራተኛው በየማምረቻ ተቋሞች በሚገኙ የሕዝባዊ ቁጥጥር ኮሚቴዎች ፣ በወጣቱ ኮሚኒስት ማኅበር መሠረታዊ ማኅበራት ፣ በሙያ ማኅበራትና በፓርቲ መሠረታዊ ድርጅቶች አማካይነት በማኔጅመንት ሥራ ይካፈላል ፤ ምርትንም ይቆጣጠራል ።

በየማምረቻ ተቋሙ የሚገኙት የአዳዲስና የተሻሉ ዘዴዎች ፣ መሣሪያዎች ፣ ወዘተ ፈጣሪዎች ፣ የነዳፊዎች ፣ የሞድ አውጭዎች ፣ ወዘተ . . . ቡድኖች ሁሉ ለተጠቀሰው ተግባር ራሳቸውን የቻሉ መድረኮች ናቸው ።

ከእነዚህ በተጨማሪ በሶቭዬቶች (ሕዝባዊ ውክልና ባላቸው የአስተዳደር አካላት) አማካይነትም ሠራተኛው ሕዝብ ምርትን ይቆጣጠራል ። ለምሳሌ በአንድ አካባቢ የሚገኝ ሶቭዬት የአካባቢውን ሠራተኛና ገበሬ በአባልነት የሚይዝ ሲሆን ፣ በየሪፐብሊኩ የሚገኙ የማምረቻ ተቋሞች ሁሉ በአብዛኛው ተጠሪነታቸው በዚያው ሪፐብሊክ ለሚገኝ ለሚመለከተው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ይሆንና ይህም ዘርፍ ደግሞ በመጨረሻው በዚያው ሪፐብሊክ ሶቭዬት ሥር ስለሚሆን የሶቭዬቶች አባል የሆኑት ሠራተኞችና ገበሬዎች በበላይነት የሚመሩት ይሆናል። ይህ በሪፐብሊኩ ደረጃ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በብሔራዊ ደረጃም የሚፈጸም ነው ። የበላይ ከፍተኛው ሶቭዬትም እንዲሁ በአብዛኛው ሠራተኛውንና ገበሬውን የሚይዝ በመሆኑና የኢኮኖሚ ዕድገት ፕላኖችን የሚያጸድቀው አካል እንደመሆኑ ሁሉ ሠራተኛው ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቆጣጠርና ዕድገቱን ለመምራት የሚችልበት ሌላው ተቋም ነው ።

ለማጠቃለል በሶሻሊዝም የምርት ማኔጅመንት ሥራና ቁጥጥር ለይምሰል ሳይሆን በሐቅ ዲሞክራሲያዊ ነው ። ከኅብረተሰቡ ወደኮሚኒዝም እየተጠጋ መሄድ ጋርም ይበልጥ ዲሞክራሲያዊ እየሆነ የሚሄድ ነው ።

ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ምሥረታ በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት

በኢኮኖሚ ዕድገት ሂደት ውስጥ ምርታማነትን ማሳደግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ። በአዲስ የኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ ወሳኝ የሆነውን የምርታማነት ዕድገት ለማረጋገጥ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ካላቸው ዋና ዋና አብዮታዊ ክንውኖች ውስጥ የሚገነባው የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚመራበትን አዲስ ዓይነት የማኔጅመንት ሥርዓት የመዘርጋት ተግባር ነው ። ዋና ዋና የኢኮኖሚ አውታሮች በመንግሥት (በሕዝብ) ይዞታ ሥር መዋል ፣ የሶሻሊስት ግንኙነቶች መፈጠርና በሠራተኛው ውስጥ የሥራ ፍላጐት ማደግ ለብቻቸው የሚፈለገውን ውጤት ማለትም አንድ ወጥና ታዳጊ ሶሻሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓት አያመጡም ። እነዚህ እርምጃዎችና የአስተሳሰብ ለው

Digitized by Google

ጦች አዲሱን የምርት ሥርዓት በአዲስ
መልክ ለመምራት የሚያስችለውን የማኔ
ጅመንት ሥርዓት ለመዘርጋት ቅድመ ሁኔ
ታዎች መሆናቸው መዘንጋት የለበትም ።
የኢኮኖሚ ማኔጅመንትም እንዲሁ በአዳዲ
ስና ትክክለኛ ዘዴዎች ላይ ወደተመሠ
ረተ ሥርዓት የተከተለ ማኔጅመንት መሸ
ጋገር አለበት ። በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት
ውስጥ የተወሰዱ እርምጃዎችና በአብዮቱ
ሰነዶች ውስጥ የሰፈሩ ሐሳቦች ይህን ሽግ
ግር ተግባራዊ ለማድረግ የተወጠኑ ናቸው ።

ዋና ዋና የኢኮኖሚ አውታሮች በሕዝብ
ይዞታ ሥር መምጣታቸው የአገሪቱ ኢኮ
ኖሚ የወጥነት ባሕርይ እንዲይዝና የተለ
ዩት የኢኮኖሚ ዘርፎችም በብዙ መጠን የብ
ሔራዊ ኢኮኖሚ የማይነጠሉ ውሁድ
አካላት ሆነው እንዲደራጁ ጥረት እየተ
ደረገ ነው ። እስከ ኢሠፓ ፕሮግራም መው
ጣት ድረስ የአብዮቱ መመሪያ የነበረው
ዋነኛ ሰነድ ማለትም በብሔራዊ ዲሞክራ
ሲያዊ አብዮት ፕሮግራም «. . .ነፃና ጠን
ካራ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚቻ
ለው በብሔራዊ ኢኮኖሚ የእርሻና የኢን
ዱስትሪ ዘርፎች መሐል የተመጣጠነ ዕድ
ገት ሲኖር እንደመሆኑ በሶሻሊስት መርሆ
ዎች ላይ የተመሠረተ ማዕከላዊ ብሔራዊ
ፕላን እንዲኖር ያስፈልጋል ። » [16] በማለት
ለሶሻሊስታዊ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሥር
ዓት መዘርጋት አቅጣጫ በግልጽ ተይዟል።
በተያያዘነው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ
ከአያሌ የግንባታ ተግባሮች ባላነሰ ያልተ
ቋረጠ ትኩረት ያገኘ ጉዳይ ይኸው አዲስ
የኢኮኖሚ አስተዳደርና ማዕከላዊ ፕላን
ሥርዓት የመዘርጋት ተግባር ነው ። ለዘመ
ናት እጅግ በከፋ ኋላቀርነት ውስጥ ዳዴ
ሲል የኖረውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋ
ጠንና በአድኀሮት ጦርነትና ጌራ የደረሰበ
ትን ጉዳት ለመጠገን ብዙ እርምጃዎች በየ
ጊዜው የተወሰዱ ቢሆንም የተቀነባበረና
ጠንካራ እርምጃ የተወሰደው በ1971 ከተ
ጀመረው ብሔራዊ አብዮታዊ የምርትና የባ
ህል ዕድገት ዘመቻ ነበር ለማለት ይቻላል።

ከዘመቻው መጀመር ጋር ብሔራዊ ኢኮ
ኖሚውን ከአንድ ማዕከል የመምራት ተግ
ባር ባለቤት ማግኘቱ ዋነኛው ጉዳይ ነው ።
በዚህ ረገድ ማዕከላዊ መምሪያው ባቋቋ
መው ዓዋጅ ላይ እንደተመለከተው የአገሪ
ቱን የሰው ፣ የገንዘብና የቁሳዊ ሀብት አሰባ
ስቦ የማንቀሳቀስ ፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ
ዎችን የማቀናጀትና አንድ ወጥ የሆነ
የኢኮኖሚ ፕላን የማውጣት ሥልጣን ተሰ
ጥቶታል ። አጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚ
እንቅስቃሴና ማኔጅመንት በመምሪያው
የበላይ አመራር ሥር እንዲሆን ተደረገ ።
ማዕከሉ የክፍለ ሀገር ፣ የአውራጃና የወረዳ
የምርትና የባህል ዕድገት ጽ/ ቤቶች ስለነበ
ሩት አመራሩ ለኢኮኖሚና ማኅበራዊ ተቋ
ሞች ሁሉ በውስጣቸው በሚገኙ የምርትና
የፕላን ዘርፎች አማካይነት ይደርሳል ።

የታቀደ የማኔጅመንት ሥርዓትን በመዘ
ርጋት ረገድ ዓይነተኛው ጉዳይ መረጃ ነው።
ቅድመ አብዮት ኢትዮጵያም ሆነች ማናቸ
ውም ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚታገል
አገር በኢኮኖሚ ግንባታ ዘርፍ ከሚያጋጥ
ሙት ዋና ዋና ችግሮች አንዱ መረጃዎችን
አሰባስቦ የመያዝ ልምድና ኢኮኖሚውን
በዕቅድ ለመምራት አስፈላጊ የሆኑት መረ
ጃዎች አለመኖር ነው ። የመምሪያው መቋ
ቋም በጥልቀት እንዲጤኑ ካደረጋቸው ጉዳ
ዮች አንደኛው ይኸው በመሆኑ የማዕከላዊ
ስታትስቲክስ ጽ/ ቤት ተጠናክሮ ከመም
ሪያው ጋር እንዲቋቋምና የኢኮኖሚና ማኅ
በራዊ ተቋሞች ሁሉም በመረጃ አያያዝ
ረገድ ልምድ እንዲቀስሙ አመቺ ሁኔታ
ዎች ተፈጥረዋል ።

በአጠቃላይ መምሪያው የሥራ አደረጃጀት
ሶሻሊስታዊ ፈር እንዲይዝ አበረታቷል።በፈ
ጠረው አመቺ ሁኔታና በሰጠውም አመ
ራር የታየው የመሻሻል ለውጥ እጅግ ከፍ
ተኛ ነው ። የሰው ኃይል ሥልጣና በመጠ

Digitized by Google

ኑም ቢሆን በዕድገት ፍላጎታችን ላይ የተ መሠረተ እንዲሆን ጥረት አድርጓል ። የሠ ጠነ የሰው ኃይል አመዳደብና አጠቃቀ ምን ሥርዓት ለማስያዝ እርምጃዎች ተወስ ደዋል ። በተከታታይ ለሰባት ጊዜ ተዘጋጅ ተው ተግባራዊ በሆኑት ዓመታዊ የዘመቻ ፕላኖች ዝግጅትና አፈጻጸም አማካይነት ብሔራዊ ማዕከላዊ የመንግሥት ፕላኖችን በማዘጋጀት ኢኮኖሚውን በአዲስ መልክ ለመምራት በምናደርገው ጥረት ውስጥ ሰፊ ቦታ የሚይዝ ልምድ በማስገኘት ለተግባሩ መሠረት ጥሏል ለማለት ይቻላል ።

የፖለቲካ ግንዛቤያቸው የሰፋ ፣ በተሰጣ ቸው ኃላፊነት አንፃር በቂ ዕውቀትና ብቃት ያላቸው ፣ የላቀ የማደራጀትና የማሰባሰብ ችሎታ ያላቸውን ማኔጀሮች መርጦ ማስቀ መጥ የማኔጅመንት ሥራው በጥራት መከ ናወኑ አንዱ ማረጋገጫ ነው ። በአብዮቱ መነሻ ይህን የመሰሉት ሥራ መሪዎች ተሟ ልተውና በሚፈለገው መጠን ማግኘት አስ ቸጋሪ መሆኑ አያጠያይቅም ። ይሁንና ይህን እጥረት በከፍተኛ የትምህርትና የማኔጅመንት ተቋሞች ለሙያ ማሻሻያ በሚ ሰጡ ትምህርቶች፣በየጊዜው በሚደራጁ ኮር ሶችና በመሳሰሉት መንገዶች የማኔጅመንት ሠራተኞችን በማዘጋጀት መወጣት አማ ራጭ የለውም ።

በተለይ የኢኮኖሚ ዕድገት ስልታችን ፈር በግልጽ የተዘረጋበት የኢሠፓአኮ ማዕ ከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ በዚህ አቅጣጫ ተጨባጭ እርምጃ እንዲወሰድ ውሳኔ ያሳለፈው ከዚሁ በመነሣት ነው። «ይህን የሚመለከተው የውሳኔው ክፍል «ዛሬ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን የማኔጅመ ንት ድክመት ለመወጣትና ወደፊት እየተ ራመደ ለሚካሄደው ታሪካዊ የግንባታ ምዕራፍ ተገቢውን የማኔጅመንት ድጋፍ ለማስገኘት ምርምር ፣ የአማካሪነት አገልግ ሎትና የሥልጠና ፕሮግራምን በማቀናጀት የሚያካሂድ ተቋም እንዲቋቋም » [16] ወስ ኗል ። ችግሩንም ለማስወገድ ከተወሰዱት

እርምጃዎች አንዱ ብሔራዊ የሥራ አመ ራር ኢንስቲትዩት እንዲቋቋም መደረጉ ነው ። ተቋሙም የሙያ ማሻሻያ ሥልጠ ናን ሥርዓት በማስያዝ ፣ የመንግሥት የተ ቋሞች አመራርና አስተዳደርን በብቃት ለማደራጀት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምር ችን በማካሄድና ውጤቶችን በማሰራጨት ተግባራዊነታቸውን በመከታተል ረገድ የአ ዲሱን የሥራ አመራርና አስተዳደር ሥር ዓት ለመዘርጋት ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያደ ርጋል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በሶሻሊስት የማኔ ጅመንት ሥርዓት ውስጥ አንዱ የማይዘለል ቁምነገር ሰፊና የነቃ ሕዝባዊ ተሳትፎ ነው። ስለሆነም ሠርቶ አደሩ ሕዝቡ በብሔራዊ ሀብት አጠባበቅ ፣ አስተዳደርና አመራር የሚያደርገው ተሳትፎ የሚገለጽበት ድርጅ ታዊ ሥርዓት መዘርጋትና በዚህ አቅጣ ጫም ንቁ ተሳትፎውን ማበረታታት ፍጹም ቸል ሊባል የሚችል ጉዳይ አይደለም ።

በአገራችን የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ሥር ዓት መዘርጋት ከዚሁ አጠቃላይ ሐቅ የሚ ነሣ ነው ። የሠርቶ አደሩን ቁጥጥር ኮሚቴ ባቋቋመው ዓዋጅ (ዓዋጅ ቁጥር 213/ 1974) እንደተመለከተው ብሔራዊ ሀ ብ ት ን በመጠበቅና በመንከባከብ ረገድ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ማሳ ደጊያና የሠርቶ አደሩን ተሳትፎም ሆነ በተ ሳትፎው ሊከናወን ለሚገባው ብሔራዊና አብዮታዊ ተግባር ማዕከላዊ አመራር የሚ ሰጥ አካል ነው ። በአሁኑም ወቅት በብሔ ራዊና በክልሉ ፣ በማምረቻ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ጭምር በተቋቋሙት የሠ ርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴዎች አማካይነት ሠርቶ አደሩ የምርትን ሂደትና በአጠቃላ ይም ብሔራዊ ሀብትን በመቆጣጠሩና በመ ምራቱ ተግባር ላይ ይሳተፋል ።

በእርግጥ በምንገኝበት የሽግግር ወቅት በማናቸውም ከፊል ፊውዳል ኋላቀር ኅብ ረተሰብ ውስጥ እንደሚታየው ሁሉ ሠራተ

Digitized by Google

ኛው ለዘመናዊ ኑሮና የአሠራር ዘዴዎች
ያለው ትውውቅ አነስተኛ ሊሆንና በአጠ
ቃላይም ምርትን ለመምራትና ለመቆጣ
ጠር ልምድና አቅም የሚጐድለው ሊሆን
ይችላል ። ይሁንና ከአንዳንድ የቀድሞውን
ሥርዓት ለመመለስ ከሚሹ ፣ ወይም ጨርሶ
ደብዛው እንዳይጠፋ ከሚጥሩ ከፍተኛ ትም
ህርትና ልምድ ካላቸው ተመጻዳቂዎች
ይልቅ በበለጠ ስሜትና ፍላጐት ይሠራል ።
ስለሆነም የሚታይበት የልምድ ማነስ ፣
አልፎ አልፎም አላዋቂነት በማኔጅመንት
መዋቅር ውስጥ የሚያደርገውን ተሳትፎ
ሊገታው አይገባም ። ስለሆነም ሠራተኛው
ራሱን በማደራጀት የምርትን ሂደት የመ
ቆጣጠሩን ተግባር ተያይዞታል ። በዚህም
ተግባሩና ጥረቱ ምርትን ለማምረት የሚያ
ስፈልገውን ዕውቀትና ልምድ ያከማቻል ።
ከውስጡም የላቀ አደራጆችንና ሥራ መሪ
ዎችን ያፈራል ።

ሠራተኛው የአዲሱን ሥርዓት መሠረት
ለመጣል በሚደረገው ጥረት በማምረት
ተግባር ላይ ከመሠማራት ባሻገር ሂደቱን
በመቆጣጠርና ዕድገቱን በመምራት ተግባር
የሚሳተፍባቸው መድረኮች የሠርቶ አደሩ
ቁጥጥር ኮሚቴዎች ብቻ አይደሉም ።በአብ
ዮታችን እንደገና ተጠናክረው የተደራጁት
የሠራተኛው ማኅበራት ሌሎች መድረኮቹ
ናቸው ።

በተለይ በሠራተኛው መሐል በመስፋ
ፋት ላይ ያለውን አዲስ ዓይነት አስተሳሰ
ብና ሕዝባዊ አመለካከት (የሥራ ፍቅር ፣
የመተባበርና የመረዳዳት ስሜት ፣ የራስን
ፍላጐትና ጥቅም ከኅብረተሰብ ጥቅምና
ፍላጐት የማስተሳሰር ልማድ ፣ ወዘተ . . .)
በማዳበር ፣ በመኮትኮትና በማሳደግ ረገድ
የሠራተኛው የሙያ ማኅበራት ከፍተኛ
ሚና ይጫወታሉ ። ብቃት ያላቸውን ሥራ
መሪዎች ለማፍራት ያግዛሉ ። በፕላን ዝግ
ጅትና በተግባር በመተርጐሙም ላይ ሠራ
ተኛውን በማሳተፍ ለምርት አመራር ቅል
ጥፍና ዕድገት ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያደር
ጋሉ ። በረጅሙም « በአጠቃላይ የኮሚኒ
ዝም ትምህርት ቤቶች እንደመሆናቸው
ሁሉ ፣ የሙያ ማኅበራት ፣ በተለይ መላውን
ሰፊ ሠራተኛ ፣ በዘለቄታውም ጠቅላላውን
ሠርቶ አደር ሶሻሊስት ኢንዱስትሪን (ቀስ
በቀስም እርሻን ጭምር) በማስተዳደር ጥበብ
ማሠልጠኛ ት/ቤት መሆን አለባቸው ።» [17]

አዲስ የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሥርዓት ለ
ማዋቀር ከተደረጉት ጥረቶች አንፃር ሲታይ
በኢኮኖሚ ማኔጅመንት ውስጥ ቁልፍ ቦታ
የሚይዘው የታቀደ ዕድገትን የማረጋገጥ
ተግባር ጐላ ያለውን ቦታ ይይዛል ። ቀደም
ሲል እንደተገለጸው በብሔራዊ አብዮታዊ
የምርት ዘመቻና ማዕከላዊ ፕላን ጠቅላይ
መምሪያ መቋቋምና በአመራሩም በተካሄዱት
ሰባት የዘመቻ ዓመታት ውስጥ በተገኙት
ልምዶች ኢኮኖሚውን በማዕከላዊ ፕላን
ለመምራት ሰፊ መሠረት ለመጣል ተችሏ
ል ። በሂደቱም ውስጥ ኢኮኖሚያችንን በዕ
ቅድ ለመምራት ይታዩብን የነበሩትን ጉልህ
ድክመቶች (ለምሳሌ የመረጃዎች እጥረት
የማቀድ ልምድ ማነስ ፣ ወዘተ ...) በመጠኑ
ለማስወገድ ተችሏል ። ስለሆነም ካለፈው
የዘመቻ አሠራር ወደተቀነባበረና ወደተዋ
ሃደ አሠራር ፣ ከዘመቻ ዕቅዶች ወደ ማዕከ
ላዊ የመንግሥት የኢኮኖሚ ዕቅዶች መሸ
ጋገር ወቅቱ የሚጠይቀውና የፈቀደውም
ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል ። ተጠሪነቱ ለሚኒስ
ትሮች ምክር ቤት የሆነው «የማዕከላዊ ፕ
ላን ብሔራዊ ኮሚቴ» መቋቋምም ለዚሁ
ቀጥተኛ ምላሽ ነው ።

የብሔራዊ ኮሚቴው መቋቋም በአዲስ
የማኔጅመንት ሥርዓት ምሥረታ ውስጥ
ከፍተኛ እመርታ ነው ። በዘመቻ ዕቅዶች
ፈንታ ማዕከላዊ ብሔራዊ ዕቅዶች እየተነ
ደፉ ተግባራዊ ወደሚሆኑበት ሥርዓት ፣
ውስን ከሆነ የኢኮኖሚ አመራር ወደአንድ
ወጥና የተጠቃለለ ማዕከላዊ አመራር መሸ
ጋገርን የሚያበስር ነው። ኮሚቴው የኢኮኖ
ሚ ፖሊሲ ግቦችንና ዕቅምን የሚያቀናጅ
ብሔራዊ ፕላን ተግባራዊ ለማድረግ እንድ

Digitized by Google

ወግ የሆነ የአመራር ሥርዓት ዘርግቷል ። ይህ ሥርዓት የኀብረተሰቡን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግቦችን ውህደት የሚያትፍ ነው ። በተዋረድ የተቋቋሙት «... የቀጠና ፕላን ጽ/ቤቶችም ለማዕከላዊ ፕላን ዝግጅት ተፈላጊውን መረጃ በማጠናቀርና እንዲሁም አካባቢያቸው የፕላኑን አፈፃፀም በማስተባበርና በመቆጣጠር የአገሪቱን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት በፕላን የመምራት ብቃትን ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይና ራቸዋል ።» [18]

አሁን የምንገኝበት የትግል ወቅት ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን በማጠናቀቅ ለሶሻሊዝም ተፈላጊ የሆኑትን ማቴሪያላዊና ቴክኒካዊ መሠረቶች የምንገልጥበት ነው ። ይህም ተግባር በእስካሁን ትግላችን የተቀዳጀናቸውን ድሎች በማጠናከርና የግንባታ ትግሉን በበለጠ ቀራጥነት ወደፊት በመግፋት ብቻ የሚከናወን ነው ።

ይህም ኢኮኖሚውን በሳይንሳዊ መንገድ ለማስተዳደር የምናደርገውንም ጥረት ያጠቃልላል ። በሌላ አባባል አዲሱን የኢኮኖሚ ሥርዓት በአዲስ መንገድ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችለንን ሥርዓት በመዘርጋትም ረገድ እስካሁን የተገኙትን ልምዶችና ውጤቶች በመያዝ ወደፊት መራመድ ያሻል ማለት ነው ። እስካሁን የተጣሉት የመነሻ መሠረቶች ብቻ መሆናቸውን በመገንዘብ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሥርዓት በሙሉ ቅርጹ እንዲሰፍን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው ።

ፓርቲያችን በመሥራች ጉባዔው ላይ ባፀደቀው ፕሮግራም በዚህ ረገድ የዘረጋው ተግባር በሚከተሉት ነጥቦች ተጠቃሎ ሊቀርብ ይችላል ።

«ማዕከላዊ ፕላንና የቀጠና ፕላንን በማጠናከር ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ መሠረት በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ሂደት ተሳትፎውን በተፈላጊው መልክና መጠን በተግባር እንዲተረጉም ይደረጋል ። የየዘመኑን ፕላኖች ሳይንሳዊ በሆኑ ዘዴዎች ለማዘጋጀትና አፈጻጸማቸውንም በዚሁ መልክ ለመቆጣጠር የሚያስችል የስታቲስቲክስ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ። የፕላኑን ተገባራዊነት ለመቆጣጠርና የፕላን ዲሲፕሊንን በሚገባ ለማስከበር የየዘመኑ ፕላኖች በሕግ መልክ ይቀረጻሉ ።»

«... ሳይንሳዊ የሥራ መለኪያዎች በሥራ ላይ መዋልና ክፍያም በሥራ መጠንና ጥራት ላይ በተመሠረተ መልክ መፈጸም አለበት ። . . . የሚሰጠው ክፍያም አንድ ወጥ ሊሆን የሚችልበት ሥርዓት ተቀይሶ ተግበር ላይ መዋሉም ይረጋገጣል። . . . ሠራተኛው በምርት አስተዳደር ሥራ ቀጥተኛ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችሉት ሁኔታዎች በተሟላ መልክ እንዲመቻቹ ይደረጋል ። . . . በግለሰቦች፣በምርት ክፍሎች፣ በፋብሪካዎችና በኢንዱስትሪዎች መካከል የሥራ ውድድር እንዲካሄድ ለማድረግና ጉልህ የውጤት ብልጫ የሚያሳዩትም የሚገባቸውን [illegible] ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወስዳሉ ። . . . በኢኮኖሚ አስተዳደር ውስጥ ቀልጣፋነትንና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ሳይንሳዊ የሆነ የሒሳብ አያያዝ እንዲሰፍን የንብረት አመዘጋገብ ፣ አጠባበቅና አጠቃቀም የተሻለ ሥርዓት እንዲይዝና የሶሻሊስት ይዞታ በቁጠባ ፣ በትርፍና በኪሣራ ስሌት መርህ መሠረት እንዲሠራ በድርጅቶች መካከል የሚኖረው ግንኙነት ሕጋዊ መልክ እንዲይዝ የሚያግዙ አስተዳደራዊ ፣ ሕጋዊና ሌሉችም አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል ።» [19]

የፓርቲያችን መሥራች ጉባዔ ባፀደቀው ፕሮግራሙ በየዘርፉ የሚጠብቁትን ተግባራት ያብራራና የወደፊቱን የዕድገት አቅጣጫዎች የተለመ ብቻ ሳይሆን በተለይ በኢኮኖሚ ግንባታ ረገድ የአሥር ዓመቱን የመጀ ዕቅድም በማፅደቅ፣የኢኮኖሚ ዕድገት አመራርና አስተዳደር ተገቢው ትኩረት

Digitized by Google

የተሰጠው መሆኑን ሲገልጽ «በመሪ ዕቅዱ ዘመን ውስጥ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ አስተዳደር ሥርዓትን ለመገንባትና ለማጠናከር ከፍተኛ ተቀዳሚነት ይሰጣል» [20] ብሏል።

ከላይ እንደተዘረዘረው በፓርቲያችን ፕሮግራምና በሱም ላይ በመመሥረት የተነደፈው የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ፣በየደረጃው ተዘጋጅተው የሚወጡትም ዓመታዊ ዕቅዶች ተግባራዊነት በሚጠይቀው ሁሉ የኢኮኖሚያችንን ሁኔታ ካለፈውና ሊሆን ከሚገባው በማነፃፀር፣ግምገማ በማድረግ ተግባራዊ የእንቅስቃሴ አቅጣጫዎችን ያመለከተውና ስልቶችን የዘረጋው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ነው ። በዚሁ ስብሰባ ላይ በፓርቲያችን ሰነዶች የተመለከተውን በማጠቃለል በጓድ አብዮታዊ መሪያችን ፣

« የኢኮኖሚ ፖሊሲያችን መሠረታዊ ዓላማ የምርት ኃይሎችን ዕድገት በማፋጠን የኢኮኖሚያችንን የማምረት ችሎታ ማሳደግ፣ የሶሻሊስቱን ይዞታ የኢኮኖሚ አስተዳደር በማሻሻል የድገት እንቅፋቶችን ማስወገድና በዚህም ሂደት ውስጥ የኢኮኖሚ ግንባታችን ዓላማ የሆ ነውን የሠርቶአደሩን ሕዝብ የኑሮና የባህል ደረጃ ማሳደግ ነው ።»[21]

በማለት እንደተገለጸው እንቅስቃሴዎቻችን በዚህ ሁሉ አቅጣጫ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ እንደሚያሻ በማስገንዘብ ዋነኛ የወቅቱን ተግባሮቻችን የተመለከቱ ሲሆን ኢኮኖሚውን በመምራትና በማስተዳደር ረገድ መሠረታዊ ችግሮችና ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች በሚገባ ተጨነዋል ።

ስለወቅቱ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታዎችና መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ለዚሁ ለማዕከላዊ ኮሚቴው ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ በቀረበው የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ሪፖርት ተተንትኗል ።በዚሁም መሠረት በአሥር ዓመቱ መሪ ዕቅድ ውስጥ የተተየሰውን አጠቃላይ ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ በወቅቱ የሚታዩትን አንገብጋቢ ችግሮች ለማቃለልና ለማኅበራዊ ዕድገት መፋጠን የተሻለ መሠረት ለመፍጠር በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ዓይነተኛ ትኩረት የሚከተሉትን ዓላማዎች ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል ።

«1. የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ የተፈጥሮን ችግር ለመቋቋም የተየሰውን የድርጊት ፕሮግራም ተግባራዊነት በማጠናከር የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ዕድገት በአፋጣኝ ማዳበር ፣

2. የኢኮኖሚውን ዕድገት ለማፋጠን እንቅፋት የሆኑ የአሠራር ጉድለቶችን ፣ የማኔጅመንት ድክመቶችንና የፖሊሲ ፕሮግራሞችን በመፍታት ለአጠቃላይ ምርታማነት ዕድገት የበለጠ አመቺ ሁኔታ መፍጠር ፣

3. የኢኮኖሚውን የወደፊት የማምረት አቅም ለማዳበር ቁልፍ የሆኑ መስኮችን ማፋጠን ፡» [22]

በሪፖርቱ ላይ እንደተመለከተው በኢኮኖሚ ተቋሞች መካከል ያለውን ግንኙነት በሕጋዊ ኮንትራት ለመምራት የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ።

የዚህ ዘዴ ዋነኛ ፍሬ ነገር ቀደም ሲልም እንደተብራራው የኢኮኖሚ ተቋሞች ለሚያካሂዷቸው እንቅስቃሴዎች ውል በሰጧቸው ሌሎች ወገኖች ፊት ተጠያቂነት እንዲኖርባቸው የማድረጉ ጉዳይ ነው ። በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ በአምራች ድርጅትና በጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች እንዲሁም በአምራች ድርጅቶችና በምርት ውጤት አከፋፋይ ድርጅቶች መሐል ግንኙነት አለ ። ይህ ግንኙነት ሕጋዊነት ባለው መሠረት ላይ የተዘረጋና ተግባራዊ መሆኑን የሚከታተል ኃይል የሚያየው መሆኑ ለተ

Digitized by Google

ለጠፈ የምርትና የሥርጭት ሂደት ወሳኝ
ነው ። ምክንያቱም በቅድሚያ በሚገባ
ውል መሠረት ጥሬ ዕቃ መቅረቡ ፣ መመረ
ቱና ለሽያጭ መታሰቡ የዕቅድ ዝግጅት
ንም ሆነ የአፈጻጸም ክትትልን የተመቻ ያደ
ርገዋል ። ከተዋዋዮቹ በማናቸውም በኩል
የሚከሰት ድክመት ዞሮ መንግሥትንና
ተጠቃሚውን ሕዝብ ፣ በአጠቃላይም የአ
ገሪቱን ዕድገት የሚጐዳ መሆኑ ግልጽ ነው።
በሌላ በኩል ዐቅምን በሚገባ በመለካትና
ወደፊት የሚደርሰን አዳዲስ ለውጥንም በማ
ሰብ በሚገባ ውል መሠረት የሚካሄድ የቀለ
ጠፈ የግንኙነት ሥርዓት የሚያስገኛቸው
ጥቅሞች ከፍተኛ ናቸው።በሪፖርቱ እንደተ
ገለጸው ለዚህ ጉዳይ ተግባራዊነት በቅድ
ሚያ የዕቅዱ ዝግጅት ለዚህ ዓይነቱ አሠራር
በሚያመች መልክ እንዲመራ ማድረግ የማ
ያሻማ መሆኑ ባይካድም ይህን ለማድረግ
በቂ ልምድ እንዳለ ስለሚታመን የታቀደ
እርምጃ መወሰዱ ወቅታዊነቱ አያጠራጥ
ርም ።

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ መንግሥታዊ
የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ቁጥጥር አካላትን
ሚና በማሳደግ ረገድ ሊወሰዱ ከታሰቡት
እርምጃዎች ውስጥ የፋይናንስና አስተዳደር
መመሪያዎችን መቀየስ ይገኝበታል ። ሶሻ
ሊዝምን ለመገንባት በሚደረገው ትግል
ውስጥ በኢኮኖሚው ውስጥ ከሚከሰቱ
አዲስ ሁኔታዎች መሐል አንዱ አዲስ የፋ
ይናንስ ሥርዓት መዘርጋት ነው ። ሶሻሊ
ስት የፋይናንስ ሥርዓት የገንዘብ ሀብትን
በዕቅድ የመያዝና የመጠቀም ተግባር ድር
ጅታዊ መገለጫ እንደመሆኑ በሶሻሊዝም
ግንባታ ወቅት ሀብትን አሰባስቦ ኢኮኖሚ
ውን ለመለወጥ ፣ ኢንዱስትሪን ለመገንባ
ትና እርሻን በኅብረት ሥራ ማኅበራት ለማስ
ባሰብ ፣ የባህል አብዮትን ለማራመድና የአ
ገሪቱን መከላከያ ለማጠናከር ዓይነተኛ
መሣሪያ በመሆን ያገለግላል ። ይሁንና የፋ
ይናንስ ሥርዓቱ በኢኮኖሚ አስተዳደር
ውስጥ ሊጫወት የሚገባውን ሚና እንዲያ
ከናውን በቅድሚያ ለዚህ በሚመች መልክ
ማደራጀቱ ወሳኝ ነው ።

የፋይናንስ ሥርዓቱ አንድ አካል የሆኑት
ባንኮች በሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ የሚ
ጫወቱት ሚና በሚገባ የሚተኮርበት ነው።
ባንኮች በሶሻሊዝም ጠቅላላውን ኢኮኖሚ
በታቀደ ሁኔታ ለማስተዳደር በሒሳብ መረ
ጃዎች ምንጭነት ከፍተኛ ተግባር የሚያከ
ናውኑ ከመሆናቸውም በላይ የመንግሥ
ትን ፖሊሲና ዕቅድ በመከተል የብድር
ሥርዓቱን በመምራት በዕቅዱ አፈጻጸም
ረገድ የመንግሥት ቁጥጥር መገለጫዎች
በመሆን ያገለግላሉ ። ከዚህም በላይ መን
ግሥታዊ የኢኮኖሚ ተቋሞችን የገንዘብ
እንቅስቃሴ በባንኮች አማካይነት እንዲሆን
በማድረግ ከማዕከላዊ ዕቅድ አንፃር ተቋ
ሞቹ የፋይናንስ አስተዳደር ዲሲፕሊን
መጠበቃቸውን ያረጋግጣሉ ። በአጠቃላ
ይም የገንዘብ ዝውውርን በመቆጣጠር ለተ
ጠናከረ የኢኮኖሚ አስተዳደር የሚያደር
ጉት አስተዋጽኦ ጉልህ ነው ።

ባንኮች ይህን የመሰለውን ሰፊ ተግባር
እንዲያከናውኑ የሚያስችሏቸውን የፖሊሲ
እርምጃዎች መወሰድ የግድ ነው ። በፋይና
ንስ አስተዳደር ፣ በባንክ ክሬዲትና ወለድ
ረገድ እስካሁን የነበሩትን መመሪያዎች
በመለወጥ የምንገኝበት የግንባታ ደረጃ
በሚጠይቀው መሠረት መቀረጽ ይኖርበ
ታል ። ስለሆነም በሪፖርቱ እንደተመለከ
ተው መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ የሚጫ
ወተውን ሚና በሚገባ የሚያንፀባርቁ ፣ ለደ
ረስንበት የዕድገት ደረጃ ተመጣጣኝ የሥራ
ቅልጥፍና ለማስገኘት በሚገባ የሚያተኩና
የገንዘብ ዝውውርን ማዕከላዊነት ባለው
መልክ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ፖሊሲ
ዎች ይነድፋሉ ፣ « . . . በመንግሥታዊ መ/
ቤቶችና ድርጅቶች በሥራ ላይ የዋሉትን
የሒሳብ አያያዝ ፣ የንብረት አስተዳደር ፣
የስቶክ አያያዝ ሥርዓቶችን በማሻሻል የድ
ርጅቶችን ምርታማነት ለማመልከት ፣ ለመ
ቆጣጠርና እንዲሁም ለፕላን ዝግጅት አስ

Digitized by Google

ፈላጊ የሆኑ የፋይናንስ፣የምርት ፣ የጥሬ ዕቃ ፍጆታ ፣ ወዘተ . . . የመሳሰሉትን መረጃ ዎች በቀላሉ ለማመንጨት በሚያስችል መልክ ተቀርፀው በተግባር እንዲተረጐሙ ለማድረግ ለፋይናንስ አስተዳደር ፖሊሲ መቀየስና በሥራ ላይ መዋል ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል ። » 23

ከእነዚህ ሌላ መወሰድ ካለባቸው ብዙ ተከታታይ እርምጃዎች ውስጥ የደመወዝ ክፍያ ፖሊሲን ደረጃ በደረጃ መቀየስ አንዱ እንደሆነም በሚገባ ተመልክቷል ። በሶሻሊስት የኢኮኖሚ ማኔጅመንት ሥርዓት ውስጥ አንዱ ዓይነተኛ ተግባር ተገቢ የሆኑትን የሠራተኛ ማነቃቂያና ማበረታቻዎች አሰጣጥ ስልት መዘርጋትና ተግባራዊ እንዲሆኑም ማድረግ ነው ። ይህ እንግዲህ ከመነሻው ከራሱ የደመወዝ አከፋፈል ግለሰብ ሠራተኞች ለምርታማነት ከሚያደርጉት አስተዋጽኦ ጋር የተሣሠረ ሆኖ እንዲዘረጋ ከማድረግ ይጀምራል ። እያንዳንዱ ሠራተኛ ዜጋ እንደዐቅሙ ሠርቶ እንደሥራው መጠንና ጥራት ክፍያ የሚያገኝበት የደመወዝ ሥርዓት መዘርጋቱ በዘለቄታው የሶሻሊስት ግንባታ ሂደት ውስጥ የማይታለፍ ጉዳይ ነው ። ስለሆነም ለማዕከላዊ ኮሚቴው 2ኛ መደበኛ ስብሰባ በቀረበው የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳይ ሪፖርት እንደተመለከተው ጥናት እየተካሄደና እንዲጠናቀቅም ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ።

በሌላም በኩል የጀመርነውን የግንባታ ትግል የተሳካ አድርገን አዲሱን ሥርዓት ለመገንባት መቻልና አለመቻልችን የሚለካው ምርታማነትን ለማሳደግ በመቻላችን ያህል ነው ። ስለሆነም በአጭር ጊዜም ሆነ በረዥሙ የሥራ ምርታማነት ዕድገት የሚያረጋግጡ የማኔጅመንት እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ነው ። በሪፖርቱ እንደተመለከተው የሥራው ባሕርይ በሚፈቅድ በት ሁኔታ ሁሉ የቁርጥ ሥራ ክፍያን ማስተዋወቅ አንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል ። በዚህ የክፍያ መርህ መሠረት እንደሚታወቀው አምራቹ የተሰጠውን የምርት ደረጃ ጠብቆ በአንድ በተወሰነ ጊዜ በሚያመርተው መጠን ክፍያ የሚፈጽምበት ዘዴ ነው ። የሰው ልጅ ፍላጐቶች ሰፊ ናቸው ። ፍላጐቶችን ለማሟላት እያደገ የሚሄደው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴም በማናቸውም ደረጃ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያረካቸው አይደለም ። ዘወትር አዳዲስ ፍላጐቶች ይቀሰቀሳሉ ፤ እናም አዳዲሶቹ ፍላጐቶች ይረኩ ዘንድ መካሄድ ላለበት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቀጠልና መስፋት አዲስ ግፊት ይሰጣሉ ። በዚህ ዓይነት ያለማቋረጥ ይቀጥላል ። ይህ ለኅብረተሰብ በአጠቃላይ ብቻ ሳይሆን ለኅብረተሰቡ አባላትም በተናጠል የሚሠራ አባባል ነው ። በቁርጥ ክፍያ መሠረት የሚሠራ ሠራተኛ የሚያከናውነው ሥራ ፍላጐቶቹን ለማርካት የሚያስፈልገውን ገቢ የሚያገኝበት ሂደት ብቻ ሳይሆን የሚያገኘው ገቢ መጠንም ለኅብረተሰቡ በሚያበረክተው ሥራ መጠንና ጥራት እንደሚወሰንም ለመረዳት ያስችለዋል ። ስለሆነም ምርታማነቱን ለማሳደግ ይጥራል ። ይህን በማድረግም የራሱን ገቢ ያሳድጋል። የምርታማነት መበረታታትም የኅብረተሰቡ የግንባታ ጥሪ ቀጥተኛ ምላሽ ይሆናል።

የደመወዝ ጭማሪ አሰጣጥም እንዲሁ ከምርታማነት ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። አምራች በሆነ ኢኮኖሚ ውስጥ በመሠረቱ ማምረት ዘወትር ፍጆታን እንደሚቀድም የታወቀ ነው ። አዲስና ተጨማሪ ፍጆታም እንዲሁ አዲስና ተጨማሪ ምርትን ያስቀድማል ። ስለዚህም ለሠራተኞች የሚሰጥ የደመወዝ ጭማሪ ሠራተኞቹ ከሚሠሩባቸው ድርጅቶች ትርፋማነት ዕድገት ጋር እየተመዛዘነ መሄድ ይኖርበታል ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. A Merriam — Webster; Websters, Third New International Dictionary, (unabridge pd), Vol. II, (Chicago: 1981), P. 1372.
2. Harry Steverman, Labour & Monopoly Capital, (USA), 1974, P. 64.
3. *Ibid.*, P. 65.
4 የማሌ መዝገበ ቃላት፣ በኢሠፓ ማ. ኮ. ርዕዮተዓለም መምሪያ የተዘጋጀ /ረቂቅ/፣ ገጽ 372።
5. Harry Steverman, P. 59.
6. *Ibid.*, P. 65.
7. V.G. Afanasyev, Scientific Management of Society (Moscow: Progress Publishers, 1971), P. 45.
8 የማሌ መዝገበ ቃላት፤ ገጽ 245።
9. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 42, (Moscow: Progress Publishers, 1975), PP. 79-80.
10. *Ibid.*, Vol. 27, P. 259.
11 የማሌ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 245።
12. Loc., V.G. Afanasyev, P. 44.
13. *Ibid.*, P. 71-72.
14. Berri, L. ya, Planning A Socialist Economy, Vol. 1, (Moscow): Progress Publishers, (1977), P. 45.
16. V.I. Lenin, ,Vol. 30, P. 425.

16 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም፣ አዲስ አበባ፣ ክፍል ሁለት፤ አንቀጽ 3።

17 የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች፣ የካቲት 1973። ገጽ 34፣

(Moscow); Progress Publishers, P. 190.

19 የኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ፣ አዲስ አበባ 1977 ገጽ 109።

20 የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ፕሮግራም፣ገጽ አዲስ አበባ 1977 96—100።

21 የኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ፤ ገጽ 110።

22 ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ሪፖርት፣ መጋቢት 1977፣ ገጽ 32፣ /ያልታተመ/።

23 የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ሪፖርት፣ የካቲት 1977 ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበ ገጽ 37 /ያልታተመ/።

24 ከላይ የተጠቀሰው፣ ገጽ 58።

Digitized by Google

የአርሶአደሩና የተፈጥር ግንኙነት ችግር በኢትዮጵያ

— አንዳንድ ገጽታዎች

አበበ ወርቁ

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ፣ አርሶ አደሮችን ፣ አብዮታዊ ሠራዊት ፣ ምሁራንና ተማሪዎች ከፍተኛ ሕዝባዊ ትግል እያካሄዱ ነው ። ሠራተኛው የበለጠ ለማምረትና ምርታማነቱን ከፍ ለማድረግ ይታገላል ። አርሶ አደሩ ለረጅም ጊዜ የነበረውን ኋላቀር የመሬት አጠቃቀም እየለወጠ የእርከንና የመስኖ ሥራን ፣ የዛፍ ተከላን ከዚህ በፊት በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ እያካሄደ ነው ። ልዩ ልዩ ድርጅቶቹን ለምሳሌ ፣ የገበሬዎች የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን እያጠናከረ ፣ የበለጠ ምርት ለማግኘት ጉልበቱን ፣ ዕውቀቱንና ሀብቱን እያስተባበረ ነው ። ምሁራን አርሶአደር ወገኖቻቸውን ለመርዳት ወደገጠር በመዝመትና የጉልበት ሥራ ጭምር በማከናወን ለተጎዱ ወገኖቻቸው መጠለያ የሚሆኑ ቤቶችን ሠርተዋል ። የምርምር ሥራቸውንም ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ይበልጥ እያዛመዱና ለምርት ማሳደግ በሚረዳ ሁኔታ እያደራጁ ነው ።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ኃይሉን በማስተባበር የልማት ሥራ እያካሄደ ነው ። በገጠርም ሆነ በከተማ የጓር አትክልት በማስፋፋት ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሠፈራ ሥራን በማከናወንና በመሳሰሉት ተግባራት ዓለምአቀፋዊ አድናቆት ያገኘ ውጤት እያስመዘገበ ፣ ለበለጠ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትግል እራሱን እያደራጀና እየታገለ ነው ። የዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መንስኤዎች ዛሬ የሕዝቡን ህልውና የሚፈታተኑና ዕድገቱን የሚያጓትቱ አያሌ ችግርች ናቸው ።

የኢትዮጵያ አርሶአደሮች ለብዙ ዘመናት በፊውዳላዊ የምርት ግንኙነት ላይ በተዋቀረ ጭቆና ውስጥ ሲማቅቁ የኖሩ በመሆናቸው ዕውቀታቸውንና የምርት መሣሪያዎቻቸውን አሻሽለው ከተፈጥር ጥገኝነት ለመላቀቅ አመች ሁኔታ አላገኙም ነበር ። ዛሬም ፊውዳላዊው የምርት ግንኙነት ከመ

Digitized by Google

ሠረቱ የፈራረሰ ቢሆንም ቅሪቱ በሕዝቡ ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ገና ሙሉ በሙሉ አልተወገደም ። ኋላቀር አመለካከት ፣ ለሕዝብ ሀብት አስፈላጊውን እንክብካቤ አለማድረግ ፣ አድልዎና ስግብግብነት ፣ ንዑስ ከበርቴያዊ ዝንባሌና ቢሮክራሲያዊ አሠራር ዛሬም በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ዕንቅፋቶች ናቸው።

ከመላ አገሪቱ ገበሬዎች 94 በመቶ በግል እርሻ የሚተዳደሩ ሲሆን በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር የተደራጁት አንድ በመቶ አካባቢ ናቸው።አርሶአደሮች ያላቸው የሥራ መገልገያ በደረጃቸው እጅግ ኋላቀርና በመጠናቸውም በጣም ውሱን ናቸው የሚታረሰው መሬት ለአያሌ ዘመናት በኋላቀር የአስተራረስ ዘዴ ጥቅም ላይ ሲውል የቆየ በመሆኑ ለምነቱን አጥቷል ። የተፈጥሮ ሁኔታ (በተለይም ድርቅ) ከዕለት ወደዕለት በኋላቀሩ የግብርና ዘዴ ላይ ታክሎ ችግሩን በማባባሱ የአርሶ አደሩና በአጠቃላይም ኑሮው በአመዛኙ በግብርና ኢኮኖሚ ላይ የተመሠረተው የአገሪቱ ሕዝብ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ሊወድቅ ችሏል ።

በምርት መቀነስ ምክንያት ብዙ ሕዝብ በምግብ እጦት ሕይወቱ አልፏል ። በገጠርም ሆነ በከተማ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አያሌ ሰዎች የዕለት ጉርስ አጥተዋል ፣ ወይም እጥረት አጋጥሟቸዋል ። በ1977 በገጠር የምግብ ዕርዳታ የሚሰጠው ሕዝብ ቁጥር 7.5 ሚሊዮን ሊደርስ ችሏል ። በአገሪቱ የምግብ እጥረት ከፍተኛ በመሆኑ የ1978 የመኸር እህል እስኪመረት ድረስ «ከውጭ 15 ሚሊዮን ኩንታል እህልና አልሚ ምግብ የሚያስፈልግ መሆኑ ታውቋል ።»[1] እስከ 1977 ማከተሚያ ድረስ ከተጠናቀሩት መረጃዎች ለመገንዘብ እንደተቻለው በ1978 በሕዝቡ የምግብ ፍላጎትና በግብርናው ዘርፍ አቅርቦት መካከል የ11 ሚሊዮን ኩንታል እጥረት እንደሚኖር ተገምቷል ።[2]

በአጠቃላይ ድርቁ በአገሪቱ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ክፍሎች በግብርና ፣ በኢንዱስትሪ ፣ በውጭ ምንዛሪና በመንግሥት ወጭ ላይ ችግር አስከትሏል ። ይህን ችግር በ1977 አጋማሽ ላይ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ባቀረበው ሪፖርት እንደሚከተለው ገልጾታል ።

> በ1976 የተከሰተው ድርቅ ኢኮኖሚውን የበለጠ አደጋ ላይ የሚጥል አሳሳቢ ችግሮችን አስከትሏል ። በድርቁ ወቅት መራዘምና በተጎዱትም የአገሪቱ ክፍሎች መበራከት የዘመኑ የግብርና የምርት ውጤት ከምንጊዜውም በባሰ መጠን ቀንሷል። የግብርና ምርት ውጤት መቀነስ ፣ በአመዛኙ በግብርና ጥሬ ዕቃ ተጠቃሚ በሆኑት የአገሪቱ ኢንዱስትሪዎች ላይ ተፅዕኖ አስከትሏል ። በዚህ የተነሳ የብዙ ፋብሪካዎች የምርት ውጤት በመቀነስ ላይ ይገኛል ። የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የማፍራት አቅምም የተመሠረተው በግብርና ምርት ውጤቶች ላይ እንደመሆኑ ድርቁ በዚህ ረገድ አሳሳቢ የሆኑ ችግሮችን አስከትሏል ። በአንድ በኩል ከግብርናና ከኢንዱስትሪ የምርት ውጤቶች መቀነስ እንዲሁም ከውጭ ንግድ ጋር የመንግሥት ገቢም እየቀነሰ ሲመጣ በሌላ በኩል የድርቁን ችግር ለመቋቋም የመንግሥት ወጭ በመጨመሩ ጠቀላላው የኢኮኖሚ ሁኔታ ከፍተኛ ትኩረትን የሚጠይቅ ሆኗል ።[3]

ከተጠቀሱትና ከሌሎችም መሰል መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ መቃወስ የኢንዱስትሪ ዕድገትን የሚያዳክምና የሙአለ ንዋይ እጥረትን የሚያባብስ ፣ በዚህም ምክንያት የአገሪቱን ሕዝብ ዕድገት የሚያጓትት ነው። ይህ መጓተትም ሕዝቡን በየወቅቱ ለሚከሰት ተፈጥሯዊ ችግር የሚያጋልጥና ሁሉ

Digitized by Google

ውናውን አጠያያቂ የሚያደርግ ነው ። ዛሬ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የሚካሄደው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ዓላማ ለረሃብና ለጭቆና የዳረገውን ኋላቀርነት ማስወገድ ፣ የገጠሙትን የተለያዩ ችግሮች መፍታትና የተሟላ ነፃነት ማጐናጸፍ ነው ። ይህ ችግር እንዴትና በምን ሁኔታ ሊፈታ ይችላል ?

ባለፈው እትማችን የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር (መስከረም ቅጽ 5 ቁጥር 22 ፣ 1977) በሚል ርእስ የኅብረተሰቡና የተፈጥሮ ግንኙነት መሠረት ሥራ ፣ እንዲሁም በሁለቱ መካከል የሚፈጠረው ግጭት መፍትሔ ማግኘት የሚወሰነው በኅብረተሰቡ ዕድገት ፣ በተለይም በሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነት ምሥረታ ፣ የተፈጥሮ ሀብት በዕቅድ አጠቃቀምና በንቃት ላይ የተመሠረተ ሕዝባዊ ተሳትፎ በማስፈን መሆኑን በመግለጽ ዋና ዋና ነጥቦችን ተመልክተናል ። በዚህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የእርሻ ሥራ ፣ የአርሶአደሩና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር እንዴት ሊፈታ እንደሚችል አንዳንድ ገጽታዎችን ለመዳሰስ እንሞክራለን ።

ግብርና በተለይም እርሻ አንደኛ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተ ፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በአመዛኙ የሚገለጽበትና ኑሮውም የተመሠረተበት ፣ ሁለተኛም ፣ በአንድ በኩል ግንኙነቱ የከፋ ችግር የገጠመው ፣ በሌላ በኩል የሕዝቡ ህልውናና ዕድገት በቅድሚያ በዚህ ችግር እልባት ማግኘት የሚወሰን መሆኑ ግንዛቤ አግኝቶ ከፍተኛ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ የሚደረግበት መስክ ነው ።

የዚህ ዓይነቱ ችግር በተለያዩ አቅጣጫዎች ወይም ከተለያዩ የሳይንስ መስኮች አንፃር ለምሳሌ በሥነ አፈር ፣ በሥነ ደንና በሥነ ውሃ ረገድ መመርመር ያለበት ነው። በዚህ ጽሑፍ ችግሩን ለመረዳትና መፍትሔ ለመጠቆም የምንሞክረው በፍልስፍናዊ ወይም ጠባብ ባለ አገላለጽ በታሪካዊ ቁስአካልነት አንፃር ነው ። በመሆኑም አቀራረቡ የአጠቃላይነት ባሕሪ ይኖረዋል ።

በዚህ አቀራረብ ፣ ተፈጥሮን መንከባከብ ማለት ምን ማለት ነው ? የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ተፈታ ማለት ምን ማለት ነው ? ለችግሩ መፍቻ የሚሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በምን ደረጃ ላይ ናቸው ? ሰው በተፈጥሮ ላይ ያለው የቁጥጥር ደረጃ መለኪያ ምንድን ነው ? በዚህ አንፃር የኢትዮጵያ አርሶአደር ምን ደረጃ ላይ ይገኛል ? በችግሩ አፈታት ወሳኙ ኃይል ምንድን ነው ? እነዚህንና ተዛማጅነት ያላቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን ። ጥያቄዎቹን ለመመለስ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በአርሶአደሩ የሥራ ሂደት ውስጥ ችግሩን ለመፍታት የሚያስችለው ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነትና የምርት ኃይሎች የድገት ከምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ፣ ምን ለመሥራት እንደታቀደና ምን ርምጃ እየተወሰደ መሆኑን እንቃኛለን ።

የችግሩ አፈታት ባህርይ

ምግብ ፣ ልብስና መጠለያ ለሰው ልጅ ኑሮ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ። የምግብ ጣዕም ፣ የልብስ ውበትና የመጠለያ ምቹነት እንደተጠቃሚው ኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ሊለያይ ቢችልም የማንኛውም ኅብረተሰብ ህልውና ካለእነዚህ መሠረታዊ ነገሮች የተሟላ አይሆንም ። የመሠረታዊ ፍላጎቶች ማርኪያዎችም ሆኑ የቅንጦት ቁሳቁሶች የሚገኙት ወይም የሚመረቱት ከተፈጥሮ ነው ።

ሰው ካለተፈጥሮ ግንኙነት ፣ ከተፈጥሮ ጋር መስተጋብር ሳያደርግ ፣ ማለትም በሥራው አማካይነት በተፈጥሮ ሀብት ሳይጠቀም ሊኖር አይችልም ። የሰውና የተፈጥሮ ግንኙነት በማንኛውም ኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ወይም ሰው እስካለ ድረስ የግድ መኖር ያለበት ሂደት ነው ። ይህ ግን

Digitized by Google

ኙነት ለሰው ህልውና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማምረት «በአንድ በኩል ሰውና ሥራው ፣ በሌላ በኩል ተፈጥሮና ሀብቷ ሆነው»[4] የሚያካሂዱት መስተጋብር ነው።

በዚህ ግንኙነት ወይም መስተጋብር መሠረት ሰው ተፈጥሮን በሚበጀው መንገድ በሥራ መለወጡ ፣ ሰው በተፈጥሮ ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ የግድ ነው ። አንዳንድ ሳይንቲስቶች ፣ ሰው በተፈጥሮ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ውሉ አድሮ የሚያስከትለውን ነገር በትክክል ለማወቅ ስለማይቻል ሰው ሠራሽ የተፈጥሮ ለውጥ በተለይም በከፍተኛ ቴክኖሎጂ አማካይነት የሚካሄደው ለውጥ መቆም አለበት ይላሉ። ይሁን እንጂ በማርክሲስቶች አመለካከት ሰው በተፈጥሮ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖና ተፈጥሮን መለወጡ የማይገታና ይልቁንም እያየለ የሚሄድ ነው ።[5]

ለምሳሌ፣ የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ ምግቡን ለማብሰል ፣ መጠለያውን ለማሞቅና እንደየዕድገት ደረጃው የሚኖሩትን ፍላጎቶች ለማርካት በእሳት ሲጠቀም ኖሯል ። በእሳት መጠቀም ማለት በአካባቢ ኦክስጂን መጠቀም ማለት ነው ። በአሁኑ የዓለም ሁኔታ ከሰው ዘር መበራከትና ከኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋርም የኦክስጂን አጠቃቀም እጅግ እያደገና አሳሳቢ ችግር እየፈጠረ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ ። ታዲያ መፍትሔው ይህን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎችን መፈለግ እንጂ ሰዎች በፍጹም በእሳት አይጠቀሙ ወይም እሳት አይንደድ ማለት የማይሆን ነው ፤ ይሁን ቢባልም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ። ስለዚህ ሰው ለመኖር እንደየሁኔታው በእሳትና አብሮም በኦክስጂን መጠቀሙ ግድ ነው ።*

ዛሬ በኢትዮጵያ በመስፋፋት ላይ ያለው የመስኖ ሥራ ተፈጥሮን ለመግራት ፣ ወንዞችን ወደሚፈለግ አቅጣጫ ለመምራትና ልማትን ለማስፋፋት ከዚህም ተያይዞ በአገሪቱ የተፈጠረውን የምግብ እጥረት ለመቋቋምና ወደ የላቀ የዕድገት ደረጃ ለመሸጋገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ዕሙን ነው ። ከመስኖው ሥራ ጋር የአካባቢ የተፈጥሮ ሁኔታ ለውጥ ሊከተል ይችላል ። ለዚህም መፍትሔው አጠቃቀሙን ሳይንሳዊ ማድረግና በየደረጃው የሚነሡ ችግሮችን ለመፍታት መታገል እንጂ ፣ ሕዝብ ለመኖር ሲል በተፈጥሮ በመጠቀሙ ሊከተል የሚችለውን ችግር በመፍራት «እጁን ከተፈጥሮ ላይ ያንሣ» ማለት ትክክል ሊሆን አይችልም ።

የሰው ልጅ ለዘመናት ያካሄደው የግብርና ተግባር ፣ እንዲሁም በኢንዱስትሪና በሌሎችም የሥራ መስኮች ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች የተፈጥሮን ሚዛን ማናጋቱ ይታወቃል ። ኑሮውን ለማመቻቸት ሲል አንዳንድ ሁኔታዎችን ሲለውጥ ወይም ሲያስወግድ ሌሎችን ደግሞ አዳብሯል ወይም አጠናክሯል ። ይህ ሰው በተፈጥሮ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የሚቀጥል ነው ።

በዚህ መሠረት ተፈጥሯዊ ሚዛን ቢናጋ ለማስተካከል (ለምሳሌ ዝናብን በሰው ሠራሽ ዘዴ ለማዝነብ ጥረት ማድረግ) እንጂ ተፈጥሮ ሚዛኗን እንድትጠብቅ ለማስቻል ሰው በዚ መጠቀም ማቆም አለበት ወደሚል አስተሳሰብ ወይም አሠራር መመለስ ጠቃሚ አይደለም ፤ ለመመለስም አይቻልም ።

በሌላ በኩል ግን ኅብረተሰቡ እስከ ተወሰነ ጊዜም ቢሆን በአንዳንድ የተፈጥሮ ሀብቶች መጠቀም ማቆምና እንክብካቤ ማድረግ ያለበት መሆኑ መታወስ አለበት። ለምሳሌ ቁጥራቸው በጣም ውሱንና ዘራቸው

---

* ይህ ማለት ግን ሰው የአካባቢ ኦክስጂን እንዳሻው ያድርግ ከሚል መደምደሚያ አያደርስም ። ለምሳሌ ከኢንዱስትሪ የሚወጣው ቆሻሻ አየሩን እንዳይበክልና በሰው ልጆች ላይ የተለያዩ በሽታዎች እንዳያስከትል መከላከል ተገቢና የሚቻል ርምጃ ነው ።

Digitized by Google

ከዓለም ሊጠፉ የተቃረቡ ብርቅ አራዊት ፣ አዕዋፍ ፣ ወዘተ . . . ሊጠበቁ ይገባል ። በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙና ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ የሆነ የዱር አራዊትንና አዕዋፍን መንከባከብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግዴታና መብት ነው ። እንደቁጥራቸው መጠን አንዳንዶቹን ከማደን መቆጠብ አስፈላጊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አለ ።

ሰው በአንዳንድ የተፈጥሮ ሀብቶች ከመጠቀም መቆጠብ ያለበት ለራሱ ህውልናና ደስታ ፣ እንዲሁም ለትውልድ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው ። ሰው ተፈጥሮን መንከባከቡ ለራሱ ጥቅም ፣ ለኑሮውና ለዕድገቱ ማሰብ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። አካባቢን መንከባከብና ማሻሻል ሲባል በመሠረቱ «ሰውን መንከባከብ »[6] ማለት ነው። በአጭሩ ተፈጥሮ የሰው ህልውና እስከ ሆነች ድረስ ካርል ማርክስ እንዳለው «የሰው ግዑዝ አካል ናት ፤»[7] እሷንም መንከባከብ ማለት በእርግጥም ሰውን እራሱን መንከባከብ ማለት ነው ።

ተፈጥሮን መንከባከብና ማሻሻል በመሠረቱ የሰውን ህልውና መጠበቅና ማስከበር ከሆነ ፣ ሰውም ለመኖር የግዴታ በተፈጥሮ መጠቀም ፣ ተፈጥሮን መግራት ፣ በተፈጥሮ ላይ ተፅዕና ማሳደር ያለበት ከሆነ ፣ በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለው ቅራኔና ከዚሁ የሚመነጨው ችግር ሰው እስካለ ድረስ ይኖራል ማለት ነው ። «የሰውና የተፈጥሮ ቅራኔ በሥራ ሂደት ውስጥ ያለማቋረጥ የሚፈታና ያለማቋረጥ የሚፈጠር ነው ።»[8] በመሆኑም «የሰውና የተፈጥሮ ግጭት ለአንዴና ለመጨረሻ መፍትሔ የሚያገኝ አይደለም ። ምክንያቱም ይህ ቅራኔ ጊዜያዊ ወይም አላፊ አይደለም . . . »[9] የግጭቱ ምንጭ የሰው ልጅ ህልውናውን ለመጠበቅ ፣ ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮችን እንደምግብ ፣ መጠለያና የመሳሰሉትን ለማግኘት የግዴታ የሚያካሂደው ሥራ ነው ። ሥራ በማንኛውም ኅብረተሰብ ያለና ምን ጊዜም የሰውና የተፈጥሮ ቅራኔ መገለጫ ነው ። ይኸው ቅራኔ መፍትሔ የሚያገኘውም በዚሁ ሂደት ነው ።

በሰውና በተፈጥሮ መካከል ያለው ትግል መፍትሔ አገኘ ማለትም በኅብረተሰብና በተፈጥሮ መካከል የሚከሰተውን ቅራኔ ኅብረተሰቡ ለመቆጣጠር ፣ ተፈጥሮ የሚያደርስበትን ወይም ሊያደርስበት የሚችለውን ጉጂ ተፅዕኖ ለመቋቋም መቻሉን ያመለክታል ። ማንኛውም ኅብረተሰብ ከችግር እየተላቀቀ በዕድገት ሊራመድ የሚችለው በዚህ ግንዛቤ ላይ በመመሥረት ተገቢውን ጥረት ሲያደርግ ነው ። ማኅበራዊ ዕድገት በተአምር አይገኝም ።

ይህ ሐቅና ቲጨባጭነት ያለው መፍትሔ ለአብዛኛው የሀገራችን ሠርቶ አደር ሕዝብ ግልጽ ሳይሆን ወይም ትክክለኛ ግንዛቤ ሳያገኝ ቆይቷል ። ለዚህም ሁኔታ ኋላቀርነትና ጭፍን እምነቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በእርሱና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ግንኙነት በትክክል በመረዳት ፣ ጥረቱ ያለውን ወሳኝነት በመገንዘብ ጠንክሮ በመታገል ፋንታ ተአምራዊ መፍትሔ በመጠበቅ ለጉዳት ተጋልጧል ።

በኅብረተሰብና በተፈጥሮ መካከል ያለው ቅራኔ መፍትሔ የሚያገኘው ስለተጨባጪ እውነታ ትክክለኛ ዕውቀት ኖሮ በ ዚ ሁ ላይ በመመርኮዝ በሚካሄድ ትግል ብቻ ነው ። በተለይም ፍትሕና የጋራ ብልጽግና የሠፈነበት ኅብረተሰብ ለመገንባት የሚቻለው በዝባዥ መደቦችን በማስወገድና የምርት ኃይሎችን በማሳደግ ፣ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን በመመሥረት ፣ የኅብረተሰቡን አስተዳደር በዕቅድ በመምራትና ሕዝባዊ ተሳትፎን ከፍ በማድረግ ነው ። በዚህ መሠረት ከኋላቀርነት በመላቀቅ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ መመሥረትን ዓላማው ያደረገው የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ስለችግሩ ትክክለኛ ዕውቀት ከመጨበጥ አንሥቶ ተገቢውን የሥራ እንቅስቃሴ እስከ

Digitized by Google

ማድረግ ድረስ ምን ያህል ብቁነት እንደሚጠበቅበት የተሠወረ አይደለም ። ለዚህም ዛሬ በአገራችን ምቹ ሁኔታ አለ ።

የገጠሩ ሁኔታ

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ መሬት ፣ ደን ፣ ውሃና ሌላውም የተፈጥሮ ሀብት የሕዝብ ነው ። በዚህም ምክንያት ግለሰቦች ይህን ሀብት በቁጥጥራቸው ሥር በማድረግና በመበዝበዝ የኅብረተሰቡንና የተፈጥሮን ችግር የሚያባብሱበት ሁኔታ በአያሌው ተወግዷል ። የሀገሪቱን ዕድገት በሥርዓት ለመምራት ጥረት እየተደረገ ነው ። በዚሁ መሠረት ከ1971—1976 የአንዳንድ ዓመት የምርት ዕድገት ዘመቻ ዕቅዶች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል ። የዕቅዶቹም ዋና ዋና ዓላማዎች አጣዳፊ ማኅበራዊ ችግሮችን ማቃለል ፣ የኢኮኖሚውን ዕድገት ማፋጠንና ለሶሻሊዝም ግንባታ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት መጣል ነበር ። ከስድስቱ የምርት ዘመቻ ዓመታት በኋላ የአሥር ዓመት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ ከ1977 ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ነው ።

የመሪ ዕቅዱ መሠረታዊ ግብ ዛሬ ሀገሪቱ የምታካሂደውን ዲሞክራሲያዊ አብዮት እያጠናቀቁ ለሶሻሊዝም ግንባታ ጠንካራ መሠረት መፍጠር ነው ። ይህ ዕቅድ ከሚያጠቃልላቸው ዓላማዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ ። [10]

1. የምርት ኃይሎችን ዕድገት በማፋጠን የኢኮኖሚውን የማምረት ችሎታ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ፤
2. የሀገሪቷን የተፈጥሮ ሀብት ለምሳሌ አፈርን ፣ ውሃን ፣ እንስሳትን ማልማትና መጠቀም ፤
3. ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ማስፋፋትና ማጠናከር ፤

ዕቅዶችን በተግባር ለመተርጐም ስልቶች የተቀየሱ ሲሆን ከነዚህም መካከል ፡—

1. የሰፊውን ሕዝብ የምግብ ፍላጎት ለማሟላት በአጠቃላይ በምግብ በ ኩ ል ራስን ለመቻል የግብርና ምርትን ማሳደግ ፤
2. የገጠሪቱን ኢትዮጵያ የልማት እንቅስቃሴ በተዋሐደ የገጠር ልማት ስልት መሠረት መምራት ፤
3. ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን መምረጥ ፣ መጠቀም ፣ ማዳበርና ማመንጨት እንዲሁም የምርምር ዓቅምን መገንባትና በአጠቃላይ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት መሠረት መጣል ፤
4. መንግሥታዊ ድርጅቶችን እንዲሁም የአምራቾችንና የአገልግሎት ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማስፋፋትና በማጠናከር ለሶሻሊስት ይዞታው መጠናከር አመቺ ሁኔታዎችን በተከታታይ መፍጠር [11] የሚሉ ይገኛሉ ።

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ጐልቶ የሚታየውን የኅብረተሰብና የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ለመፍታት ፣ ለዚህ ችግር ሕዝቡን ያጋለጠውን ኋላቀር ሁኔታ ለመለወጥ ወሳኙ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የፖለቲካ የበላይነት አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ማረጋገጥ ፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የምርት ኃይሎችን ዕድገት ማፋጠንን ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ማስፋፋት ነው ።

ግብርና 85 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የሚተዳደርበት ፣ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ከ48 በመቶ በላይ የሚገኝበትና ሀገሪቷ ለውጭ ገበያ ለምታቀርበው ምርት 90 በመቶ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው ። የወደፊቱም የሀገሪቷ የኢኮኖሚ ዕድገት በዚሁ መሻሻልና ውጤታማነት የሚወሰን ነው። ስለዚህም በዕድገት ትልሞችን ውስጥ የተለየ ትኩረትና ቅድሚያ ተሰጥቶታል ። ይሁን እንጂ ክፍለ ኢኮኖሚው ኋላቀር የም

Digitized by Google

ርት ግንኙነቶች የሰፈኑበትና በአመዛኙ
ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ የራቀ ነው ። በሀገሪቱ
ውስጥ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ማስፋ
ፋትን ዓላማቸው አድርገው ከሚታገሉ
ሕዝባዊ ኃይላት ውስጥ የሚጠቃለሉት የገ
በሬ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት
አባላት ከጠቅላላው ገበሬ ውስጥ ከአንድ
በመቶ አይበልጡም ።[12] ለሀገሪቱም ብሔ
ራዊ ምርት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦም
ብዛታቸውን ከሚያመለክተው አኃዝ የሚ
ርቅ አይደለም ።

በአንፃሩ በግል የሚያመርቱት ገበሬ
ዎች ከጠቅላላው የግብርና ምርት ከ94
በመቶ በላይ የሚያስገኙ ቢሆኑም ፤ በሰፋፊ
የጋራ ይዞታ ላይ በዘመናዊ የአመራረት ዘዴ
ዎች በመጠቀም ከፍተኛ ውጤት ለማስገ
ኘት ከሚያስችላቸው አደረጃጀት ውጭ
ናቸው ።በዚህ መሠረት ያለ ችሎታና አቅም
ማቀናጀትን የሚጠይቀውን የተፈጥሮ ችግ
ርን በአስተማማኝ ለማስወገድ ሠርቶ አደሩ
ሕዝብ ቀላል ሁኔታ ላይ እንደማይገኝ ግልጽ
ነው ። ሆኖም የምርት ኃይሎችን ዕድገት
ለማፋጠን ምርትን ለማሳደግና አንገብጋቢ
ችግሮችን በተለይም የምግብ እጥረትን ለማ
ስወገድ እያደርም የሶሻሊስ የምርት ግንኙነ
ትን ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታ መኖሩ መዘን
ጋት የለበትም ። በዚህ ረገድ በተለይም
የልዩ ልዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች መኖር ጠቃ
ሚ መንደርደሪያ ነው ። ከሞላ ጐደል በመላ
አገሪቱ ገጠር የተደራጁት የገበሬ ማኅበ
ራት የዲሞክራሲ መብት መግለጫ መድረ
ኮች ከመሆናቸውም ሌላ የምርት ኃይሎ
ችን ዕድገት ያፋጥናሉ ። በቀጥታም ሆነ
በተዘዋዋሪ ለሶሻሊዝም ምሥረታ አስተዋ
ጽኦ ያደርጋሉ ። የአገልግሎት የኅብረት
ሥራ ማኅበራትን በማስገኘት ለጋራ ጥቅም
መዳበር ድርሻ ያበረክታሉ ። ለአምራቾች
የኅብረት ሥራ ማኅበራት መቋቋም ድጋፍ
በመስጠት ለሶሻሊዝም ዓላማ ተግባራዊ
ነት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ ። ከዚህ አኳያ
የገበሬ ማኅበራት ያላቸውን ሚና በሚመለ

ከት የግብርና ሚኒስቴር በ1977 ባወጣው
አንድ ጽሑፍ የሚከተለውን አሥፍሯል ።

የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት የገጠርን መሬ
ት የሕዝብ ያደረገውን አዋጅ ተግባራዊ
ማድረግን መሠረት አድርገው ይነሱ እንጂ
በተከታታይ ለተቋቋሙትና ለሚቋቋሙት
ማኅበራት ማለትም ለአገልግሎትና ለአም
ራቾች የኅብረት ሥራ ጥሩ መንደርደሪያና
መረማመጃ ናቸው ። አርሶአደሮች የድርጅ
ትና የትግል ልምድ የሚቀስሙበት ፣ የጋራ
ችግሮች በወል ጥረት መፍትሔ ማገኘት
እንደሚቻል የሚማሩበት ፣ ራሳቸውን በራ
ሳቸው በማስተዳደር በሶሻልና በፖለቲካ
ውስጥ ተሳትፎአቸውን የሚያዳብሩበት የመ
ጀመሪያው ትምህርት ቤታቸው የቀበሌ
ገበሬ ማኅበር ነው ።

የቀበሌ የገበሬ ማኅበራትን መሠረት
በማድረግ የሚቋቋሙት የአገልግሎት የኅብ
ረት ሥራ ማኅበራት ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊ
ና ማኅበራዊ ተግባሮችን በማከናወን ተጨ
ባጭ ጠቀሜታ በማስገኘት ላይ ናቸው ።
ለገበሬው የተሻሻሉ የምርት መሣሪያዎችና
ምርጥ ዘሮች በማቅረብ ፣ የገበሬዎችን
የጋራ ካፒታል በማዳበር ፣ የመዋዕለ ንዋይ
አቅምን በማሳደግ ወዘተ የማይናቅ አስተ
ዋጽኦ ያደርጋሉ ። ለአምራቾች የኅብረት
ሥራ ማኅበራትም አቅም በፈቀደ መጠን
ብድርና ሌሎችንም ድጋፎች ይሰጣሉ ።
የገበሬዎች የአገልግሎት የኅብረት ሥራ
ማኅበራት በሠርቶ አደሩ ጥቅም አንፃር ከተ
መሩና በዚሁ አኳያ ከተጠናከሩ የኢትዮ
ጵያ አርሶአደሮች የገጠማቸውን የዕድገት
ችግር ለማቃለልና የምርት ኃይሎችን ዕድ
ገት ለማፋጠን የሚያግዙ ናቸው ።

በኢትዮጵያ ኋላ ቀርነትንና በአመዛኙ
ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመጣውን የተፈጥሮ
አደጋ ለማስወገድ ፣ በአጠቃላይ ማኅበራዊ
የዕድገትን ለማፋጠን ይቻል ዘንድ ዕቅድ
ከፍተኛ ሚና እንዳለው የታመነ ነው ።ይሁ
ን እንጂ ዕቅድ ማውጣት በራሱ የአንድን

Digitized by Google

አገር የለውጥ ሂደት ከግብ አያደርስም ። ማቀድ ራሱ ውስብስብና በቀላሉ የማይታይ ቢሆንም ዋናውና ወሳኙ ዕቅዱን በተግባር መተርጐሙ ነው ።

ከ1971 ጀምሮ በተካሔዱት በዘመቻ ዓመታት ቅድሚያ ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ የግብርና ክፍለ ኤኮኖሚን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ነበር ። ከዚህ አንፃር በተለይ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ዕድገት የታየ ሲሆን ፣ ይህ አዝማሚያ በተለይ በተፈጥሮ ችግር ምክንያት በተፈለገው መልክ ሊቀጥል አልቻለም ። ሆኖም በዚሁ ጊዜ ውስጥ የተገኘው በዕቅድ ለመሥራት ጥረት የማድረግ ልምድ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

የተፈጥሮ ችግር በልማት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ባያጠያይቅም እንቅፋትነቱ አንፃራዊ ነው ። ምክንያቱም ችግሩ የደረሰበትን ወገን ለመቋቋም ያለው አቅም ሚና አለው ። ይህም በአመዛኙ በሥራ መገልገያ ዓይነት የሚገለጥ ነው ።

የምርት ኃይሎች

በአንድ በኩል ሰውና ሥራው ፣ በሌላ በኩል ተፈጥሮና ሀብቷ ሆነው የሚካሄደው የምርት በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ በዝርዝር ሲታይ ሦስት አካላት (elements) አሉት ። እርነሱም አንደኛ ፣ ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ፣ ድርጊቱን የሚያዘው አካል ወይም ሠርቶ አደሩ ፣ ሁለተኛ ፣ የሥራ ተገብሮ (ሥራ የሚካሔድበት አካል) ሦስተኛ ፣ የሥራ መገልገያዎች ናቸው ።

ሦስቱ የምርት ሂደት አካላት በሰውና በተፈጥሮ ግንኙነት አንፃር ሲታዩ የተለያዩ ሚናዎች አሏቸው ። የሥራ ተገብሮዎች ድርጊቱ የሚፈጸምባቸው ፣ የሚከናወንባቸው ነገሮች ናቸው ። የሥራ ተገብሮዎች ኅብረተሰቡ በምርት ክንውን ውስጥ የሚጠቀምባቸውን የተፈጥሮ ሀብት ዓይነት ወይም ባሕርያት የሚያሳዩ ሲሆኑ ፣ ኅብረተሰብ ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ያለውን የኃይል ወይም የዕውቀት ደረጃ ግን አያሳዩም ።

ለምሳሌ በቆሎ የሚዘራበት መሬት የገበሬዎች በቆሎ ማምረቻ ማሳ መሆኑ እንጂ ገበሬዎቹ ማሳውን ምን ያህል እንደሚቆጣጠሩት በምን ያህል ምርታማና ቀልጣፋ የሥራ ደረጃ እንደሚጠቀሙበት አያሳይም ። ይህን የሚያሳየው የሥራ መገልገያ ነው ። ለምሳሌ የበቆሎው ማሳ ፣ እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ኅብረተሰብ በሾለ እንጨት ወይም በአንካሴ ፣ ከዚህም በተሻለ ኅብረተሰብ በእንስሳ በሚጐተት ማረሻ ፣ በዘመናዊ ኅብረተሰብ ደግሞ በትራክተር ታርሶ ሊዘራ ይችላል ። በእነዚህ በተለያዩ የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃዎች የማሳው መታረስ በራሱ የሚያሳየው ኅብረተሰቦቹ በማሳ መጠቀማቸውን ወይም ለመጠቀም መቻላቸውን ሲሆን የሥራ መገልገያዎቹ ግን ኅብረተሰቦቹ ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የሚጠቀሙባቸውን ማምረቻዎች ፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የዕድገት ደረጃቸውን ፣ ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ያላቸውን አቅምና ችሎታ ያሳያሉ ።

ካርል ማርክስ እንዳለው «ተፈጥሮ ማሽኖችን ወይም ሐዲዶችን ፣ የኤሌክትሪክ ቴሌግራፍን ፣ ወዘተ . . . ወይም ሌሎች የሥራ መገልገያዎችን አታመርትም ።»[13]

እነዚህ የሥራ መገልገያዎች ፣ ሰው ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ፣ ፍላጐቱን ለማርካት በማሰብ በእጁ በመሥራት ዕውቀቱን ወደ ቁሳዊ ኃይል የለወጠባቸው ነገሮች ናቸው። ስለሆነም መሣሪያዎች በኅብረተሰብ ዕውቀት ተሠርተው የሠራቸውን ኅብረተሰብ ዕውቀት ፣ ኅብረተሰቡ በተፈጥሮ ላይ ያለውን የበላይነት ደረጃ የሚያሳዩ ናቸው ።[14] «የሥራ መገልገያዎች በኅብረተሰብና በተፈጥሮ ግንኙነት ውስጥ የሰብአዊ ኃይል መመዘኛ ፣ የማኅበራዊ ዕድገት መለኪያ ናቸው ።»[15]

በመገልገያዎች ዕድገት አንፃር የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በምን ደረጃ ላይ ናቸው?

Digitized by Google

በሌላ አነጋገር ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ያላቸው ችሎታ ምን ያህል ነው ?

የአገራችን አርሶ አደሮች በአመዛኙ በፊውዳሊዝም ቀንበር ሥር ለዘመናት ሲመዘበሩ የኖሩ እንደመሆናቸው የሥራ መገልገያዎቻቸው በጣም ኋላቀር መሆናቸው ግልጽ ነው ። በብዙ ታዳጊ ሀገሮች ካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነት በመጠኑም ቢሆን በመስፋፋቱ የገጠር ኤኮኖሚ ዘርፍ የቅድመ ካፒታሊስት የምርት ግንኙነቶች (የፊውዳል ፣ የጋርዮሽ ፣ ወዘተ) የሥራ መገልገያዎችን እስከተወሰነ ደረጃ ቢሆንም በካፒታሊስታዊ የሥራ መገልገያዎች ተተክተዋል ። ቅድመአብዮት ኢትዮጵያ ግን በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ እጅግ ወደኋላ የቀረ የምርት ግንኙነት የበላይነት ከያዘባቸው ጥቂት ሀገሮች አንዷ ነበረች ። በዚች ሀገር የካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነት መስፋፋትና ከዚህም ጋር ተያይዞው የሚመጡት የሥራ መገልገያዎች ለምሳሌ ትራክተር ፣ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር በጣም ውሱን ናቸው ።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በገጠሩ የኢኮኖሚ መዋቅር ውስጥ አመዛኙን ድርሻ የያዙት ቅድመ ካፒታሊስታዊ በተለይም ፊውዳላዊ የምርት ግንኙነቶች ነበሩ ። በአብዮቱ ውስጥ ግን ፊውዳል የምርት ግንኙነት ከመሠረቱ ፈራርሷል ። ለአርሶ አደሩ የሥራ መገልገያዎችም አመች የዕድገት ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል ። ሆኖም በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ተፅዕኖዎች ምክንያት ገና መሠረታዊ ለውጥ አላሳዩም ። አርሶ አደሮች ለምርት ተግባር በአመዛኙ የሚጠቀሙት በራሳቸው የሥራ ኃይልና በበሮቻቸው ጉልበት ነው ። ሌሎችም የሥራ መገልገያዎቻቸው ገና አልተለወጡም።

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ችግር ፣ የሚጠቀሙባቸው የተግባር መገልገያዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አንፃር ሲታዩ ኋላቀር መሆናቸው ብቻ አይደለም ። ችግሩ እነዚሁ ኋላቀር መጣሪያዎች ራሳቸው እጅግ ውሱን መሆናቸውም ነው ። ለምሳሌ ብዙ የአገራችን አርሶ አደሮች ለእርሻ ሥራ በበሬ ይጠቀማሉ ። ነገር ግን በቂ የበሬ ይዞታ አይታይም ። ይህንን ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል ።

የእርሻ በሬ ይዞታ ፤

ከጠቅላላ ገበሬዎች መካከል	አማካይ ይዞታ
37.7	0
32.0	1
24.5.	2
5.7	3
2.0	4

ምንጭ ፦ በኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊ.ወ.መ. የግብርና ሚ/ር

ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ከገበሬዎች 37.7 በመቶ ምንም በሬ የሌላቸው ሲሆን ፣ 32.0 በመቶ የሚሆኑት አንዳንድ በሬ ብቻ ነው ያላቸው ። በኢትዮጵያ አርሶአደሮች ዘንድ እስከ ዛሬ ጉልቶ በሚታየው የአስተራረስ ዘዴ አንድ ገበሬ በሁለት በሮች ነው የሚያርሰው ። ስለሆነም 32 ከመቶ የሚሆኑት ባለ አንዳንድ በሬዎች ቢያቀናጅ ማግሾቹ ማለትም 16 ከመቶ የሚሆኑት በሬ በሌላቸው ገበሬዎች ውስጥ የሚመደቡ ይሆናሉ ። በዚህ መሠረት ከኢትዮጵያ ገበሬዎች 54 ከመቶ (37.7+16) አካባቢ የሚሆኑት የሚያርሱበት በሬ የላቸውም ለማለት ይቻላል ። በሌላ አነጋገር ፣ ባላቸው ዓቅም ተፈጥሮን ለማሸነፍ ለመግራትና የሚፈልጉትን ምርት ለማግኘት የሚያስችላቸው በእርሻ ሥራ እጅግ ተፈላጊ የሥራ መገልገያ የላቸውም።

በበቂ መረጃዎች አለመገኘት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የበሬዎችን እጥረት በትክክል ለማወቅ ያስቸግራል ቢባልም ዛሬ በአገራችን ከሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲታይ ከላይ የቀረበው ማስረጃ እምብዛም አከራካሪ አይሆንም ። ይልቁንም በተደጋጋሚ የደረሰው ድርቅ ባስከተለው የመኖ

Digitized by Google

እጥረት ወይም በአንዳንድ አካባቢ ከነጭ
ራሹ መታጣት ምክንያት ያሉትም በሮች
ለማረስ በቂ ጉልበት እላቸው ለማለት ያስ
ቸግራል ። ይህ ሁኔታ ድርቅ ከፉኛ ባጠ
ቃው የአገራችን ሰሜናዊ ክፍል በጉልህ
እንደሚታይ አያጠያይቅም ።

በሬ ለሌለው አርሶአደር አማራጩ በዶ
ማና በመሳሰለው የእጅ መሣሪያ መቆፈር
ነው ። እያሌ አርሶአደሮች በእነዚህ የሥራ
መገልገያዎች እንደሚጠቀሙም በተግባር
የሚታይ ነው ። ባለው የመረጃዎች ችግር
ምክንያት የመገልገያዎቹን መጠን በትክ
ክል ለማወቅ ባይቻልም አርሶአደሩ የእነ
ዚህ መሣሪያዎች እጥረትም እንዳለበት ይገ
መታል ።

በአምስቱ የዘመቻ ዓመታት መርሐ ግብር
መሠረት የእርሻ መሣሪያዎችን ለአርሶ አ
ደሩ ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል ። ከ1977
ጀምሮም የአርሶአደሩ የእጅ መሣሪያዎችን
ለምሳሌ ዶማ ፣ ድጅና ፣ ማጭድና የመሳሰ
ሉትን በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በማ
ምረትና ከውጭ ሀገር በመግዛት ለአርሶአ
ደሩ ቀርበዋል ። እንዲሁም ትክራተሮችን
በናዝሬት የትራክተር መገጣጠሚያ ጣቢያ
በማዘጋጀት፣ከውጭ ሀገር በመግዛትና በመ
ንግሥት እርሻዎች ላይ የተሠማሩትን በመ
ቀነስ የሠፋሪ አርሶአደሮች ማሳ በወቅቱ
እንዲታረስና እንዲዘራ ተደርጓል ። ለወደፊ
ቱም የትራክተር አገልግሎት ጣቢያዎችን
በማስፋፋት አርሶአደሩ የገጠመውን የሥራ
መገልገያዎች እጥረት ለመቋቋም ጥረት
እየተደረገ ነው ።

በኢትዮጵያ አርሰአደሮች ዘንድ እጥረትና
አጠቃቀማቸው ጉልቶ የሚታየው ሌሎቹ
መገልገያዎች ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ናቸው።
በ1977 ከተጠናቀረው መረጃ መገንዘብ እን
ደሚቻለው በማዳበሪያ የሚጠቀሙት ከጠ
ቅላላው አርሶአደር 4 በመቶ ብቻ ናቸው። [16]
በተጨማሪም ይጠቀማሉ የሚባሉትም አር
ሶአደሮች በአማካይ የተጠቀሙት ማዳበሪያ
መጠን በጣም ዝቅተኛ ነው ። በጥቅም ላይ
ይውላል የሚባለውም ከፍተኛ የአጠቃቀም
ብኩንነት ያለበት መሆኑን ብዙ ዘገባዎች
ያመለክታሉ ። ምርጥ ዘርንም በሚመለከት
ሁኔታው እምብዛም የተለየ አይደለም ።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የእርሻ ሥራ መገል
ገያዎች ኋላቀርነትና እጥረት አርሶአደሩ
ከተፈጥሮ ጋር ባለው ግንኙነት ምን ያህል
ጥገኛና ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ያለው ዓቅም
እጅግ በጣም ውሱን መሆኑን ያመለክታል።
አርሶአደሩ ያጋጠመውን የአካባቢ ችግር
እልባት ለመስጠት ፣ ተፈጥሮን በቁጥጥሩ
ሥር ለማድረግ ሲታቀድ መጤን ከሚገባ
ቸው መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ
የሥራ መገልገያዎች መሆን ይኖርበታል ።
ሌላው ትኩረት የሚያስፈልገው ጉዳይ የአ
ርሶ አደሩን የመሥራት ኃይል ፣ የዕውቀት
ደረጃና ልምድ ከፍ የማድረግ ጥያቄ ነው።

በኅብረተሰቡና በተፈጥሮ ግንኙነት ውስጥ
የሥራ መገልገያዎች ኅብረተሰቡ ተፈጥሮን
ለመቆጣጠር ያለውን ችሎታ ያመለክታሉ
ሲባል እነሱን የሚሠራው ፣ የሚያንቀሳቅ
ሰውና የሚጠቀምባቸው ሰብአዊ አምራች
ኃይል መታወስ አለበት ። በገጠሪቱ ኢትዮ
ጵያ ሞፈር ፣ ቀንበር ፣ ማረሻ ፣ ዶማ ፣ ማዳበ
ሪያ ፣ የተባይ መከላከያ ፣ ትራክተር ወዘተ
አርሶአደሩ ካላንቀሳቀሳቸውና ካልተጠቀመ
ባቸው በስተቀር በራሳቸው ከሱ ውጭ በተ
ፈጥሮ ላይ ኃይል የላቸውም ። እነዚህ የተ
ግባር መገልገያዎች በሰውና በተፈጥሮ ግን
ኙነት ውስጥ ኃይል የሚሆኑት ፣ ተፈጥሮን
ለመግራት የሚያገለግሉትና ኅብረተሰብ
በተፈጥሮ ላይ ያለውን የግዛዝ ደረጃ የሚያ
መለክቱት አርሶአደሩ ሲገለገልባቸው ነው።
ስለዚህ በእርሻ ምርት ውስጥ ፣ ዋነኛው አር
ሶአደሩ ፣ የእርሱ ዕውቀትና ልምድ ነው ።

በአጠቃላይ አነጋገር «የምርት ኃይሎች
ሰው ፣ ኅብረተሰብ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን
ግንኙነት ይገልጻሉ ። የእነርሱ የዕድገት
ደረጃ ሰው ተፈጥሮን ምን ያህል እንደሚ

Digitized by Google

ቆጣጠር ያሳያል ፡፡» [17] ይህ በአርሶአደሩና በተፈጥሮ መስተጋብር አንፃር ሲታይ አርሶአደሩ ያለው ዕውቀትና ልምድ እንዲሁም የሚያንቀሳቅሳቸው የእርሻ መሣሪያዎች አርሶአደሩ ተፈጥሮን ምን ያህል እንደተቆጣጠረ ወይም እንደሚቆጣጠር ያሳያሉ ፡፡

የኢትዮጵያ አርሶአደር ለብዙ ዓመታት ከዕውቀት ፋና ፣ ከሙያ ትምህርት ርቆ የኖረ ለፖለቲካ ጭቆናና ለኢኮኖሚ ብዝበዛ የተጋለጠ ስለነበር እስከ አብዮቱ መቀጣጠል ድረስ ዕውቀቱን ለማሻሻልና ብሎም ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የሚያስችሉት አመቺ ሁኔታዎች አላገኘም ነበር ፡፡ በአብዮቱ ማግ በልዩ ልዩ ማኅበራት እየተደራጀ ፣ ከማይምነት እየተላቀቀ ፣ በጋራ ለማምረት የሚያስችለውን ሁኔታ እየገነባ ፣ ይህንንም ዓቅሙን የበለጠ ለማዳበርና በአሸናፊነት ለመውጣት ዋስትና የሆነውን ፖለቲካዊ ተሳትፎን ከፍ እያደረገ ፣ የመብቱንና የነፃነቱን አድማስ እያሰፋ በመሔድ ላይ ይገኛል ፡፡

በሙያ ሥልጠናው ረገድ በስድስቱ የዘመቻ ዓመታት በሥራ አመራርና በሒሳብ አያያዝ ከአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት 38, 052 ፣ ከአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት 74,998 አርሶ አደሮች ሠልጥነዋል ፡፡ በእነዚሁ ዓመታት «በሌሎች ሙያ ነክ በሆኑ የግብርና ሥራዎች ማለትም በአዝርእት ፣ በእንስሳትና በተፈጥሮ ሀብት ልማትና በኑሮ ዘዴ . . . ቁጥራቸው 286,358 አርሶአደሮች ትምህርት አግኝተዋል ፡፡» [18] ከዚህም በተጨማሪ አርሶአደሩን በዕለት ተዕለት የምርት ሥራው ለመርዳት አያሌ የእርሻ ባለሙያዎች ወደገጠሩ በየጊዜው እንዲሠማሩ እየተደረገ ነው

የአገራችን ኢኮኖሚ ዋልታ በሆነው በግብርናው ዘርፍ ተፈላጊውን ዕድገት ለማስገኘት በሥልጠናና በሙያ ማስፋፋት ረገድ ልዩ ልዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው ፡፡ በአጋርፋ (ባሌ) ሁለገብ የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማዕከል ተከፍቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን ፣ በአርዳይታ (አርሲ) የተከፈተው የካቲት 25 የኅብረት ሥራ ኢኒስቲትዩትም ከፍተኛ የኅብረት ሥራ ባለሙያዎችን ለማፍራት በተወሰነ ደረጃ ሥራውን ጀምሯል ፡፡ በከፍተኛ ደረጃ የእርሻ ምሁራንን ለማፍራትም የዓለማያ የእርሻ ኮሌጅ ከዚህ ዓመት ጀምሮ በዩኒበርስቲ ደረጃ አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር ተደርጓል ፡፡ የደብረ ዘይት የእንስሳት ሕክምና ባለሙያዎች ማሠልጠኛ ተቋም በዚህ ዓመት በዶክትሬት ደረጃ ማስመረቅ እንደሚጀምር ይጠበቃል ፡፡

አርሶአደሩ ምንም እንኳን በትምህርት ያልገፋና ያለውም የሥራ መገልገያ በጣም ውሱን ቢሆንም በሚገባ ከተንቀሳቀሰና ያለውን ኃይሉን ካስተባበረ የገጠመውን የተፈጥሮ ችግር ለማስወገድና ዕድገቱን ለሐፋጠን ከፍተኛ ኃይል መሆኑ እሙን ነው ፡፡ ለዚህም እጅግ የተባባሰውን ድርቅ ለመቋቋም ኢሠፓ የቀየሰውን የድርጊት ፕሮግራም በተግባር በመተርጐም ረገድ በየአቅጣጫው የሚያሳየውን ሰፊ እንቅስቃሴ መመልከቱ በቂ ነው ፡፡

በኢትዮጵያ የአካባቢ ችግር ጐልቶ የሚታይበት ዋንኛ መድረክ የሆነው የአርሶአደሮች የእርሻ ሥራ ከዚህ ዓይነቱ ኋላቀርነት ለመላቀቅ የሚችለው የሀገሪቱ ሠርቶአደሮች በአሁኑ ጊዜ ብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮቱን እያገባደዱ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነትን ለመመሥረት በሚያካሄዱት የትግል ሂደት ውስጥ ነው ፡፡ ወሳኙ ቁምነገር አርሶአደሩ ውስብስብ የተፈጥሮና የፖለቲካ ችግሮችን በመረዳትና ከሌሎች ሠርቶአደሮች ጋር በመተባበር በሠራተኛው መደብ ዓላማ እየተመራ ለእውነተኛ ነፃነት ለተሟላ ዕድገት የሚያደርገው ትግል ነው ፡፡ በዚህ መሠረት በድል ለመራመድ የቻለ እንደሆ ነው ዛሬ ካለበት የተፈጥሮ ጥገኝነት ለመላቀቅና ተፈጥሮን ተቆጣጥሮ ለጥቅሙ ለማዋል የሚችለው ፡፡

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘ ፣ ሐምሌ ፣ 1977 ።
2. አዲስ ዘመን ፣ ጥቅምት ፣ 1978 ፣ ገጽ 7 ።
3. ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዘርፍ ሪፖርት ፣ አዲስ አበባ ፣ የካቲት ፣ 1977 ፤ ገጽ 4 ። /ያል ታተመ/ ።
4. Karl Marx, *Capital*, Vol. 1 (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 179.
5. See, for example, E. Fedorov, *Man and Nature* (Moscow: Progress Publishers, 1980), p. 107.
6. I. Laptev, *The Planet of Reason* (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 214.
7. Karl Marx, *Economic and Philosophic Manuscripts of 1884*, 5th Rev. ed. (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 74.
8. I Laptev, p. 12.
9. *Ibid.*, pp. 10-11.
10. *የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ የማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ ፣ /1977—1986/ ፣* አዲስ አበባ ፣ መስከረም ፣ 1977 ፣ ገጽ 26—27 ።
11. ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 28—29 ።
12. የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዘርፍ ሪፖርት ፣ ገጽ 7 ።
13. Karl Marx, Quoted by I. Laptev, p. 16.
14. See, V. Kelle and M. Kovalson, *Historical Materialism*: An Outline of Marxist Theory of Society (Moscow: Progress Publishers, 1973), p. 51.
15. I. Laptev, p. 15.
16. ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘ ።
17. V. Kehle & M. Kovalson, p. 47.
18. ዜና የኢኮኖሚና የባህል ዕድገት ዘመቻ ፣ ቅጽ 4 ፣ ቁ. 19 ፣ 1977 ፣ ገጽ 7 ።

እ ር ማ ት

1. መስከረም ቅጽ 5 ፣ ቁጥር 22 ፣ ገጽ 12 ፣ ሁለተኛ ዓምድ 23ኛ መሥመር 70 ከመቶ የሚለው 60 ከመቶ ተብሎ ይነበብ ።
2. መስከረም ቅጽ 5 ፣ ቁጥር 22 ፣ ገጽ 29 ፣ አንደኛ ዓምድ ፣ ሰባተኛ መሥመር በምርት ኃይሎች የሚለው በምርት መሣሪያዎች ተብሎ ይነበብ ።

Digitized by Google

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ

ታረቀኝ አደቦ

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለምን የማስፋፋትን ተግባር በሁለት ደረጃዎች ለማየት ይቻላል ። የመጀመሪያው ደረጃ ሰፊው ሕዝብ የርዕዮተ ዓለሙን መሠረታዊ መርሆዎች ተቀብሎ በመደብ ትግሉ በመመሪያነት እንዲጠቀምባቸው በልዩ ልዩ የቅስቀሳ ስልቶች በሰፊው ማሠራጨትና ማዳረስ ይሆናል ።

ሁለተኛው ደረጃ የተሠራጨው ርዕዮተ ዓለም በአብዮታውያንና በሰፊው ሕ ዝ ብ አእምሮ በጥልቀት ሠርጾ አመለካከታቸውንና ግንዛቤያቸውን እንዲመራ ፣ ንቃተ ኀሊናቸውም በእርሱ እንዲቀረጽ የሕይወታቸው አጠቃላይ መመሪያ እንዲሆን የማድረግ ትግልን የሚመለከት ነው ። በእርግጥ ሁለቱም ሳይንሱን በስፋት የማሠራጨትና ጥልቀት እንዲኖረው የማድረግ ተግባሮች የማይነጣጠሉ ፣ ተደጋጋፊና ዲያሌክቲካዊ አንድነትም ያላቸው ናቸው ። ቢሆንም ተግባሩን በደረጃዎች ማየቱ በየወቅቱ ለሚቀየሱ ስልቶች ጠቃሚነት አለው ።

በአገራችን ሶሻሊዝም የአብዮቱ መመሪያ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም የሥርጭቱ ተግባር በይፋ እየተካሄደ ነው ። በተለይም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲን የማደራጀቱ ትግል በኢሠፓአኮ መከሰት እመርታ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይንስ የማስፋፋት ሥራ በዕቅድ ሲከናወን ቆይቷል ። በኢሠፓ መመሥረትም አዲስ ምዕራፍ ተከፍቶለታል ። ይሁንና ካለው ዓላማ ጋር ሲነፃፀር በመስኩ ገና ብዙ መሠራት እንዳለበት ግልጽ ነው ። ስለሆነም በተለያዩ ዘዴዎችና ደረጃዎች ሁኔታ በፈቀደ መጠን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም በፓርቲ አባላት ፣ በምሁራንና በሰፊው ሕዝብ አእምሮ በጥልቀት እንዲሠርጽ ከፍተኛ ጥረትና ተከታታይ ሥራ ያስፈልጋል ።

Digitized by Google

ከላይ በርእሱ የተጠቀሰው የማርክሳዊ-ሌኒናዊ ሥነ ዘዴን ግንዛቤ ማስፋፋት ወቅታዊና ለሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥረጽና ለኅብረተሰብ የግንባታ ተግባርም እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው ።

ስለማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትምህርት በአገራችን የሦስተኛ ደረጃ ተማሪዎች* ስላላቸው አስተያየት በአንድ ወቅት እንደሚከተለው ተዘግቧል ። «የማሌ ሳይንስ የሚጠናው በሳይንስነቱና በተግባር መመሪያ ነቱ» አይመስላቸውም ። ትምህርቱም «ደባል እንጂ ራሱን የቻለ አንድ የዕውቀት ምንጭ » መሆኑን አይገነዘቡም ። ከዚህ አባባል እንደምንረዳው አብዮታችን የሚመራበት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስና በንባብና በግንዛቤ ወይም በሥርጭት ደረጃም እንዲለመድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ነው ።

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ እንደ አንድ የትምህርት መስክ ብቻ የሚጠና ሳይሆን ለሌሎች የትምህርት መስኮችና ጥናቶችም መሪ የሆነ የግንዛቤና የምርምር ሥነ ዘዴ ነው ። የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ የሠራተኛው የመደብ ትግል መማሪያና የግንባታ መርህ ብቻ ሳይሆን የሳይንሳዊ ምርምር ሥነ ዘዴም ነው ። ስለሆነም ራሱ የሚጠና ሳይንስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሳይንሶች ቁሳዊና ማኅበራዊ ክስተቶች የማጥኛና የመገንዘቢያ መክፈቻ ነው ።

ሳይንሳዊ ዘዴ ለማንኛውም ሰው የግንዛቤ ጥራትና ተጨባጭነት ጠቃሚና አስፈላጊ ቢሆንም ፣ ይህ ጽሑፍ የሚያተኩረው በተለይ በሦስተኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች ፣ መምህራንና በምርምር ፣ በጥናትና በዕቅድ በተሠማሩ ምሁራን የግንዛቤ ዘዴ ላይ ነው ። ዋና ዓላማውም የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስን ሥነ ዘዴነት መግለጽ ሲሆን ፣ በይዘቱም የሥነ ዘዴን ትርጉምና ሚና ፣ ዕድገቱን ፣ ጠቀሜታውንና ወገናዊነቱን የሚመለከቱ ነጥቦችን ያቀፈ ነው ።

የሥነ ዘዴ ትርጉምና ሚና ፦—

ሥነ ዘዴ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በእንግሊዝኛ (methodology) የሚለውን ይወክላል ። ይህም በቀጥታ ሲተረጐም የዘዴ ዕውቀት ወይም በጥቅሉ ሳይንሳዊ ዘዴ (scientific method) የሚለውን ያመለክታል ።

ሥነ ዘዴ የማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና አንዱ ፈርጅና ከእርሱም ጋር ያደገ ሳይንስ ነው። ሰፋ ባለ ትርጉሙ የአንድን ተግባር ከንዋኔ አወቃቀር ፣ አመክንዮአዊ (logical) አደረጃጀት ፣ ዘዴና ሥልት ማጥናትን ይመለከታል ። [1] ጠበብ ባለ ትርጉሙም ሳይንሳዊ ዘዴን ማለትም ሳይንሳዊ ግንዛቤንና ዕውቀትን ለማጠናከር የምንከተለውን ሥነ ሥርዓትና ስልት ያመለክታል ።

የሥነ ዘዴ አንዱ ተግባር የግንዛቤን ፣ የዕውቀትን ወይም እውነታን የመረዳትን ሂደት በአግባብ ማደራጀትና በሥርዓት ማካሄድ ወይም አንድን ነገር ለመለወጥ በሚደረግ ትግል እንደተቆጣጣሪና መርህ ሆኖ ማገልገል ነው ። [2] ሳይንሳዊ ዘዴ ተፈጥሮንና ማኅበራዊ አካባቢን ለማጥናትና በትክክል ለመገንዘብ ፣ ለመለወጥና ለሰብአዊ ጠቀሜታ ለማዋል አስፈላጊ መማሪያ ነው ።

ሥነ ዘዴ ፍልስፍናን ፣ የተለያዩ ሳይንሶችን ንድፈ ሐሳቦችን ፣ ዘዴዎችንና ስልቶችን ያቅፋል ። [3] መሠረቱም ሳይንሳዊ ፍልስፍና ነው ። ሥነ ዘዴ የንጽረተ ዓለም (World outlook) አካል ነው ።

ስለ ሥነ ዘዴ ዕድገት አንዳንድ ነጥቦች

የግንዛቤን ሂደት በሚመለከት በሁለት አቀራረቦችና አመለካከቶች መካከል ትግል ሲካሄድ የቆየ ነው። እነዚህም ሐሳባዊና ቁስአካላዊ ዝንባሌዎች ናቸው ። በእነዚህ በሁለቱ መካከል ከጥንት ጀምሮ ትግል ሲደረግ የኖረ ቢሆንም ፣ የምርት ኃይሎች ዳብረው ሳይን

* ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ያሉ የትምህርት ተቋሞችን ያጠቃልላል ።

Digitized by Google

ስና ቴክኖሎጂ ሲስፋፉ የሐሳባዊነት ተፅዕኖ እየተዳከመ መጣ ።

የሐሳባዊነት አመለካከት ከቁስ አካል ንቃተ ኅሊናን የሚያስቀድም ፣ የተፈጥሮን፣ የማኅበራዊ ግንኙነትንና የንቃተ ኅሊናን ትንታኔ የሚያቀርበው በተጨባጭና በዲያሌክቲካዊ ግንኙነታቸው ሳይሆን በቁንጽልና ዲበአካላዊ [4] (metaphysical) በሆነ መንገድ ነው ። አስተሳሰብን (የአእምሮን ዓለም) ከአንጐል ማለትም ከዳበረ ቁስአካል ተግባር የተለየ ህልውና ያለው አድርጎ ያቀርባል። ነገር ግን ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ታሪካዊ ዕድገት ያለው ፣ ከምርት ተግባርና ልምድ ጋር ዲያሌክቲካዊ ትንጅት ያለው ፣ ከእርሱም ዕድገት ጋር አብሮ የዳበረ የአንጐል ሥራ ነው ።

በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት ሰዎች እርስ በርሳቸውና ከተፈጥሮ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ባልዳበረበት ወቅት በችግር ፣ በፍርሃትና በድንቁርና ኖረዋል ። አካባቢያቸውን በትክክል ስላልተረዱትና መረዳትም ስላልቻሉ የሚያዩት ነገር በልዩ ኃይል የሚገዛ ይመስላቸው ነበር ። የዝናብ አመጣጥ ፣ የወራት መለዋወጥ ፣ የዕፀዋት ዕድገት ፣ የሰውና የእንስሳት መራባትና የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሂደቶችና ክስተቶች ዕንቆቅልሽ ስለሆኑባቸው በደፈና «የመናፍሥት» ሥራ አድርገው ያዩዋቸው ነበር ።

የጥንት ሰዎች ተፈጥሮንና ኑሮአቸውን ከአንድ ከተፈጥሮ ውጭ በሆነ ኃያል ማዕከል እንደሚታዘዙና ከዚያ በሚመነጭ ሥርዓትም እንደሚገዛ ፣ ሁሉ ነገር ዕድሉና ሥፍራው አስቀድሞ እንደተወሰነ አድርገው ይመለከቱ ነበር ። በፊውዳላዊ አስተሳሰብ መሠረትም ሁሉ ነገር በተዋረድ የተዋቀረ ፣ ያለው ሁሉ ፍጹማዊ በሆነ አገዛዝና ደንብ ሥር የሚኖር ሰው ያላደረገው ሊለውጠውም የማይችል ፣ ተፈጥሮን መመራመርና ማወቅም ከሰዎች ችሎታ ውጭና ሊታወቅ የማይችል ምሥጢር ነው ። በዚህ ሁኔታ ከእውነታና ከሳይንስ ይልቅ ሥነ ተረት ፣ የተሳሳቱ እምነቶችና አመለካከቶች የበላይነት ነበራቸው ። እነዚህ ኢሳይንሳዊ አስተሳሰቦች በየዘመናቱ የበላይነት የነበራቸው የባሪያ አሳዳሪው ባሪያን ፣ ፊውዳሉ ጭሰኛውን ረግጠው እንዲገዙ መሣሪያ ሆነው አገልግለዋል ።

ፊውዳሊዝም ተንኮታኩቶ በካፒታሊዝም ሲተካ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲስፋፉ የላቁ አስተሳሰቦች አብረው ተከስተዋል ። ተፈጥሮንም የማደራጀትና የመቆጣጠሩ አድማስ እየሰፋ ሄዷል ። የቡርዧ አመለካከት በመሠረቱ በሐሳባዊነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ፣ የኅብረተሰብ እንቅስቃሴዎች በተናኮታዊ (mechanical) ግንኙነት የሚገዙ አድርጎ የሚያቀርብ ነበር ። ይህ የአመለካከት ዘዴ ፣ ምንም እንኳ የሳይንስ ዕድገት ውሱን የሆነውን የፊውዳላዊ ሥነ ልቡናና ንቃተ ኅሊና ገድግዳ አፈራርሶ የዕውቀትን አድማስ ያሰፋ ቢሆንም ክስተቶችን በተናጠልና በቅርፃቸው ማየት ፣ የዕውቀትን ተጨባጭነትና አንፃራዊነት አለመገንዘብ በጥቃቅንና ውጫዊ ነገሮች ማተኮር ዓይነተኛ ባሕርያቱ ነበሩ ።

በኅብረተሰብ ጥናት የቡርዧ አቀራረብ ክስተቶችን የሚረዳው በቅርጽና በቁንጽል እንጂ ውስጣዊ ግንኙነታቸውንና አንቀሳቃሽ የኅብረተሰብ ዕድገት ሕጎችን በመግለጽ አይደለም ። የኅብረተሰብን ዕድገት ታሪክ በነባራዊ ሕግጋት የሚገዛ ሳይሆን በማይታወቁና ሰው ሊረዳቸው በማይችል ሁኔታዎች ውስጥ እንደሚሄድ አድርጎ ያቀርባል ። የቡርዧ ታሪክ ተንታኞች የሰው የኑሮ ሁኔታ የሚወሰነው በተጨባጭ ሕግጋት ሳይሆን በማይታወቁና በማይታዩ አጋጣሚዎች (The play of the contingent and unforeseen) እንደሆነ አድርገው ያቀርባሉ ። የሰው ታሪክም ተከታታይና የተያያዘ ሳይሆን ጨርሶ ግንኙነት በሌላቸው የተለያዩ ሥልጣኔዎች የተገነባ ፣ አንቀሳቃሾቹም ጠቢብ መሪዎችና የየወቅቱ የገዥ

Digitized by Google

መደቦች እንደሆኑ አድርገው ያቀርባሉ። በዚህም የሰፊውን ሕዝብ ታሪክ ሠሪነት ይክዳሉ ።

በአጠቃላይ የቡርዧ ፍልስፍናና ማኅበራዊ ንድፈ ሐሳቦች ሁለንታዊ የሆነ ሥነ ዘዴ ሊያቀርቡ አልቻሉም ። ዛሬ በተለይ ካፒታሊዝም በአጠቃላይ ቀውስ ውስጥ በመሆኑ የዚህ ነፀብራቅ የሆኑ ፍልስፍናውም ሆነ ንድፈ ሐሳቦቹ በየወቅቱ የሚለዋወጡና ውጥንቅጣቸው የወጣ ሆነው ይገኛሉ ። መሠረታዊ መርሆዎቻቸውም ሆነ አጠቃላይ ንድፈ ሐሳባዊ መደምደሚያዎቻቸው በጽኑ ሳይንሳዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረቱ አይደሉም ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ የምርት ኃይሎች በበለጠ በማደጋቸውና ሳይንስና ቴክኖሎጂ በመስፋፋታቸው በንቃተ ኅሊናም ከፍተኛ እመርታ ተደረገ ። ዲያሌክቲካዊ ቁስአካላዊ ፍልስፍና [5] የተዋቀረው ታሪክንም ከዚሁ አንፃር መተንተን የተጀመረው በዚህ ወቅት ነው ። ለዚህ ፍልስፍና የወዝአደሩ መደብ ማደግና መደቡን የሚወክሉ ምሁራን መነሣት አስፈላጊውን ማኅበራዊ መሠረት ጥሎለታል ። ይህ ፍልስፍና ሰዎች ዓለምን ከራሱ ለመረዳትና ለማወቅ ፣ የዕውቀትንና የነፃነት አድማሳቸውን ለማስፋት ከኋላቀርነትና ከሐሳባዊነት ጋር ለዘመናት ያደረጉት ትግል ውጤት ነው ።

በማርክስ ፣ በኤንግልስና ሌኒን የተዋቀረው የዲያሌክቲካዊ ቁስ አካላዊ ፍልስፍና ሐሳባዊነትን በማንኛውም ቅርጹ የማይቀበልና ክስተቶችን በተጨባጭ የሚያጠና ሳይንስ ነው ። የቁስ አካልን መሠረታዊነትና ዘለዓለማዊነት ፣ በማይቋረጥ ዲያሌክቲካዊ እንቅስቃሴ በተለያዩ ቅርጾች መከሰቱን ፣ በአዝጋሚ ለውጥ (ኢቮሉሽን) እንዲሁም በሥራ ሰዎች ከእንስሳት ዓለም መለየታቸውን በሳይንሳዊ ምርምር ላይ በመመርኮዝ በተጨባጭ ያስረዳል ። ሰውም የተፈጥሮ አንዱ አካል መሆኑን ይገልጻል ። በዚህም የተፈጥሮና ማኅበራዊ ክስተቶችን መሠረታዊ አንድነትና ልዩነት በየፈርጃቸው በትክክል ለመገንዘብ ያስችላል ።

የሥነ ዘዴ ጠቀሜታ

የሥነ ዘዴን ጠቀሜታ በግንዛቤ ወይም በዕውቀት ሂደት ባለው መግሪያነቱና ከመደባዊ ትግል አንጻር ለማየት ይቻላል ። መጀመሪያ በግንዛቤ ሂደት ያለውን ጠቀሜታ እንመልከት ። ሳይንሳዊ ግንዛቤን ለመጨበጥና ዕውቀትን ለማጠናቀር ትክክለኛ አቀራረብ ፣ ሥነ ሥርዓት ፣ ቴክኒክና ዘዴን መከተል ያሻል ። ማርክስ እንዳለው «እውነት ውጤትን ብቻ ሳይሆን እሱን ለመፈለግ የሚከተሉትንም መንገድ ጭምር ያቅፋል። እውነትን የመከታተያው ዘዴ ራሱ እውነተኛ መሆን አለበት ።» [6]

ሳይንሳዊ ሥነ ዘዴ በሳይንሳዊ ፍልስፍና ላይ ይመሠረታል ። ማርክስ ፣ ኤንግልስና ሌኒን የተለያዩ የንቃተ ኅሊና ዘርፎች (ፍልስፍና ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፣ ታሪክ ፣ ወዘተ) በዲያሊክቲካዊና ታሪካዊ ቁስ አካላዊ አመለካከት አንፃር እንዲጠኑ መሠረት የሚሆን ንድፈ ሐሳብ በማቀነባበራቸው ለአብዮታዊ አስተሳሰብ እመርታን አስገኙ ፤ ለወዝአደሩ ንቅናቄ ፖሊሲና ስልትም መሠረታዊ ሐሳብ አቀረቡ ።

ማርክሳዊ ዲያሌክቲክስ የዕድገትና የሁለንተናዊ ግንኙነት ንድፈ ሐሳብ ነው። ዓለም በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ፣ ለውጥና ዕድገት ውስጥ መሆኑን ይገነዘባል ። በጠቅላላው በምድርም ሆነ በኅዋው ያለው ሁሉ የቁስአካል የረጅም ጊዜ ዕድገት ውጤት መሆኑን ይገልጻል ። ኤንግልስ ዲያሌክቲክስ የተፈጥሮ ፣ የኅብረተሰብና የሐሳብ ወይንም የንቃተ ኅሊና እንቅስቃሴና ዕድገት አጠቃላይ ሕግጋት ሳይንስ ነው ይላል ።

ፍልስፍናው የታሪካዊ ሂደትን ፍሬ ነገርና የማኅበራዊ ዕድገትንም አጠቃላይ ሕግጋት

Digitized by Google

የሚያጠና ሳይንስ እንደመሆኑ ፣ የማንኛውም ማኅበራዊ ሳይንስ ንድፈ ሐሳባዊና ሥነ ዘዴያዊ መሠረት ነው ። [7]

ዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁስአካልነት የምርምርና ጥናት ሁለንታዊ ሥነ ዘዴ ነው ። ፍልስፍናው የተገኘው በሰዎች የረጅም ጊዜ ልምድና ንድፈ ሐሳባዊ ሥራዎች ከተደረሰባቸው ተጨባጭ መደምደሚያዎች ነው ። ስለሆነም መደምደሚያዎቹ ለልምድ መመሪያና በልምድም የሚበለጽጉ እንጂ ንድፈ ሐሳባዊ ይዘታቸው እንደቀኖና የሚታይ አይደለም ። ስለሆነም የተፈጥሮም ሆነ የማኅበራዊ ሳይንሶች ጥናትና ምርምር በሰፊው እንዲካሄድ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ በከፍተኛ ደረጃ ያደፋፍራል ።

የማኅበራዊ ግንዛቤ ንድፈ ሐሳብም ሆነ ሥነ ዘዴ ያለ አጠቃላይ ፍልስፍናዊ መርሆዎች ሊኖሩ አይችሉም ። ይህም ማለት ሳይንሶች የተፈጥሮም ሆኑ ማኅበራዊ ከየራሳቸው ንድፈሐሳብና ቴክኒክ ሌላ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍናን መሠረታቸው ያደርጋሉ ወይም የሱ አካል ሆነው ይታያሉ ማለት ነው። ስለሆነም በግናቸውም የምርምርና ጥናት ተግባር የተሠማሩ ምሁራን ለሥራቸው ሥምረት የማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብን መሠረታዊ ግንዛቤ እንዲያገኙና በሥነ ዘዴነቱም እንዲጠቀሙ ማድረግ ወሳኝ ነው ።

ሥነ ዘዴ ሲጠን በተለይ የማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። የኅብረተሰብን ዕድገት በትክክል ለመምራት ፣ የቡርዧንና ሌሎችንም ኢሳይንሳዊ አመለካከቶች ለመታገልና የሰፊውንም ሕዝብ ንቃተ ኅሊና በሳይንሳዊ አመለካከት ለመቅረጽ ማኅበራዊ ሳይንሶችን በትክክለኛ ሥነ ዘዴ ላይ መመሥረት ወሳኝ ጉዳይ ነው ።

በማኅበራዊ ሳይንሶች ማርክስ የፖለቲካ ኢኮኖሚን አስመልክቶ እንዳለው «ለግንዛቤያችን በዘዴነት ማይክሮስኮፕም ሆነ የኬሚካል ንጥረ ነገሮች አይጠቅሙም ። ሁለቱም በረቂቅ የሐሳብ ትንተና መተካት አለባቸው ።» [8]

በታሪካዊ ቁስአካልነት ሥነ ዘዴያዊ ጽንሰ ሐሳቦች፣ ፈርጆችና ሌሎችም የ«ረቂቅ ሐሳብ ትንተና (the force of abstraction`) መነሻዎች ለሳይንሳዊ ግንዛቤያችን በመሣሪያነት ያገለግላሉ ። እነዚህ ማኅበራዊ ክስተቶችን የምንረዳባቸው መነሻዎች እንዲሁ በዘፈቀደ የሚገኙ አይደሉም ። ከተጨባጭ ነገሮችና ግንኙነቶች ጋር የተገናዘቡ የክስተቶችን ባሕርያት በትክክል የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው ። ይህ ካልሆነ የክስተቶችን ባሕርያት ፣ ግንኙነትና ሕግጋት አጥንቶ ሳይንሳዊ ግንዛቤ ለማግኘትና ከጠቃሚ መደምደሚያዎች ለመድረስ አይቻልም ። ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ ከሐሳባዊነት የሚለየውም አንዱ በዚህ ነው ።

ማርክስ ስለዚህ አቀራረብ መሠረታዊነት እንዲህ ሲል አብራርቷል ። «እኛ የምንጀምርበት መነሻ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚገኝ አይደለም ፤ ቀኖናዊም አይደለም ። ነገር ግን ለረቂቅ ሐሳብ መነሻ ከሆኑ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ነው ።» [9] የማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ ፍልስፍናና ሥነ ዘዴ ከተጨባጭ ማኅበራዊ ልምድና የዕድገት ታሪክ የተቀመሩ መደምደሚያዎች ናቸው ። ስለሆነም የታሪክ ቁስአካልነት መርሆዎች ፣ ጽንሰ ሐሳቦች ፣ ፈርጆች (Categories) እና ሕጎች የሰውን ንጽረተ ዓለም የሚቀርጹ ከመሆናቸውም ሌላ ተጨባጭ ታሪካዊ ማኅበራዊ ክስተቶችን ለመገንዘብ ሥነ ዘዴያዊ መሣሪያ ናቸው ።

ማንኛውም ማኅበራዊ ሳይንስ ማኅበራዊ ኅልውና ከማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና ቀዳሚ መሆኑን ፣ የንድፈ ሐሳብና ልምድ አንድነትን ፣ ወዘተ. መርሆዎች ፣ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነት፣ የታህታይና ላዕላይ መዋቅር ግንኙነቶችና መስተጋብርን ፣ የማ

ኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን ምንነት ፣ ወዘተ . . . ፈርጆችንና በኅብረተሰብ ሕይወት የቁሳዊ ምርት ወሳኝነትን ፣ የመደብ ትግልን ፣ ወዘተ . . . ሕጎች የግድ በትንታኔው መጠቀም ይኖርበታል ። [10]

ከላይ እንደተመለከተው ሁለንታዊ የሆነው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ የንድፈ ሐሳብንና የተግባርን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት አበክሮ ያስረዳል ። ማኅበራዊ የምርት ክንዋኔ ለሰዎች ህልውና መሠረታዊ የመሆኑን ያህል የጽንሰ ሐሳቦች ፣የንድፈ ሐሳቦች፣የዕውቀትና የሳይንስም ምንጭ ነው ። ያለ ልምድ ንድፈ ሐሳብ ብቻውን ፋይዳ አይኖረውም ፤ ያለ ንድፈ ሐሳብም ልምድ ዕውር ነው ።

ለትክክለኛ ግንዛቤም ሆነ ምርትን ለማሳደግ የተፈጥሮም ሆነ ማኅበራዊ ሳይንሶች ከልምድ ጋር መሄድ አለባቸው ። በማርክሳዊ ሥነ ዘዴ «ትምህርት ለትምህርትነቱ ፣ ዕውቀት ለዕውቀትነቱ» የሚለው አቀራረብ ተቀባይነት የለውም ። ስለዚህ ነው ዛሬ የአብዮቱ የትምህርት መስክ መፈክር «ትምርት ለምርት ፣ ለምርምርና ለንቃተ ኅሊና» የሚለው ። ይህም የምርምርና ጥናት ውጤቶች ከምርምር ጣቢያና ከሴሚናር ክፍሎች ወጥተው ለሰፊው ሕዝብ ምርታማነት ፣ ለተሻሻለ አደረጃጀትና አሠራር እንዲውሉ ፣ በዚህም ልምድ እንዲዳብሩ የማድረግን አስፈላጊነት ያስረዳል ።

በአጠቃላይ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ ያለፉትንም ሆነ አዳዲስ ሂደቶችንና ክስተቶችን ለማጥናትና ለመተርጐም ፣ ለሚከሰቱ ችግሮችና ቅራኔዎች በትክክለኛ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ሳይንሳዊ መፍትሔ ለመስጠት የተፈተነ መመሪያ ነው ። የዚህ ሥነ ዘዴ ባሕርያት ሲጠቃለሉ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። [11]

1. ነባራዊ አቀራረብ ፣ (objectiveness) ማለትም ሂደትንና ክስተቶችን እንዳሉ ማጥናት ፤

2. አጠቃላይነት (comprehensiveness) (በዚህ ሂደትና ክስተቶች በውስብስብ ግንኙነታቸው ተጠንተው ዋና ምክንያታቸው ይለያል ፤)

3. ሂደትንና ክስተቶችን ከዕድገት አንፃር ማጥናት ፤ በዚህም የለውጥ ውስጣዊ ምክንያታቸውን መለየት ፤

4. የሚጠናውን ጉዳይ ከታሪክ አንፃር መተንተን ፣ (Historical approach)

የምርምር ሥነ ዘዴ ከርዕዮተ ዓለም ተጽዕና ሊወጣ አይችልም ። በመደብ በተከፈለ ኅብረተሰብ ርዕዮተ ዓለም የመደቦችን ጥቅም የሚያንፀባርቅ የአስተሳሰብ ፣ የአመለካከት ፣ የንድፈ ሐሳብ ፣ ወዘተ...ቅንብር እንደመሆኑ በሥነ ዘዴ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። ዛሬ ጐልተው የሚታዩ የፊውዳል ፣ የቡርዧ የንዑስ ከበርቴና የማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለሞች አሉ ። እነዚህ ሁሉ ለመደብ ጥቅም የቆሙም ቢሆን ፣ ለሠርቶ አደሩ ጥቅም የቆመው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም ሳይንሳዊ በሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች ፣ ፍልስፍናና ንድፈ ሐሳብ የተገነባ በመሆኑ ፣ ለሳይንሳዊ ሥነ ዘዴ አመቺና ሳይንስንም ከማንኛውም ውሱንነትና ማነቆ ነፃ ለማድረግ የሚታገል ርዕዮተዓለም ነው ።

የቡርዧው መደብ ዘዴና አመለካከት በሐሳባዊ ፍልስፍና ላይ የተመረኮዙና ለዚያ መደብ ጥቅም የቆሙ ናቸው ። ቡርዧው የተፈጥሮ ሳይንስን ያዳበረው ምርቱን ከፍ ለማድረግ በነበረው ጥረቱ ነው ። በእርግጥ የሳይንስ መምጠቅና መራቀቅ ጠቅላላ የሰው ልጆች ያካበቱት የጋራ ሀብት ቢሆንም ፣ የምርት መሣሪያዎች በጥቂቶች እጅ በሚገኙበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤትም በአብዛኛው የጥቂቶች ይሆናል ።

ዛሬ በካፒታሊስት አገሮች የሚገኙ ሳይንቲስቶችና ውጤቶቻቸው በሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር ያሉና የእነርሱም አገልጋዮች በመሆናቸው ሳይንስና ቴክኖሎጂ የእነዚሁ

Digitized by Google

የጥቂት ሞኖፖሊስቶች አገልጋይ ነው ። በዚህ ምክንያት በካፒታሊስቱ ዓለም ሀብት በጥቂቶች እጅ እየተካበተ በሌላ ጐን ወዝ አደሩ በአንጻራዊና ቀስ በቀስም እየጨመረ በሚሄደው የድኅነት አዘቅት መግባት ግድ ሆኖበታል ።

በስግብግብ ሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር የተካበተ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቱ እጅግ አደገኛ መሆኑን ካለፉት ሁለት የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶችና ከተለያዩ የዕብሪት ወረራዎች ፣ ዛሬም ዓለምን ለቴርሞኒዩክሊየር ጦርነት ሥጋት ከማጋለጡ አንፃር ለማየት ይቻላል ።

የሰው ልጅ ከሥራ ልምድ ለሥራ ምርታማነት ያካበታቸው ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙሉ ጠቀሜታቸው ለጋራ የሚሆነው በሶሻሊስት አብዮት ብቻ ነው ። ይህንንም ፣ የሶሬውን ሕዝብ ኑሮ በአጭር ጊዜ በማሻሻል በዓለም ላይ በፍትሕና በሰላም ጥያቄ ግንባር ቀደም ሚና ካለው ከዓለም ሶሻሊስት ሥርዓት በተግባር ለማየት ይቻላል ። በአገራችንም በኋላቀር አስተሳሰቦች ተተብትቦና ለጥቂት የገዥ መደቦች መጠቀሚያ እንዲሆን ተወስኖ የነበረው ሳይንስና ውጤቱ ዛሬ ለብዙኃን በሚያገለግልበት ሁኔታ እየተስፋፋ ነው ። በዚህ በጋራ ጥቅም ፍልስፍና መሠረት ሳይንሳዊ ምርምርን ማስፋፋት ለሰፊው ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ብልጽግናና ነፃነት ቁ ል ፍ ነው ። የሰፊው ሕዝብ ወገን የሆኑ ምሁራንም ግልጋሎታቸው ለጥቂት ተንደላቃቂዎች ሳይሆን ለታሪክ ሠሪው ወገን መሆኑን በመገንዘብ በቆራጥነትና በአብዮታዊ መንፈስ ፀረ ሳይንስ አመለካከቶችን መዋጋትና ለዕድገት ድርሻቸውን ማበርከት ይፈለግባቸዋል ።

የተሳሳተ አስተሳሰብና የመደብ አመለካከት ጐልቶ የሚታየው በተለይ በማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ነው ። ማኅበራዊ ሳይንስ የኅብረተሰብን ሁኔታ አጥንቶ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ኑሮ ለማደራጀት ለመምራትና ለመቆጣጠርም ከፍተኛ ሚና ያለው ዘርፍ ነው ። በእርግጥ የሞኖፖል ቡርዧ ሁለንታዊ የሆነ የኅብረተሰብ ሳይንስ ባይኖረውም ፣ ለሥርዓቱ መሰንበትና ለመደቡ ጥቅም መከበር በሚበጅ አኳኋን በቁንጽል የሚዋቀሩ ግን በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የማይመሠረቱ ንድፈ ሐሳቦችና ሳይንሳዊ መሰል አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ርዕዮተ ዓለማውያን አላጣም ። እንዲያውም ግርክስ እንዳለው ቡርዧው ይህንኑ ብቻ መሥራት ድርሻቸው የሆነ ምሁራን አሉት። ይህ ሆኖ ሳለ የቡርዧ ምሁራን «የአካዳሚ ነፃነት» እያሉ ለዕውቀት ወይም ለምርምር ለራሱ እንጂ ለተወሰነ መደብ እንዳልቆሙ ይናገራሉ።በቡርዧ ኅብረተሰብ ከዚህ መደብ ቁጥጥርና ጥቅም ውጭ የሚኖሩ ምሁራንም ሆኑ የትምህርት ተቋሞች ቢኖሩ ሁኔታው ከአገር ወደአገር ቢለያይም ጥቂት ናቸው ። እነዚህ ጥቂቶችም ቢሆኑ ከባድ ተፅዕኖ ይደረግባቸዋል ። ይህ አባባል በካፒታሊስት ጐራ የሚገኙ የወዝአደሩንና የግንባር ቀደም ፓርቲዎቻቸውን ትግል እንዲሁም እየተባባሰ የሚሄደውን የካፒታሊዝምን ቀውስና የመጨረሻ ውድቀቱን በምንም ዓይነት ዝቅ አያደርግም ።

የቡርዧ ማኅበራዊ ንድፈ ሐሳቦች ዓላማ በአገርም ሆነ በውጭ አገር በተለይ በኋላቀር አገሮች የሕዝቦችን ሥነ ልቦና ፣ አስተሳሰብና አመለካከት ለዚህ መደብ ጥቅም በሚመች ሁኔታ መቅረጹ ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው በካፒታሊስት አገሮች በሞኖፖሊስቶች ቁጥጥር ሥር የሆኑ የከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋሞች የምርምሮቻቸው ዓላማ ለሞኖፖሊስቶች የሚውል ነው ። በማደግ ላይ ባሉት አገሮችም ያሉትን ተመሳሳይ ተቋሞች ያለባቸውን የገንዘብ ፣ የሰው ኃይልና የምርምር ልምድ ድካም በመጠቀም ሞኖፖሊስቶች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር ለማ

Digitized by Google

ዋል ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ ተቆጥበው አያውቁም ።

የቡርዧ ማኅበራዊ ምርምር ምንም እንኳ በስታቲስቲክስ፣ በዘመናዊ ኮምፒዩተር ቴክኒክና በሒሳብ የሚደገፍ ቢሆንም የማኅበራዊ ክስተቶችን ትክክለኛ ባሕርያት፣ ውስጣዊ ግንኙነታቸውንና ነባራዊ ሕጎቻቸውን የሚያስረዳ አይደለም ። ዛሬ ሳይንሳዊ ትንታኔ እንደሚያስረዳውና ከዕለታዊ ኑሮም መገንዘብ እንደሚቻለው በብሔርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛውና የማይታረቅ ቅራኔ ያለው በወዝ አደርና በካፒታሊስት መደቦች፣ በአርነት ንቅናቄና በሞኖፖሊስቶች፣ በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል ነው ። የሞኖፖል ቡርዧ በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች ተረፈ እሴቱን በተለያዩ የዘረፋ ዘዴዎቹ የማግበስበስ ተግባሩን ለመቀጠል ሲል ይህንን የሚቃወሙትን ኃይሎች ቢቻለው ለማዳከም የተሳሳቱ አመለካከቶችንና ንድፈ ሐሳቦችን ማቅረብ አንዱ ስልቱ ነው ። በዚህም እውነታን መካድ፣ የሌለውን እንዳለ፣ ያለውንም እንደሌለ አድርጐ ማቅረብ የባዶ ቃላትና ጽንሰ ሐሳቦች ናዳ ማውረድና ታሪክንም አጣሞ ማቅረብ ተግባሩ ሆኗል ።

ይህ ዓይነቱ አሳሳችነት በቡርዧ ታሪክ ውስጥ ከዱሮ ጀምሮ የቆየ ባሕርይ ነው ። ቡርዧ ዲሞክራሲ ፣ ወንድማማችነት ፣ እኩልነት ፣ የሰው ልጅ መብት ለሁሉ ፣ ወዘተ . . . እያለ በአንድ በኩል ሲለፍፍ በሌላ በኩል የባርያ ንግድን፣ ቅኝ አገዛዝን፣ ፋሺዝምን ፣ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝንና ዘረኝነትን ሲደግፍና እንደየሁኔታው ሲያስፋፋ እንደኖረ፣ ዛሬም ባመቸው ሁኔታ በእነዚህ ዘዴዎቹ እንደሚጠቀም ታሪክ ምስክር ነው ። ጌታና ባርያ፣ ቅኝ ገዢና ተገዢ፣ ጥቂት የሀብትን ምንጭ የሚቆጣጠሩና ብዙኃኑ ድሀ ሠርቶ አደሮች ባሉበት ዲሞክራሲ፣ ወንድማማችነት እኩልነት፣ መብት፣ ወዘተ . . . ማለት ለሰፊው ሕዝብ ከአፋዊነት አያልፍም ።

ካፒታሊዝምን የመጨረሻ ሰብአዊና እንዲሁም የማያልፍ ዘለዓለማዊ አድርጐ ማቅረብ የቡርዧ ምሁራን ተግባር ነው ። ነገር ግን በታሪክ ወደር የሌለው እልቂት ሲፈጽም የኖረና በዘረፋ፣ በጭፍጨፋና በሰው ዘር ፍጅት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት መሆኑን ያለፉት የአምስት ምዕት ዓመታት ታሪክ ምስክር ነው ። የካፒታሊስት ሥርዓት አላፊ መሆኑንም ዛሬ በከፍተኛ ደረጃ እየተገነባ ያለው ሰብአዊው የሶሻሊስት ሥርዓት በተግባር አሳይቷል ።

ሲዘርፉ እንረዳለን፣ ሲያደነቁሩ እናሠለጥናለን፣ ሲወስዱ እንሰጣለን ብሎ መዋሸት የካፒታሊስቶች ልምዳቸው ነው ። ቀድሞ ቅኝ አገዛዝን ሥልጣኔና ክርስትና ማስፋፋት እያሉ ይመጻደቁ እንደነበር ሁሉ ዛሬም እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን መረዳዳትና የእኩልነት ግንኙነት ለማስመሰል ይጥራሉ። በዚህም የታወቀውን ሳይንሳዊውን የሌኒንን የኢምፔሪያሊዝም ንድፈ ሐሳብ [12] ለመቃወም ይሞክራሉ ። ነገር ግን እንደቡርዧ ምሁራን ምኞታዊ ዘዴና ንድፈ ሐሳቦች ሳይሆን ታሪክ በተጨባጭ እንዳሳየው ጭቁን ሕዝቦች በአርነት ንቅናቄዎቻቸው መሪነት በመነሣትና የኢምፔሪያሊዝምን ቀንበር ሰባብረው የተሰነዘሩትንም የሐሰት ንድፈ ሐሳቦች ውድቅና በትክክለኛ ንቃተ ኅሊና ታሪክም ሥፍራ የሌለው መሆኑን አስመስክረዋል ። አዲሶቹን ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተፈጠሩ ንድፈ ሐሳቦችንም ታሪክ እያጋለጣቸው ነው ።

ቡርዧው ዛሬም በአገሩ ያለውን የወዝአደር ትግል ለማደብዘዝና አብዮታዊ ስሜትን ለማኮላሸት ሐሳባዊ ዘዴውን በማዳበር የተለያዩ የማደናገሪያ ጽንስ ሐሳቦችና ንድፈ ሐሳቦችን ይጠቀማል ። እነዚህ ሲተነተኑ አጠቃላይ ጥረታቸው በወዝ አደሩና በቡርዧው መካከል ቅራኔ እንደሌለ፣ የመደብ ትግልም እንዳከተመ፣ የካፒታል ውጤት ለጋራ ጥቅም እንጂ ለጥቂቶች እንዳይደለና

Digitized by Google

ብዝበዛም ጨርሶ እንደሌለ ፣ ርዕዮተ ዓለም ራሱና ትግሉም እንዳበቃ አድርገው የሚያቀርቡ ግልጽ የሐሰት ትንታኔዎች ናቸው ። ከዚሁ ጋር የሶሻል ዲሞክራቲክ ጠጋኝ አመለካከቶች በወዝአደሩና በሞኖፖሊስቶች መካከል በአስታራቂነት እየተደነቀሩ የብዝበዛን ዕድሜ የማራዘም ሚና ይጫወታሉ።

ነገር ግን በየዕለቱ በርቡዧ አገሮች የሚታየው ሐቅ የሚያሳየው ተቃራኒውን ነው ። የወዝአደሩ ኑሮ በየጊዜው እየቆረቆዘ ፣ ከብሔራዊ ገቢ የሚያገኘውም አንፃራዊ ድርሻ ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ የሞኖፖሊስቶች ትርፍ ግን እየናረ ፣ ሥራ አጥነትና አንፃራዊና ፍጹም ድኅነት እየጨመረ መሄድ ፣ በዚህም ምክንያት የመደብ ትግል በሰላማዊ ሰልፎች ፣ በሥራ ማቆም አድማዎች ፣ በሰላም ጥያቄ መረባረብና በመሳሰሉ ቅርጾች እየከረረ መምጣቱ የቡርዧ ንድፈ ሐሳቦች ከእውነት የራቁ መሆናቸውን ያሳያሉ ። ተጨባጭ ሁኔታ በምኞት አይገዛምና ሂደቱ በማኅበራዊ ምርትና በግል ፍጆታ መካከል ያለው ቅራኔ በሶሻሊስት አብዮት ካል ሆነ እንደማይፈታ ፣ ይህም እውነታ ሊሸፈን እንደማይችል በተግባር የታየ ነው ። ይህንንም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ በግልጽ ያሳያል ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሞኖፖሊስቶች ከፍተኛ ርዕዮተ ዓለማዊ ጦርነት ያካሂዳሉ ። ለፀረ ሶሻሊስት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳቸው መሠረተ ቢስ ጽንሰ ሐሳቦችንና ንድፈ ሐሳቦችን የሚያቀነባብሩና ለዚሁ ተግባር በተፈጠሩ ተቋሞች የሚሠሩ ምሁራን አሏቸው። የእነዚህ ምሁራን አንዱ ተግባር ታዳጊ አገሮች በተቻለ መጠን ከዓለም አቀፍ ሞኖፖል ካፒታል ወጥመድ ሳይላቀቁ እንዲቀጥሉ በረቀቀ ዘዴ የሚያግባቡ ንድፈ ሐሳቦችንና ዘዴ እየፈጠሩ ማስፋፋት ነው ። [13]

እነዚህ ንድፈ ሐሳቦች የካፒታሊዝምን ጥሩነትና የቡርዧ መደብን «ለውጥ» ወዳድነት የሚሰብኩ ፣ ኋላቀር አገሮች ዕድገታቸው የሚሠምረውም በሥር ነቀል ለውጥ ሳይሆን በሞኖፖሊስቶች ሥር ሲሆኑ እንደሆነ አድርገው የሚያስተምሩ ፣ ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚቃረኑና በተግባር ከሚታየው ጋር የማይጣጣሙ ናቸው ። በእነዚህም ውስጥ «ምዕራባዊነት ፣ ዘመናዊነት ፣ የኮሚኒቲ ዕድገት ፣ የፖለቲካ ዕድገት ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት» የሚሉ መደባዊ ትንተናንና ማርክሳዊ ዘዴን የሚቃረኑ ሐሳቦች ይገኙባቸዋል ። በተጨማሪም የቅኝ አገዛዝ ስልት የነበረውን የመከፋፈልን ዘይቤ የሚያስፍን ጐሳዊነት (Ethnicity) የተባለውን የብሔረተኝነት ጽንሰ ሐሳብ የቡርዧ ምሁራን ዛሬ በሰፊው ይጠቀሙበታል ። [14] ይህ አቀራረብና ዘዴ በአካባቢ ደረጃ ሰፊውን ሕዝብ በቋንቋና በባህል ሰበብ ከማለያየትና የተገንጣይነትንም አመለካከት ከማስፈን ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፀረ ሶቭዬት ስሜትን እስከ ማፋፋም ድረስ የአድኅሮት መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ። የተፈጠረበትም ዓላማ ሳይንሳዊ የመደብ ትንተና ዘዴን ለማደብዘዝና የሰፊውን ሕዝብ መደባዊ አንድነት ፣ ፀረ አድኅሮትና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ግንባርን ለማዳከም ነው።

የእነዚህ ንድፈ ሐሳቦችና ዘዴዎች ዋና ዓላማ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የሚገኙትን ኅሊናዊ ሁኔታዎች ለካፒታሊስት ብዝበዛ በሚያመች ሁኔታ ለመቅረጽና የሰው ኃይልና ኢኮኖሚያቸውንም በሚፈልጉት ሁኔታ አደራጅተው ለመበዝበዝ ነው ።

በአጠቃላይ የቡርዧ ማኅበራዊ ንድፈ ሐሳቦችና የትንተና ዘዴ በሥነ ዕውቀት አኳያ ሐሳባዊ ፣ ቢበዛም ከፊል ሳይንሳዊና ተናክአታዊ ፣ ክስተቶችን በቁንጽል የሚያቀርቡ ከእውነታ ጋር የማይጣጣሙና በኢይንሳዊ ፍልስፍና ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ከመደብ አኳያ ለገዥ መደብ የቆሙና ለጭቆና የሚበጁ ፣ ፀረ ሠርቶ አደርና የኢምፔሪያሊዝም መሣሪያ ናቸው ። ስለዚህ ዛሬ በዓለም ላይ በእነዚህ ኢሳይንሳዊና አድኃሪ አመለካከቶች ፣ ንድፈ ሐሳቦች ፣ ርዕዮተ

Digitized by Google

ዓለምና በሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብና ርዕዮተ ዓለም መካከል ከፍተኛ ትግል ይካሄዳል ። የምርምር ሥነ ዘዴ ጥያቄም የዚሁ ትግል አካልና ወሳኝነትም ያለው ነው ።

የሦስተኛ ደረጃ ትምህርትና የምርምር ተቋሞች በአድኃሪ አመለካከቶችና በሳይንሳዊ ርዕዮተ ዓለም መካከል ከፍተኛ ፍልሚያ ከሚደረግባቸው ግንባር ቀደም መድረኮች ዋናዎቹ ናቸው ። በአገራችንም በእነዚህ ተቋሞች የሚሠማሩ ምሁራንና ተማሪዎች በሳይንሳዊ ግንዛቤና ሥነ ዘዴ እንዲታጠቁ ማድረግ ለተተለመው የዕድገት ዕቅድ ተገቢ ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ያዘጋጃቸዋል ። በቡርዧ የአመለካከት ዘዴና አሠራር ሶሻሊዝምን እንገነባለን ብሎ መጠባበቅ ህልም ነው ።

ለሶሻሊስት ግንባታ መሳካት የምሁራን ማፍሪያ መድረኮችና የምርምር ተቋሞች በማርክሳዊ ሌኒናዊ የምርምር ዘዴ እንዲታጠቁ ማድረግና የሰፊውን ሕዝብ ምሁራን በብቃትና በብዛት ማፍራት ወሳኝነት አለው ። በዚህ ረገድ የአገራችን የከፍተኛ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማም ፣ በማርክሲዝም ሌኒንዝም ፍልስፍና ላይ በመመሥረት ወጣቱን ትውልድና ሰፊውን ሠርቶ አደር ሕዝብ በአካል ፣ በመንፈስና በአእምሮ በማበልጸግና የሳይንስ ፣ የቴክኖሎጂና የባህል ደረጃውን በማሳደግ ሰብእናው የተሟላ አዲስ ሶሻሊስት ዜጋን ማፍራት መሆኑ [15] በግልጽ ተመልክቷል ።

ይህንን ግልጽ ዓላማ በተግባር ለመተርጐም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስ በየትምህርት ተቋሙ እንደ አንድ ትምህርት እንዲሰጥ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር ለግንዛቤና ለምርምር ብቸኛ ሳይንሳዊ ሥነ ዘዴ የመሆኑ ሐቅ ታውቆ በሥራ መተርጐም ይኖርበታል ። ለዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ጠቃሚ ነው ።

1. ተማሪዎች ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ አንብበው እንዲረዱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ትምህርቶችና ክስተቶች ለመተንተን ብቸኛ ሳይንሳዊ ሥነ ዘዴ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግ ፤ ማናቸውንም ክስተት በቃል ሲተነትኑ ወይንም በትምህርት ወቅትና ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ጥናቶች ሲያቀርቡ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳቦችንና ንድፈ ሐሳቦችን መነሻቸው አድርገው እንዲጠቀሙ የሚረዳ የትንተና ዘዴን ማስተማር ፤ ይህም ተማሪዎች አመለካከታቸውን በትክክል እንዲቀርጹ ፣ የዕውቀት አድማሳቸውን እንዲያሰፉና በሥራ ሲሠማሩ በግንባታቸው ሂደት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ከመርዳቱም ሌላ በከፍተኛ ት/ቤቶች አሁንም በተለያዩ ቅርጾች የሚከሰቱ የቡርዧ ንድፈ ሐሳብ ርዝራዦች እንዲወገዱ ይረዳል ። ትክክለኛ ማርክሳዊ ግንዛቤና ሥነ ዘዴ ከሌለ ተማሪዎችም ሆኑ ምሁራን ስለ አብዮቱም ሆነ ስለሠርቶ አደሩ ትግል ትክክለኛ ግንዛቤ ኖሮአቸው አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ማለት ዘበት ነው ።

2. አስተማሪዎች በትክክል ለማስተማርና ጠቃሚ ሳይንሳዊ ጥናቶችንና ምርምሮችን ለማቅረብ እንዲችሉ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ መታጠቅ የግድ ያሻቸዋል ። ይህ ከሆነ በሽግግር ወቅት በአስተሳሰባቸው በሐሳባዊ ወይም በቡርዧና በማርክሳዊ ሌኒናዊ አመለካከቶች መካከል የሚካሄደው ዲያሌክቲካዊ ትግል በቁስአካላዊ አመለካከት አሸናፊነት እንዲመራ ከማገዙም ሌላ አስተማሪዎች ለአብዮታዊ ርዕዮተ ዓለም በወገናዊነት እንዲታገሉ ያስታጥቃቸዋል ። ከላይ እንዳየነው ከመደብ ጥቅም ነፃ የሆነ ዘዴና ሳይንስ ወይም ምሁርነት ከቶ የለም ። «በአካዳሚክ ነፃነት» ስም ራስን ከሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል

Digitized by Google

ማግለል የቡርዧ ግብዝነትና ንዑስ ከበርቴያዊ ገለኝነት መሆኑ መታወቅ አለበት። ወገናዊ ያልሆነ ተቋም፣ ሳይንስ፤ ወይም ምርምር በፍጹም አይኖርም። ይልቅ እውነተኛ ነፃነት የሚገኘው ለሰፊው ሕዝብ ትግልና ትግሉ ለሚመራበት ሳይንሳዊ ርዕዮተ ዓለም በወገናዊነት ሲቆሙና በእሱም ሲመሩ ነው።

3. በምርምር ተቋሞች የሚሠሩ ምሁራንና በየመሥሪያ ቤቱ በምርምር በጥናት፣ በዕቅድ ዘርፎች የተሠማሩ ሠራተኞች ለምርት መዳበርና ለኅብረተሰብ ዕድገት የሚያደርጓቸው ጥናቶች ጠቃሚ ውጤት የሚኖራቸው ከዕድገታችን አቅጣጫ ጋር በሚጣጣም በማርክሳዊ ሥነ ዘዴ ሲተነተኑ ብቻ ስለሆነ ሥነ ዘዴውን እነርሱም እንዲከተሉ ማድረግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በቡርዧ አመለካከት ግንዛቤና ዘዴ ተመርቶ ሶሻሊዝምን መገንባት አይቻልም። ይህ ሲባል ቡርዧ የሚጠቀምባቸውን ጠቃሚ የሆኑ አቀራረቦችና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችንም (ስታቲስቲክስ፣ ሒሳብ፣ ኮምፒዩተር፣ ወዘተ...) አለመጠቀም ማለት ሳይሆን እንዲያውም እነዚህን በስፋት መጠቀምና ሐቆችንና ቁምነገሮችን ከታሪካዊ ሂደት ጋር አገናዝቦ በትክክል መተርጐምና ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ ማለት ነው። «ምርምር ለምርምር» ሲባል ሳይሆን ምርምር ለተግባር መመሪያ፣ ለዕድገት መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያሻል።

4. በአገራችን የጥናት ሴሚናሮች በየወቅቱ ይካሄዳሉ። በእርግጥም ትምህርታዊ ሴሚናሮችና ዓውደ ጥናቶች ጠቃሚ እንደመሆናቸው ዕቅድ እየተደረገላቸው በየዘርፉ መካሄድ አለባቸው። ነገር ግን ለእንዲህ ዓይነት መድረኮች የሚቀርቡ ጥናቶችም ማርክሳዊ ሌኒናዊ የትንተና ዘዴን የተመረኮዙ መሆን አለባቸው። (ይህም ባይ[illegible]ል ለጊዜው ቁ[illegible] ነገሮችን እንዳሉ የሚያቀርቡና ፀረ ማርክሲስት ዘዴና አመለካከቶች የሚያስፋፉ አለመሆናቸው መረጋገጥ አለበት።) ማንኛውም የቡርዧ ድርጅት በ«አካዳሚክ ነፃነት» እና በዕርዳታ ሽፋን ኢሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ለማስፋፋት ዕድል ማግኘት የለበትም።

እነዚህን የተጠቀሱትን ነጥቦች በሥራ ለመተርጐም ብዙ ጠቃሚ መንገዶች ይኖራሉ። ከእነዚህም የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

1. በምርምር ሥነ ዘዴ ዕውቀትና በተለይ በማርክሳዊ ሥነ ዘዴ ተከታታይ ጥናታዊ ሴሚናሮችን በማዘጋጀት ለሦስተኛ ደረጃ መምህራን መስጠት፤ (ይህም በአጠቃላይና በየትምህርቱ ዘርፍ ሊሆን ይችላል) እንዲሁም ምሁራን በየመስኩ በምርምር የተመረኮዙ ጽሑፎች እንዲያዘጋጁ ማደፋፈር፤
2. በየምርምር ተቋምና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጥናትና ዕቅድ ለተሠማሩ ሠራተኞች በኮርሶችና በሴሚናሮች የሥነ ዘዴን ዕውቀት የሚያገኙበትን መንገድ መቀየስ፤
3. የማርክሳዊ ሥነዘዴን ትምህርት በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ማስተማርና ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስ ማንኛውንም ክስተት በትክክል ለመረዳት ቁልፍ የመሆኑን ሐቅ ለተማሪዎች ማስጨበጥ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. Great Soviet Encyclopaedia, Vol. 16 (New York: MacMillan Inc., 1974), P. 209.
2. *Ibid.*
3. *Ibid.*, P. 210.
4. V.G. Afanasyev, Marxist Philosophy (Moscow: Progress Publishers, 1980 P.19-20.
5. F. Engels, Dialectics of Nature (Moscow: Progress Publishers, 1976), P. 62; K. Marx and F. Engels, Selected works in three volumes, Vol. 3 (Moscow: Progress Publishers, 1976), P. 339; Afanasyev, Op. Cit., PP. 18-19.
6. K. Marx and F. Engels, Collected Works, Vol. 1 (Moscow: Progress Publishers, 1977), P. 113.
7. Philosophy in the USSR (Moscow: Progress Publishers, 1981), P. 156.
8. K. Marx, Capital, Vol. 1 (Moscow: Progress Publishers, 1977), P. 19.
9. Marx and Engels, Selected Works, Vol. 1, (Moscow: Progress Publishers, 1976), P. 19.
10. Philosophy in the USSR, P. 159.
11. Vasili Krapivin, How to Study Marxist-Leninist Theory (Moscow: Novosti Press Agency Publishing House, 1984), P. 10.
12. V.I. Lenin, Selected Works, Vol. 1, (Moscow: Progress Publishers, 1977), PP. 642-731.
13. E.A. Tarabrin (Ed.), Neo-colonialism and Africa in the 1970s, (Moscow: Progress Publishers; 1978), PP. 249-268
14. Tarekegn Adebo, "Ethnicity Vs. Class: Concepts in the Analysis of the Ethiopian Revolution," Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies (Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies etc., 1984), PP. 541-594.
15. የኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት መሪ ዕቅድ(አዲስ አበባ፡ 1977) ገጽ 81-83

Digitized by Google

የ ፓ ር ቲ
ዲ ሲ ፕ ሊ ን

የቆየ መንገዳ

በአብዮታችን ሂደት ውስጥ ስለ ፓርቲ ዲሲፕሊን በተለያየ ጊዜና አቀራረብ ተደጋግሞ ተገልጿል ፤ ተነግሯል ። ይሁን እንጂ በተለይ የፓርቲ አባላትን ፣ በአጠቃላይም የመላውን ሠርቶ አደር የዲሲፕሊን ተገዥነትና የዓላማ ጽኑነት ለማጉልበት አሁንም ገና ያልተጨለፈና ብዙም መገለጽ ያለበት አስፈላጊ ጉዳይ ነው ። ብዙ ማንበብና ጠልቆም መገንዘብን ይጠይቃል ። ስለዚህም ስለፓርቲ ዲሲፕሊን ምንነትና አስፈላጊነት ተጨማሪ ግንዛቤን ማስጨበጥ የተጨበጠውንም ማዳበር የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ነው ።

በትድግሂያ የዲሲፕሊንን በአጠቃላይና በተለይም የፓርቲ ዲሲፕሊንን ትርጉም መገንዘብ ለአጠቃላዩ ግንዛቤያችን ይበጃል።

ዲሲፒሊን ኅብረተሰብ ለሚከተለው ልምድና ወግ ወይም ለመመሪያዎችና ለትእዛዝ ራስን የማስገዛት ሥነ ምግባር ነው ። ሰዎች በማኅበር ሊኖሩ የሚችሉት ፣ የሚኖሩበትንም ሥርዓት የሚያከብሩት ዲስፕሊን ሲኖራቸው ብቻ ነው ። [1] ዲሲፕሊን አንድ ኅብረተሰብ ከሚቀበለውና ሕግና ከሚተዳደርበት ሞራል ጋር የሚስማማ ፣ በዚህ ላይ የተመሠረተ የተወሰነ ሰብአዊ ባሕርይ ነው [2] ለማለት ይቻላል ።

«የፓርቲ ዲሲፕሊን የተግባር አንድነት፣ የውይይትና የሐሳብ ፣ የመንቀፍና የመደገፍ ነፃነት ነው ። » [3] የፓርቲ ዲሲፕሊን የአባላት የተግባር አንድነት ነው ፤ የውይይትና የጊስ ነፃነት ነው ። [4]

ለአንድ ኅብረተሰብ ወይም ድርጅት ህልውና የተሟላና የተደላደለ ሕይወት መስፈን ይህ ሰብአዊ ባቢርይ እጅግ አስፈላጊ ነው ። ለተመጣጠነና ለተደላደለ ማኅበራዊ ዕድገት ፣ ለተሟላ ድርጅታዊና ቡድናዊ የሥራ እንቅስቃሴና አጥጋቢ ውጤት መገኘት በአንድ ኅብረተሰብ ወይም ድርጅት ውስጥ የሰዎች የተሟላ ጠባይ መገኘት አስፈላጊ ጉዳይ ነው ።

Digitized by Google

ምኒዝም ቢሆን ባንድ ኅብረተሰብ ፥
ወይም ድርጅት ውስጥ ፥ በአጠቃላይ ማን
ኛውም የኅብረተሰብ ወይም የድርጅቱ
አባል ወደደም ጠላ ሊቀበለውና ሊከተለው
የሚገባ ማኅበራዊ ግዴታ ይኖራል ። እንዲ
ሁም በዚያው ኅብረተሰብ ውስጥ እንደ ድር
ጅቶች የሥራም ሆነ የአደረጃጀት ጠባይ ፥
እንደ አስፈላጊነቱ የሚስማማ ፥ የተለየ የዲ
ሲፕሊን ሁኔታ ይኖራል ። ለምሳሌ«የሥራ
ዲሲፕሊንን» ብንወስድ ፥ የተወሰነ ሥራን
በተወሰነ ጊዜ በጥራትና በብቃት ለማከናወን
የሚያስችሉ ሁኔታዎችን (ጠባይን) አሟ
ልቶ መገኘትን፥ማለትም የሥራ መሣሪያዎች
መሟላት ፥ መሣሪያዎችን በተገቢው መን
ገድ በጥንቃቄ መጠቀምና መንከባከብ ፥
የሥራ ጊዜን ማክበርና መጠቀም ፥ ሠራተ
ኛን በተገቢው ቦታና ሁኔታ ማሠማራት ፥
በአጠቃላይ ለምርት ዕድገትና ለኅብረተ
ሰቡ ደኅንነት የሚበጀውን ሁሉ በተገቢው
መልክ ማከናወን ፥ ለዚህ ብቁ የሚያሰኘ
ወን ሰብአዊ ባሕርይ ይዞ መገኘት ፥ በዚህ
ዘርፍ የዲሲፕሊን መሟላትን የሚገልጽ
አንዱ ሁኔታነው ።

ወታደራዊ ዲስፕሊንን ብንመለከት በወ
ታደራዊነት የሚገባውን ባሕርይ ፥ ማለ
ትም ወታደራዊ ግዴታን በብቃት ለመወ
ጣት የሚያስችልን አጠቃላይ ባሕርይ ይዞ
መገኘትን የሚያጠቃልል አንዱ የዲሲፕ
ሊን ሁኔታ ነው ፤ የትምህርት ቤት ዲሲ
ፕሊን ደግሞ ከክፍል ውስጥ ጀምሮ በትም
ህርት ቤት ቅጥር ግቢ ሊከተሉት የሚገ
ባን ሥነ ሥርዓት ከቤተሰቡና ከኅብረተሰቡ
ጋር ሊያደርግ የሚገባን ማኅበራዊ ግንኙ
ነት የሚያቅፍ ፥ «የተማሪነት» ባሕርይን
የሚያንፀባርቅ የዲሲፕሊን ዘርፍ ነው ።
በዚህ መልክ በየዘርፉና በየድርጅቱ በተ
ለይ ሊከተሉት ፥ ሊፈጽሙትና ሊያከብሩት
የሚገባ የዲሲፕሊን ሁኔታ ይኖራል ። ከነ
ዚህ ውስጥ የፓርቲ ዲሲፕሊን አንዱ
ሲሆን ፥ ዘርዘር ባለ መልኩ ወደ ፊት የምና
የው ይሆናል ። በቅድሚያ ግን ባንድ የተወ
ሰነ ወቅት ባንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚ
ከሰቱ የዲሲፕሊን ዓይነቶችን ጠቅለል
ባለ መልክ እንመልከት ።

የዲሲፕሊን ዓይነቶች

ባንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረው የዲ
ሲፕሊን ዓይነትና ሁኔታ ፤ ባንድ የተወሰነ
ወቅት ባለው ማኅበራዊ ግንኙነት ላይ
የሚመሠረትና የሚወሰን ነው ። በዚህ የተ
ወሰነ ወቅት ባለው የኅብረተሰቡ ማኅበ
ራዊ ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ የሚኖረው
ዲስፕሊን በሦስት ዓይነት ሊከፈል ይቻላል፤

1. ራስን በራስ የመግዛትና የመቆጣጠር
ውስጣዊ ዲሲፕሊን ፥

2. ለግል ጥቅምና ፍላጐት ሲባል እያንዳ
ንዱ የኅብረተሰብ አባል ሊቀበለውና
ሊከተለው የሚገደድ ዓይነት ዲሲፕ
ሊን ፥

3. በውጭ ኃይል አስገዳጅነት የሚከበር
ዲሲፕሊን ።[5]

እነዚህ ሦስቱም የተለያዩ የዲስፕሊን
ዓይነቶች ባንድ የተወሰነ ወቅት ባለ ኅብ
ረተሰብ ውስጥ ባንድነት የሚከሰቱና እያን
ደንዳቸው በራሳቸው አስፈላጊነት ያላቸው
ናቸው ።

ውስጣዊ ዲሲፕሊን (Inner Discipline
or self Discipline) የሚባለው ፥ ራስን በራ
ስ የመግዛት (የመቆጣጠር) ፥ የኅብረተሰቡ
አባላት በሚቀበሉትና በሚከተሉት ልማድና
ሕግ ላይ ተመሥርቶ የሚንፀባረቅና የሕዝ
ቡን አጠቃላይ ጠባይ በሚገዙት ልማዶች
አስገዳጅነት እያንዳንዱ የኅብረተሰቡ አባል
በእነዚህ ውስጣዊ ልማዶችና ጠባዮች፥ራሱ
በራሱ የሚገራበት (የሚገዛበት) የዲሲፕ
ሊን ዓይነት ነው ። ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን ፥
ያለምንም የውጭ ኃይል አስገዳጅነት ፥ በአ
ካባቢው በኅብረተሰቡ ልማዳዊ ተፅዕኖ እግ
ካይነት ብቻ ቀስ በቀስ በኅብረተሰቡ አባ

Digitized by Google

ላት ሥርጸ ተመልሶ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚንፀባረቅ ሰብአዊ ባሕርይ ነው ።

ሰዎች በኅብረተሰብ ወይም በድርጅት ውስጥ ጥሩ ወይም መጥፎ ተብለው የሚቆጠሩ ልማዶችን ለማስወገድ ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ የተለመዱ ሁኔታዎችንና በሕግም ሆነ በልማድ ተቀባይነት ያላቸውን ለማክበር ያለምንም የውጭ ኃይል አስገዳጅነት በራሳቸው የውስጥ ስሜት አስገዳጅነት ብቻ ራሳቸውን በራሳቸው ይቆጣጠራሉ ። በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ከሌላቸው ነገሮች ፣ የኅብረተሰቡ አ ባ ላ ት መጥፎ ከሚሏቸው ልማዶች (ድርጊቶች) ራሳቸውን ይገታሉ ። በኅብረተሰቡ ዘንድ ከተለመደው ጠባይ ውጭ በሚሆኑበት ጊዜም በኅብረተሰቡ ተቀባይነት የሌለው፣ አልፎም የሚያስነውር ድርጊት በመፈጸማቸው ፣ ከተለመደው ጠባይ ውጭ ሆነው በመገኘታቸው ጥፋተኛነታቸው በራሳቸው ይሰማቸዋል ። የራሳቸው ኅሊና መልሶ ራሳቸውን ይወቅሳቸዋል ። በኅብረተሰቡ አባላት የሚሠነዘርባቸውንም ኂስ ለማጤን ይገደዳሉ ። ከልማድ ውጭ ለፈጸሙት ድርጊት (ላሳዩት ጠባይ) የመፀፀት መንፈስ ያድርባቸዋል ። ጥፋቱን ድጋሚ ላለመፈጸም በራሳቸው ላይ ውሳኔ ያደርጋሉ ። ማለትም በራሳቸ የውስጥ ስሜት ይገዛሉ ።

ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን የሚያስገነዝበን ሰዎች የኅብረተሰቡ አባላትና የኅብረተሰቡ ሕግም ሆነ ልማድ የማይቀበለውን ድርጊት በሚፈጽሙበት ጊዜ ድርጊቱን በራሳቸው ተገንዝበው ፣ ድጋሚ ላለመፈጸም፣ ያለምንም የውጭ ኃይል አስገዳጅነት ራሳቸውን መከረውና ወቅሰው ፣ ራሳቸውን የማስማማት ጤናማ የዲሲፕሊን ዓይነት መሆኑን ነው ። በዚህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን ውስጥ ሰዎች ለልዩ ጥቅም ፣ ለዝና ፣ ለክብር. . . ሲሉ የሚያሳዩት ጠባይ ፣ የሚፈጽሙት ድርጊት ቦታ አይኖረውም ። ወኔአቸውም ሆነ ክብረ ኅሊናቸው የሚሸጥ የሚለወጥ ወይም የሚሸነገል አይሆንም ። በኅብረተሰቡ አባላት ዘንድ ማንነታቸው ታውቆ ፣ ተወደውና ተከብረው የመኖር ዕድላቸው የሰፋ ነው ። ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን ነው ለሰዎች (ለሠርቶ አደሮች) ነፃነት ፣ መብትና እኩልነት ፣ ለእውነት ፣ ለፍትሕና ለትክክለኛ ሥራ በጽኑ የሚፈለገው ። ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን ነው በሶሻሊስት ግንባታ ሂደት ውስጥ እየሠፈነ ፣ እየበለጸገ የሚሄደው ።

ሌላው ዓይነት ዲሲፕሊን ከጥቅም ጋር በተያያዘና ለግል ፍላጎት ሲባል የሚደረግ (ሊከተሉት የሚገደዱበት) በውጭ ኃይል አስገዳጅነት ላይ የተመሠረተው የዲሲፕሊን ዓይነት ነው ። ለጥሩም ይሁን ለመጥፎ ፣ ጎጂም ይሁን ጠቃሚ ፣ ለሠራበት ወይም ሥራ ለፈታበት ፣ ላጠፋው ወይም ላለማው ፣ . . . ነገር ጥቅም ወይም ጉዳት የሚያስከትልበት ፣ በራሱ የውስጥ ስሜትና ፍላጎት ሳይሆን የውጭ አስገዳጅነት ያለበት ዓይነት ዲሲፕሊን ነው ። ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን እያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል ወዶም ይሁን ሳይወድ እንዲቀበለውና እንዲከተለው የሚገደድበትን ሁኔታ የሚያስገነዝብ ነው ።

ያንድ ኅብረተሰብ ወይም ድርጅት አባል ኅብረተሰቡ ወይም ድርጅቱ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ፣ ሕጎችና ደንቦች ወደደም ጠላ የመቀበልና የመፈጸም ግዴታ ይኖርበታል ። ስለዚህም ይቀበላል። እንዲቀበል የሚያደርጉት ፣ የሚያስገድዱት ምክንያቶች ምንድንናቸው?ብለን ብንጠይቅ ፣ ለምሳሌ ቁሳዊ ጥቅም ሊያገኝበት የሚችለውን ተግባር ወይም ሌላ ዕድገት ነክ ጥቅሞች ሊያስገኙለት የሚችሉ ተግባራትን (ኃላፊነትን ፣ ...) በትክክል ሳያሟላ ቢቀር ፣ የሚገባውን አሟልቶ ባለመገኘቱ ፣ ሊያገኝ የሚገባው ጥቅም ፣ ክብር ፣ ሽልማት ፣ ዕድገት ፣ . . . ይቀርበታል ። ይህን ዓይነቱን ጥቅም ላለማጣት ሲባል ፣ ኅብረተሰብ ወይም ድርጅት የሚጠበቀውን ተግባር አሟልቶ ለመገኘት ሲባል የሚከተሉት ሥነ ምግባር ሌላው የዲሲፕሊን ዓይነት ነው ።

Digitized by Google

ለልዩ ጥቅምና ዕድገት ሲባል ሳይሆን ፣ ኅብረተሰብ ወይም ድርጅት የማይፈልገውን የማይቀበለውን ፣ (ከሞራል ወይም ከሕግ ውጭ) ተግባር በመፈጸም፣ከሚደርስ ወቀሳ፣ ማስጠንቀቂያ ፣ ቅጣት ወዘተ . . . ለመዳን ወይም ለመሸሽ ሲባል ብቻ የሚስተዋል ዲሲፕሊንም አለ ።

እነዚህ የዲሲፕሊን ዓይነቶች ባንድ የተወሰነ ወቅትና ኅብረተሰብ ውስጥ ባንድነት የሚከሰቱና እያንዳንዳቸው ተፈ ላጊነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ ። ባንድ ወቅት ባንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖ ረው ዲሲፕሊን በውስጡ ባሉት የኅብረተ ሰቡ አባላት የዕለት ተዕለት ድርጊትና ፍላ ጎት ፣ በኅብረተሰቡ አባላት ተዘውትረው የሚፈጸሙና የተለመዱ ማኅበራዊ ልማዶ ችና ደንቦች አጠቃላይ የዕድገት ደረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚወሰን (የሚታይ) ነው ። እነ ዚህ ማኅበራዊ ልማዶች ፣ ሕጎችና ደንቦች በኅብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸው እንደ መሆናቸው በእያንዳንዱ የኅብረተሰቡ አባል ውስጣዊ ስሜት ቀስ በቀስ ሠርፀው በመግ ባት በየዕለት ድርጊቱ ይገለጻሉ ፤ ይንፀባረ ቃሉ ። በየቀን ተግባር ካልተገለጹ ግን የነ ዚህ ወግና ልማዶች ፣ ደንቦች ፣ በእያንዳንዱ የኅብረተሰቡ (ድርጅቱ)አባላት መጣስ ፣ ከነ በረው አርጌ ልማድ የማፈንገጥን አዝማሚያ ያሳያል።ከዚህ ውጭ ሲሆን ማኅበራዊ ቀውስ ይከሰታል ። በኅወረተሰቡ ተቀባይነት የነበ ራቸው ልማዶች ፣ ወጎች ፣ ሕጎች ፣ ደንቦች ወዘተ..-በሙሉ ወይም በከፊል ተቀባይነታ ቸውን ያጣሉ ። ይህም ሁኔታ በወቅቱ በኅ ብረተሰቡ ውስጥ ባለው ሕግና ደንብ አስ ገዳጅነት ይገታል ፣ ይወሰናል ፤ ያለዚያም በወቅቱ የዲሲፕሊን ቀውስ ይፈጠራል ። በኅብረተሰቡ ውስጥ የተለያዩ ፣ በፊት ያልተለመዱ ባሕርያት ይከሰታሉ ። የነዚህ ልዩ ልዩ ባሕርያት መከሰትና መስፋፋት የነበረውን ማኅበራዊ ልማድ (አርጌ ሥነ ስርዓት ወይም ሥነ ምግባር) ከማቃወስ አልፎ ወደአዲስ ማኅበራዊ ለውጥ (ግን ኙነት) ያመራል ። በኋላቀር ማኅበራዊ ልማድ መሠረት ጥሩ ተብለው በኅብረተ ሰቡ ተቀባይነትና ሕጋዊነት ኖሯቸው ይከ በሩ የነበሩ ማኅበራዊ ሕጎች ፣ ወጎችና ልማ ዶች ፣ በአዲስ ሕግ ፣ ወግና ልማዶች ይተ ካሉ ። ቀስ በቀስም በማኅበራዊ ግንኙነቱ ላይ የይዘት ለውጥ ያስከትላሉ ።

እያንዳንዱ ኅብረተሰብ በራሱ ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ጥሩ ወይም መጥፎ ብሎ የሚመድባቸው የራሱ የሆኑ ወግና ልማ ዶች አሉት ። ባንድ የተወሰነ ወቅት ባለው ኅብረተሰብ አባላት ዘንድ ጥሩ ሆኖ የሚ ቆጠረው ወግና ልማድ በሌላ ወቅትና ኅብ ረተሰብ አባላት ዘንድ በከፊል ወይም በሙላ የሚወገዝና የሚጠላ ሊሆን ይችላል ። ይህ ሁኔታ በወቅቱ ባለው ኢኮኖሚያዊና ማኅ በራዊ ግንኙነት ላይ የሚመሠረት ፣ የዚሁ የግንኙነቱ ነፀብራቅ ነው ።

ለምሳሌ በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅ በር ጌታው ባሪያውን ቢሸጠው ፣ ቢገር ፈው ፣ ቢገድለው ፣ . . . አሚን ብሎ ካልተ ቀበለ ፣ ስለሰብአናው ፣ ስለበደሉ ሐሳብ ሲሠነዝር ከተሰማ ፣ የተደነገገለትን ወግና ልማድ ፣ ሕግ እንደጣሰ ይቆጠራል ።

በፊውዳሉ ሥርዓት ጌታው ሲሾም ሲሸ ለም ፣ ዓመት በዓል ሲሆን ፣ ስጦታ ያላበረ ከተና በአንድ ዓይነት መልክ ታማኝነቱን ያልገለጸ ጭሰኛ የነበረውን ወግና ልማድ እንዳፋለሰና ከኅብረተሰቡ ውጭ እንደሆነ ይቆጠራል ።

በካፒታሊስቱም ሥርዓት ስለግል ሀብት ማካበት መተቸት ፣ ስለሰዎች መብትና እኩ ልነት መቆምና መታገል የሚነወርበት አል ፎም የሕግ አንቀጽ ተጠቅሶ የሚቀጣበት ይሆናል ። በአንፃሩ የግል ሀብት ማካ በት ፣ መበዝበዝ ፣ የሠራተኛን ጉልበት

Digitized by Google

እንደሸቀጥ ገበያ ላይ አቅርቶ መግዛት፣ መሸጥና መለወጥ ፣ ከመጠን ያለፈ ሀብትና ድኅነት ጐን ለጐን መኖር እንደማኅበራዊ ልማድና ደንብ በመሆን ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ሰፍኖ የሚታይ ነው ።

በነዚህ የተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የሚኖረውም መመሪያ ፣ ሕግና ደንብ የገዥውን መደብ ጥቅም የሚያስጠብቀውን ወግና ልማድ የሚያስከብርና በዚህ ላይ የሚመሠረት ነው ። ሆኖም የኅብረተሰብ ነባራዊ ዕድገት ሕግ ወሳኝ ነውና ፣ በቅራኔዎች ዕድገት ምክንያት ወደሶሻሊስት ባህልና ዲሲፕሊን የመሸጋገሩ ሁኔታ የማይቀር ይሆናል ። ስለዚህም በኅብረተሰብ ዕድገት ሂደት ውስጥ በነፃነትና እኩልነት፣በመተሳሰብና በመረዳዳት ላይ የተመሠረተ ውና የድርጊት ፣ የሐሳብና የሂስ ነፃነት መገለጫ የሆነው ፣ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዲሲፕሊን ይመሠረታል ። ይህም በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራርና በነቃ ሕዝባዊ ተሳትፎ በሚካሄድ ትግል የሚገኝ ነው ።

የፓርቲ ዲሲፕሊን

ሌኒን በኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ የሚመሠረተውን ዲሲፕሊን ሲገልጽ «ጓዳዊ ዲሲፕሊን ፣ ፍጹም በሆነ የጋራ መከባበርና መተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ዲሲፕሊን ፣ በትግል ሂደት ውስጥ ከልብ የመነጨ የነፃነት ዲሲፕሊን ነው» [6] ይለዋል ።

ኮሚኒስታዊ ዲሲፕሊን «በኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ ለተጨቋኝ መደብ ነፃነት በሚደረገው ትግል ፣ ሥራንና ኃላፊነትን በፍላጎትና በፈቃደኝነት በመቀበል የሚገለጽ በጎ ሥነ ምግባር ነው ። «ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን ካፒታሊዝም በሠራተኛውና በሚሊታሪው ውስጥ ሊያሠፍነው ከሚፈልገው የሠራተኛ ነቀርሳ የሆነ ዲሲፕሊን ጋር ሲነፃፀር ፍጹም የተለየ ነው ። ኮሚኒስታዊ ዲሲፕሊን በሕዝባዊነቱ (ዲሞክራሲያዊነቱ) የላቀ ፣ በማንኛውም ታሪካዊ ፀረ ጭቆና እንቅስቃሴ ውስጥ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በንድፈ ሐሳብ ለማስታጠቅና በስፋትና በንቃት ለማሳተፍ የሚበጅ ፣ ጓዳዊ መንፈስ የሰፈነበትና በዚህ ላይ የተመሠረተ ነው ።» [7]

ሌኒን የፓርቲን ዲሲፕሊን ምንነት ሲገልጽ የሚከተለውን አስፍሯል ። «የፓርቲ ዲሲፕሊን የአባላት የተግባር አንድነት ነው ፤ የውይይትና የሂስ ነፃነት ነው ። ይህ ዓይነት ዲሲፕሊን ብቻ ነው ለአንድ ተራማጅ ግንባር ቀደም ፓርቲ የሚበጀው ። የሠራተኛው መደብ ትግል ጥንካሬ ድርጅት ነው ። ሰፊው ሕዝብ ካልተደራጀ የወዛደሩ ትግል ውጤት አይኖረውም ። በድርጅት አንድነቱን ከመሠረተ ግን ምንም የሚበግረው ኃይል አይኖርም ። መደራጀት ማለትም የድርጊት አንድነትን መፍጠር ማለት ነው ። በተግባራዊ ክንዋኔ ውስጥ አንድነትን ማስገኘት ማለት ነው ። ማንኛውም ድርጊት ጠቃሚነት የሚኖረው አንድን ዓላማ የሚያደክም ሳይሆን፣የሚያራምድ እስከሆነ ድረስ ነው ። በአብዮት ወቅት የአብዮታውያን ትግልና ተግባር የወዛደሩን፣ በአጠቃላይም የሠርቶ አደሩን የትግል አንድነት በማስገኘት አብዮቱን የሚያራምድ መሆን አለበት . . . » [8]

እነዚህ በተለያየ መልክ የተሰጡት የዲሲፕሊን መግለጫዎች በተለይም በአንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ውስጥ ፣ በአጠቃላይም በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የዲሲፕሊን ዓይነት የሚያስገነዝቡ ናቸው ። ፓርቲ ፣ በአጠቃላይም ሶሻሊስት ዲሲፕሊን ፣ የውጭ ኃይል አስገዳጅነት የሌለበት፣ከኅብረተሰቡ አባላት ውስጣዊ ስሜትና ፍላጎት ጋር የራስ አነሳሽነትና ፈቃደኝነት የሰፈነበት ፣ በመተሳሰብና በመረዳዳት ላይ የተመሠረተ ፣ ለልዩ ጥቅም፣ ለግል ክብርና ዝና ሳይሆን ፣ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ የተሟላ ነፃነት ፣ መብትና እኩልነት፣ ለኅብረተሰቡ የተስተካከለ ዕድገትና

Digitized by Google

ሰላም መስፈን በሚበጅ ማኅበራዊ ልማድ ላይ የተመሠረተ ነው ።

ይህ ዓይነቱ ዲስፕሊን እንዴት ይመሠረታል ?

ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን ሊመሠረትና ሊዳብር የሚችለው ፣ በንቃት ላይ የተመሠረተ አዲስ ማኅበራዊ ግንኙነት በመገንባት ሂደት ውስጥ ኮሚኒስታዊ ዜጋን ለመፍጠር በሚደረገው ረጅም የትግል ሂደት ውስጥ ነው ። በዚህ የትግል ሂደት ወቅት በተለይ በመሪ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ የሚመሠረተው ዲሲፕሊን ወሳኝነት አለው።የአባላት ንቃትና የዓላማ ጽኑነት ፣ ቆራጥነት፣ ከሰፊው ሕዝብ ጋር የሚኖረው የቀረበ ግንኙነትና የሕዝብ ተሳትፎ መገኘት ፣ የፓርቲው የተሟላ አሠራር ወዘተ...ለሚሰፍነው ዲሲፕሊን መሠረቶች ናቸው ። ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን ሊገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ሌኒን እንደሚከተለው ገልጾታል ።

1- በሠራተኛው ፓርቲ አባላት ዘንድ ባለው መደባዊ ንቃተ ሕሊና አባላት ፓርቲው ለቆመለት ዓላማ ባላቸው ጽኑነት ፣ ቆራጥነት ፣ ጥብቅነትና በእያንዳንዱ አባል መንፈስ ውስጥ በሚኖር የመሥዋዕትነት ፣ የአርበኝነት ወኔ ፤

2- ፓርቲው ከሰፊው ሕዝብ ጋር በሚመሠርተው የጠበቀና የቀረበ ግንኙነት፣ ሠራተኛውን ሕዝብ በአጠቃላይ ፣ወዝአደሩን በተለይ ፣ ለመቅረብና ለማቅረብ በሚኖረው ችሎታ ፤

3- ይህ ግንባር ቀደም ፓርቲ በሚቀይሰው ፖሊሲና በሚሰጠው ፖለቲካዊ አመራር ብቁነት ፣ በሚቀይሰው ፖለቲካዊ ስትራቴጂና ታክቲክ ትክክለኛነት ፣ ይህ ትክክለኛ መሥመር ለሕዝብ በሚኖረው ግልጽነት ስለአመራሩ ትክክለኛነት ሠራተኛው ሕዝብ በሚኖረው ትክክለኛ ግንዛቤ ፣... መሟላት የሚረጋገጥ ነው ።[9]

የእነዚህ ሁኔታዎች መሟላት ለማንኛውም ሠራተኛ ሕዝብ ነፃነት በቆመ አብዮታዊ ፓርቲ ውስጥ ጠንካራ ዲሲፕሊን ለማስፈን ያስችላል ። ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልተሟሉ በአንድ አብዮታዊ ፓርቲ አመራር ውስጥ ጠንካራ የፓርቲ ዲሲፕሊን ለማስገኘት የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ሁሉ ወሬና ቃላት ብቻ እንጂ ተግባራዊ አይሆንም ። በሌላ በኩልም የተጠቀሱት ሁኔታዎች በብዙ ጥረት እንጂ በቀላሉ የሚገኙም አይሆኑም።በሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስን ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በሚቀየስ ስትራቴጂና ታክቲክ አማካይነት የሚሟላ ነው ። በ1917—1920 (እ. ኤ.አ) በሩሲያ በነበረው የውስጥና የውጭ የጠላት ወረራ ወቅት የቦልሼቪክ ፓርቲ ጠንካራ ዲሲፕሊንና የጠበቀ ማዕከላዊነትን ሊያገኝና በተሟላ ሁኔታም ሊቆጣጠር የቻለው የሩሲያን ተጨባጭ ሁኔታ በመከተል በቀየሰው የአመራር ስልትና ሁኔታዎችን ካገኘው ልምድ ጋር ለማገናዘብ በመቻሉ ነበር ።

የጠንካራ ዲሲፕሊን መኖር ለአንድ አብዮታዊ ፓርቲ አመራር ስምረት እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው ። የፓርቲውን ፕሮግራም ፣ ደንብና መመሪያዎች ፣ በመፈጸምና በማስፈጸም ረገድ የኮሚኒስታዊ ዲሲፕሊን መኖር ወሳኝ ነው ። ለሠራተኛው መደብ ትግል ዓይነተኛ መኩሪያ ለሆነው ለድርጅታዊ ሥራ ዲሲፕሊን ያለውን አስፈላጊነት ሌኒን ደጋግሞ ገልጾታል ።

Digitized by Google

የኢትዮጵያ አብዮት ለድርጅት ጥያቄ የላቀ ትኩረት በመስጠት ከ10 ዓመት መራራ ትግል በኋላ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ሊመሠረት በቅቷል ። ታዲያ ይህ ከብዙ መስዋዕትነት በኋላ የተገኘው መሪ ድርጅታችን የአመራር ሚናውን የሚወጣው በተለይ በውስጡ የጠበቀ ዲሲፕሊን ሲገኝ መሆኑ በተለያየ ጊዜ ተደጋግሞ የተገለጸ ጉዳይ ነው ። ፓርቲው ግንባር ቀደም የመሪነት ሚናውን በትክክል ሊወጣ የሚችለው በንቃት ላይ የተመሠረተ ይህ ዓይነቱ ዲሲፕሊን በውስጡ ሲረጋገጥ ብቻ ነው ። የጠንካራ ዲሲፕሊንና አንድነት መረጋገጥ ለአንድ ግንባር ቀደም አብዮታዊ ፓርቲ የመሪነት ሚና መሳካት ወሳኝ ሁኔታዎች ናቸው ። በዚህ ዓይነቱ ጠንካራ ዲሲፕሊን ላይ የተመሠረተ ፓርቲ ሲሆን ነው ሰፊውን ሕዝብ ማደራጀትና ለተፈለገው የግንባታ እንቅስቃሴ በብቃት ማሰለፍ የሚቻለው ።

ለአንድ የማርክስሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራር ብቃት አንዱ ማረጋገጫ የሰፊውን ሕዝብ ድጋፍና ንቁ ተሳትፎ ማግኘት ነው፤የሶቭዬት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ በ1920 (እ-አ-አ) የውስጥና የውጭ ጠላትን ድል ነሥቶ በአሸናፊነት ሊወጣ የቻለበትን ዋንኛ ምክንያት ሌኒን ሲገልጽ ከፍተኛ ድርሻ የሰጠው ለፓርቲው ውስጣዊ ዲሲፕሊንና ለሕዝባዊ ድጋፍ ነበር ። ይህንኑ አስመልክቶ ሲናገርም « በፓርቲያችን ውስጥ ከብረት የጠነከረ ዲሲፕሊንና እውነተኛ የሠራተኛው መደብ ሙሉ ተሳትፎ ባይኖር ኖሮ ቦልሼቪኮች ለሁለት ዓመት ከመንፈቅ ቀርቶ ለሁለት ወር ተኩል እንኳን ሥልጣን ይዞ መቆየት ባልቻሉ ነበር [10] ብሏል ።

ጠንካራ የፓርቲ ዲሲፕሊን ከፓርቲው አባላት ርዕዮተ ዓለማዊ አንድነት መገኘት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው ። በፓርቲው ውስጥ የአባላት የአመለካከት አንድነት መገኘት በፓርቲው ውስጥ ለሚሠፍነው ዲሲፕሊን ዋና መሠረት መሆኑ ተደጋግሞ የተነገረ ታላቅ ቁምነገር ነው ። በአባላቱ መካከል የአስተሳሰብ መጣጣም ከሌለ የተግባር አንድነት ከቶ ሊኖር አይችልም ። የተግባር አንድነት ከሌለ ደግሞ የፓርቲው ፕሮግራም ፣ ደንብ ፣ መመሪያ ፣ . . . ተፈጻሚነት ሊያገኙ አይችሉም ። ስለዚህም የፓርቲው የመሪነት ሚና ውጤት አያገኝም ። የፓርቲ የጠበቀ ውስጣዊ ዲሲፕሊን በአባላቱ የአመለካከት አንድነት ላይ የሚመሠረት ነው ። በንቃትና በአመለካከት አንድነት ላይ የተመሠረተ ዲሲፕሊን ብቻ ነው እውነተኛና ከብረት የጠነከረ ዲሲፕሊን የሚሆነው የሚባለውም ለዚህ ነው ። የዚህ መሠረት ከሌለ ፓርቲው ያለጥርጥር የጠጋኞችና የሥርዓተ አልበኞች መፈንጫ ይሆናል ።

ይህን በመሰለው ጠንካራ አንድነት ላይ በተዋቀረ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ሕይወት ውስጥ ጥገናዊም ሆነ የከፋፋይነት አዝማሚያዎች መግቢያ ቀዳዳ አይኖራቸውም ። ምክንያቱም እያንዳንዱ አባል ለፓርቲው ውሳኔዎችና መመሪያዎች መከበር ተዋጊ ፣ ቆራጥ አርበኛሆና የሚገኝበት ነውና ። እነዚህንም ውሳኔዎችና መመሪያዎች በተግባር መተርጐምና የሠራተኛውን መደብ ትግል ከማኅበራዊ ዕድገት ሕግጋት ጋር እያገናዘበ፣ወቅታዊ የትግል ስልት መቀየስና መመሥረት እንደሚገባ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስ በጥብቅ ያስገነዝባል ።

አብዮታዊ እርምጃዎች ሁሉ ሳይንሳዊ ዕድገታቸውን ጠብቀውና ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር ተገናዝበው፣ ወቅታዊ ስትራቴጂና ታክቲክ በመጠቀም ፣ ደረጃ

Digitized by Google

በደረጃ መከናወን አለባቸው ። ስለዚህም ወቅታዊ ሁኔታዎች ቅድሚያ እየተሰጣቸው ሌሎችም በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ሁኔታዎች በጽሞና መታየትና መፈጸም እንዳለባቸው የኅብረተሰብ ዕድገት የለውጥ ሂደት ሕግ ያስገድዳል ። ከዚህ ውጭ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ያልተገናዘቡ እርምጃዎች ለከፋፋይነት በር የሚከፍቱና የወዝአደሩን ትግል የሚያዳክሙ ናቸው ። ስለዚህም የፓርቲው አመራር ሥምረት ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር በሚኖረው ግንዛቤ የሚወሰን ይሆናል ። ለዚህ ዓይነቱ ብቁ አመራር መገኘት ደግሞ በእያንዳንዱ የፓርቲ አባል ዲሲፕሊን መገኘት ላይ የሚመሠረት ነው ። በተናጠል የሚከሰተው የአባላት ዲሲፕሊን ሁኔታ ሲጠቃለል የፓርቲው ዲሲፕሊን ሁኔታ መግለጫ ነው ። በእኛም ተጨባጭ ሁኔታ ለኢሠፓ አመራር መቃናት ወይም መዛባት የእያንዳንዱ አባል ለኢሠፓ ፕሮግራምና ደንብ ተገዥ መሆን ወይም ያለመሆን ድምር ውጤት ነው ። በአንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ የሚነደፈውን ታክቲክና ስትራቴጂ በጥብቅ የማያከብሩና የማይከተሉ አባላት መገኘትና እየበረከቱም መሄድ ፣ በአጠቃላይ የዚህ ሁኔታ መከሰት በፓርቲው ውስጥ የዲሲፕሊን መበላሸትን ያሳያል ። ለፀረ አንድነት ድርጊት አመቺ ሆኖ መገኘትን ያስረዳል ።

ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ለአድኃሪያን ከበባና ፀረ—ሶሻሊስት ተግባር ቅስም መስበሪያ ዋና መሣሪያ የአብዮታውያን ጠንካራ አንድነት መሆኑ አያጠያይቅም ። በተለይም በመሪው ድርጅት ውስጥና በየደረጃው ባሉ የፓርቲው አካላትና አባላት መካከል የጠበቀ አንድነትና መተሣሠር መኖር የጋራ የሆነ አስተሳሰብና ጥራት ያለው የሥራ ውጤትን ያስገኛል ። በአንፃሩም ለከፋፋይነትና ለማፈንገጥ አዝማሚያ መግቢያ ቀዳዳ ያሳጣል ። በአባላቱ መካከል መግባባትን ፣ መተማመንንና የተግባር አንድነትን ያጠናክራል ።

የአንድነት አለመረጋገጥ በፓርቲው ውስጥ የሐሳብ መለያየትን ፣ መከፋፈልን ፣ ለጠላት አመቺ ሆኖ መገኘትን ያስከትላል ። ስለዚህም ነው ማንኛውም መደባዊ ንቃት ያለው ሠርቶ አደር በፓርቲ ውስጥ የሚከሰትን የከፋፋይነት አዝማሚያ በጽኑ ሊዋጋው እንደሚገባ ሌኒን አጥብቆና ደጋግሞ ያስገነዘበው ።

ቀልባሽ ኃይላት ለዓላማቸው መሳካት ዓይነተኛ መሣሪያ በፓርቲ ውስጥ የሚፈጠር የአባላት መከፋፈል መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ ። ስለዚህም የዚህን አዝማሚያ መፈጠር አጥብቀው ይፈልጉታል ፤ አድፍጠውም ይጠብቁታል ። የሚቻላቸውን ሁሉ ከማድረግም አይቆጠቡም ።

እ.ኤ.አ በኅዳር 1920 ሞስኮና ካርኮቭ በተባለ ከተማ ተደርገው በነበሩ የቦልሼቢክ ፓርቲ ስብሰባዎች ላይ « ወርከርስ ኦፖዚሽን ግሩፕ» (Workers Opposition Group) እና «ዲሞክራቲክ ሴንትራሊዝም » (Democratic Centralism) ብለው እራሳቸውን በሰየሙ ቡድኖች አማካይነት የሶቭየት ኮሚኒስት ፓርቲን ለመከፋፈልና ለመበታተን ተደርጎ የነበረው ሙከራ አንድ ልምድ ነው ።[11]

በተለይም «ወርከርስ ኦፖዚሽን ግሩፕ» እያለ ራሱን ይጠራ የነበረው ቡድን ሠራተኛውን ለማወናበድ በወቅቱ ከተጠቀመባቸው ዘዴዎች አንዱ ፣ የብሔራዊ ኢኮኖሚው አመራር ፣ ጉዳይ የመላ ሩሲያ የአምራቾች ማኅበር ጉባኤ ተግባር ነው[12] የሚል ነበር ።

በዚህ አቀራረብ ውስጥ «አምራቾች» (Producers) የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በው

ስጡ ወዝአደሩን ፣ ከፊል ወዝአደሩንና አነስተኛ ሸቀጣሸቀጥ አምራቹን የሚያጠቃልል መሆኑ ግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ ተሸፋፍኖ የቀረበ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ይህም ሠራተኛውን መደብ ከመሠረታዊው የመደብ ትግል መሥመር በማውጣት በመደቦች መካከል ያለውን መሠረታዊ ቅራኔ በመሸፈን እውነቱን ለማድበስበስ የሚጠቀሙበት አንዱ ስልት ነው ።[13]

በሠርቶ አደሩ ሕዝብና በሠራተኛው መደብ መካከል ያለውን ልዩነት ለማድበስበስና «አምራቾች» በሚለው ጽንሰ ሐሳብ ሸፍና በውስጡ የተለያየ መደባዊ አመለካከትና ልዩነት ያላቸው ፣ የተለያየ መደብን የሚወክሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በሚያጠቃልለው በ«አምራቾች ጠቅላላ ጉባኤ» በሚወከል አካል ይመራ ማለት የወዝአደሩን የበላይነት በቀጥታ አሳልፎ ለመሸጥ በሚሹ የቡርዧ ወኪሎች የሚጠነሰስ የቅልበሳ ሤራ ነው ። ቀልባሾች ቀዳዳ ባገኙ መጠን የማይሸርቡት ደባ አይኖርም ።ዛሬም በኢትዮጵያ አብዮት ላይ አድኅሮት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚፈጽሙት ድርጊት ከዚህ የተለየ አይደለም ። በተለይ በአየር ንብረት መዛባት የተነሣ በወቅቱ በአገራችን የደረሰውን ድርቅ ሁኔታ እንደአጋጣሚ በመጠቀም ከየአቅጣጫው የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ የፀረ አብዮት ሤራቸው አንዱ መገለጫ ነው ።

የውስጥም ሆነ የውጭ አድኃሪ ኃይላት ምንጊዜም እንደማይተኙልን መገንዘብ ያስፈልጋል ። የፓርቲውን ፖሊሲ አጣመው መተርጐምና ፣ ማቅረብ ፣ የሆነውን እንዳልሆነ ፣ ያልሆነውንም በተቃራኒው በማስተጋባት ለማደናገር ተቆርቋሪ መስለው መቅረብ የተለመደ ስልታቸው ነው ። በ1968 (እ.ኤ.አ) በቼኮዝሎቫኪያና በቅርቡም በፖላንድ ውስጥ የተከሰተው የመከፋፈልና የቅልበሳ ሙከራ በምሳሌነት የሚታይ ነው ።

ይህ ዓይነቱን የቅልበሳና የከፋፋይነት አዝማሚያ ነቅቶ መጠበቅና እንደአመጣጡም ተዋግቶ በእንጭጩ በመቅጨት የፓርቲያችንን ደኅንነት መጠበቅ የእያንዳንዱ አባልና በአጠቃላይም የመላው ሠርቶ አደር ዓቢይ ተግባርና ኃላፊነት ነው ። አንድነታችን የማይበገር የብረት ክንዳችን ነው ። ማንኛውንም የአብዮት ቀበኛ ቅስም ሰብሮ ይመልሳል ። ሌኒን ይህን የአንድነትን የኃይል መሠረትነት ሲያስገነዝብ እንዲህ ብሏል ።

እጅግ አስቸጋሪ በሆነው የትግል ጎዳና አንድነታችንን አጠንክረን እየተጓዝን ነው። በየአቅጣጫው በጠላት ተከበናል፣ ቢሆንም እነሱ የሚያደርሱብንን ጥቃት እየመከትን ወደፊት መግፋት አለብን፤ አንድነታችን በጋራ ውይይትና ውሳኔ ላይ የተመሠረተ ነውና ጠላቶቻችንን መጋፈጥና መደምሰስ እንጂ ወደ ኋላ አናፈገፍግም።[14]

ይህን በመሰለው አንድነት ላይ የተመሠረተ ዲሲፕሊን ሲገኝ ነው እውነተኛው «ከብረት የጠነከረ» የፓርቲ ዲሲፕሊን ሊኖር የሚችለው ።

ለማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ዲሲፕሊን መጠበቅና በጽኑ መመሥረት አንዱና ዓይነተኛው መሣሪያ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የአሠራር መርህ መስፈን ነው ። በፓርቲውና በሱም አማካይነት በየደረጃው የሚዋቀሩ አካላት ውስጥ የዚህ መርህ በትክክል መገኘት ወይም አለመገኘት ፣ በፓርቲው ውስጥ ለሚመሠረተው ዲሲፕሊን መጐልበት ወይም መዳከም ወሳኝነት አለው ። በማዕከላዊ ዕቅድ የሚነደፉ ፕሮግራሞች ግባቸውን ሊመቱ ፣ ትክክለኛ ተፈጻሚነት ሊያገኙ ከሚያስችለው ሁኔታ አንዱ የትክክለኛ አመራር መኖር ነው ። ይህም በዲሞክራሲያዊ ማዕከ

Digitized by Google

ላዊነት መርህ መገኘት የሚረጋገጥ ነው ። በኮሚኒስት ፓርቲው ውስጥ የሚኖር ውስጣዊ ኅብረት በዚህ መርህ ተግባራዊነት የሚረጋገጥ ነው ።

ይህ መርህ ተግባራዊ ከሚሆንባቸው እርምጃዎችም አንዱ የውስጠ ፓርቲ ቁጥጥር ዲሞክራሲያዊ መሆን ነው ። የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ቁጥጥር ኮሚሽን ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ያቀረበው ሪፖርት የውስጠ ፓርቲ ቁጥጥር ዲሞክራሲያዊነትን ሲያብራራ የሚከተለውን አሥፍሯል ፤

ፓርቲው አባላት ለጋራ አላማ በእኩል መብትና ግዴታ የሚመሠርቱት እንደመሆኑ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ነው ። ይህም ዲሞክራሲያዊነት በውስጡ በሚካሄድ ቁጥጥርም ውስጥ ይንጸባረቃል ።

በመሆኑም የፓርቲው የቁጥጥር ሥርዓት በአንድ በኩል ቁጥጥር አድራጊዎች በሌላ በኩል ቀጥጥር የሚደገባቸው በማለት በሁለት ክፍሉ የሚይዝ አይደለም ። የፓርቲውን አባላት በሚመለከት አባላት በፓርቲው የቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ በጋራና በግል በአንድ በኩል ቁጥጥር አድራጊዎች ሲሆኑ በሌላ በኩል ቁጥጥር የሚደረግባቸው ናቸው ። ይህም ለምሳሌ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲዎች ደንብ ውስጥ ሂስና ግለሂስን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይገለጻል ። አካላትን በሚመለከት የፓርቲው የቁጥጥር ሥርዓት የበላይ አካላት የበታች አካላትን የሚቆጣጠሩበት ብቻ ሳይሆን . . . የበታች አካላት የበላይ አካትን የሚቆጣጠሩበት አሠራርና መመሪያ አለ ። [15]

ሂስ እርስ በርስ ለመማማር ፣ ለበለጠ ትግል ጽኑ አቋም ለመመሥረትና በፓርቲ አባላት ዘንድ መተማመንን የበለጠ ለማስፈን ጠቃሚ መሣሪያ ነው ። በመሆኑም በፓርቲያችን ሰነዶች ውስጥ ተደጋግሞ እንደተገለጸው በማንኛውም ደረጃ በፓርቲ አካል መሪነት የተመደቡ ጓዶች ይህን አሠራር የሚያበረታቱ ፣ ሂስ በማድረግም ሆነ በመቀበል ፓርቲያችን በደንቡና በመመሪያዎቹ ላይ ያሠፈራቸውን ድንጋጌዎች ሕያውነት በተግባር ቀደምትነትና በአርአያነት የሚያስፈጽሙና የሚፈጽሙ መሆናቸው ወሳኝ ነው ። የሂስና ግለሂስ ብሎም በግልጽ በድክመቶች ላይ ተወያይቶ የመተራረም አግራጭ መተማማትና ከንቱ አሉባልታ ማናፈስ ነው ። ይህ ደግሞ ከምንመራበት ርዕዮተ ዓለም ጋር የማይጣጣምና ለቆምንለትም ዓላማ ተግባራዊነት ዕንቅፋት ነው ። ስለሆነም ኢሠፓ በጽኑ ይዋጋዋል ።

በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አባላት መካከል የመብትና የግዴታ መበላለጥ የለም ፤ ሊኖርም አይገባም ። ሁሉም የፓርቲው አባላት የፓርቲው ዲሲፕሊን ተገዢ መሆን አለባቸው ። እላይ የተጠቀሰው ሪፖርት ስለዚህ ነጥብ ሲገልጽ ፦

ለፓርቲው ጥብቅ ዲሲፕሊን መገዛት በሁሉም አባላት ላይ በፓርቲው ውስጥ የአገልገሉት ጊዜ ርዝማኔን ወይም የሥልጣን ደረጃን ሳይለይ በሁሉም ላይ በእኩልነት የሚፈጸም ነው ።

የፓርቲው ቁጥጥር ይህን መሠረታዊ መርህ የሚከተል ሲሆን ከዚህ ውጭ ከግዴታ መብት አንፃር አባላትን ከፋፍሎ ማስቀመጥ የተሳሳተ ነው ። እዚህ ላይ ማከል የሚያሻው በፓርቲው ውስጥ የሥልጣን ደረጃ የተሰጠው ጓድ ከአባልነት ግደታው በተጨማሪ ኃላፊነቱ ድርብ ግዴታ እንደሚጥልበት ነው ። [16]

ኢሠፓ አባላቱ ዲሲፕሊን ሲጥሱ በትክክለኛ መረጃ በመደገፍ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ። ነገር ግን በተቀዳሚ አባላት «የአባልነት ግዴታቸውን በብቃት ሊወጡ የሚችሉበት አመቺ ሁኔታ መፈጠሩን በማረጋገጥ ከስሕተትና ከዲሲፕሊን ጉድለት

እንዲጠበቁ ይጥራል።» ከዚህ ባሻገር መለስተኛ ጥፋት የሚፈጽሙና ሊታረሙ የሚችሉ አባላት እንደሁኔታው ቅጣት የሚወስንባቸው ሲሆን፣ የቅጣቱም ዓላማ ስሕተታቸውን በማረም በፓርቲው ውስጥ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ነው። በተጨማሪም ፀረ ፓርቲ ባሕርይ በሚያሳዩና ፓርቲው ላለመለት ዓላማ ተግባራዊነት ዕንቅፋት በሚሆኑ ላይ ጠንካራ እርምጃ በመውሰድ ኢሠፓ እራሱን የማያዳዳ መሆኑን ገልጿል።

የየማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊነት አንዱ መግለጫ በውስጣዊ አሠራሩ የጋራ አመራር መርህን ተግባራዊ ማድረጉ ነው። የጋራ አመራር መርህ መከበር የውስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊነት ዋስትና ነው።

ይህም ፓርቲው የጋራ ዓላማ ያላቸው ሰዎች በእኩል መብት የሚመሠረቱት ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ከመሆን ይመነጫል። የጋራ አመራር በፓርቲው ሕይወት ውስጥ የሚገለጸው በፓርቲው ጉባዔዎችና ስብሰባዎች እንዲሁም በፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች የሥራ ክንውን ነው። በእነዚህ ስብሰባዎች የፓርቲው አባላት በሙሉ በቀጥታ ወይም በመረጧቸው አባላት አማካይነት በፓርቲው ልዩ ልዩ ውሳኔዎች አሰጣጥ ውስጥ በመሳተፍ የጋራ አመራር ይሰጣሉ።[17]

በፓርቲ ውስጥ የጋራ አመራርን መጣስ ችል መባል የሌለበት አዝማሚያ ነው። ይህን ጉዳ አዝማሚያ ለማስወገድና መርሁን ተግባራዊ ለማድረግ፣ 1ኛ/የኢሠፓ ደንብ በሚያዘው መሠረት የፓርቲ አካላት ስብሰባዎችን በወቅቱ ማድረግ፣ 2ኛ/በስብሰባዎቹም ላይ ጓዶች ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ እንዲችሉ የአጀንዳዎችን ይዘት አስቀድሞ ማሳወቅና እያንዳንዱ አባል ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማበረታታት፤ 3ኛ/ በጋራ የተወሰኑ ጉዳዮች ተግባራዊ መሆን አለመሆን፣ በተግባር ሂደት ውስጥ የገጠሙ ዕንቅፋቶችን በጋራ መገምገም ፍጹም ሊታለፉ የማይገባቸው እርምጃዎች መሆናቸውን ለሁለተኛው መደበኛ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ የቀረበው የቁጥጥር ኮሚሽን ሪፖርት አስገንዝቧል።[18]

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አብዮታዊ ድርጅቶች ማለትም አንድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ውሳኔ ላይ እንዴት እንደሚደርስና ውሳኔውም በጋራ ላይ እንዴት እንደሚወጡ በአባላቱና በአባላት መካከል ያለውን ግንኙነት ብቃት የሚወስን የድርጅታዊ አሠራር መርህ ነው። የፓርቲ ዲሲፕሊን በአጠቃላይ ይዘቱ በፓርቲው የሚወጡ ሕጎችና ደንቦች፣ የሚቀየሱ ፖሊሲና መመሪያዎች፤ የሚተላለፉ ውሳኔዎች፤ ሥነ ሥርዓቶች፤ ወዘተ፤ - - - በአባላትና በአጠቃላይም በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዘንድ በትክክል መከበራቸውን የሚያስገነዝብ ነው። የፓርቲው ፕሮግራም፣ ደንብ፤ መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ አመራር መከበር፣ የአባላት የአመለካከትና የዓላማ አንድነት በአጠቃላይም የድርጅታዊ አንድነት መጠበቅ ለፓርቲ ጥብቅ ዲሲፕሊን መስፈን መሠረት ነው።

ሌኒናዊ ፓርቲ፣ የቆመለትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን ጠንካራ ዲስፕሊን ለማስፈን በተለያዩ መንገዶች ቁጥጥር የሚያደርግ ሲሆን በዚህ ተግባር አባል ያልሆኑ ሠርቶ አደሮችም እንዲሳተፉ ያደርጋል።

ፓርቲው ለሠራተኛው ሕዝብ የቆመና የጠበቀ ግንኙነት ያለው እንደመሆኑ የፓርቲውን ጥራትና ጥንካሬ በማረጋገጡ የቁጥጥር ተግባር ውስጥ አባል ያልሆኑ ሠርቶ አደሮች ጭምር ያሳትፋል። ፓርቲው ስለ አካላቱና ስለአባላቱ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ላለው አስተያየትና ለሚያደርገውም ጥቆማ ከፍተኛ ግምት በመስጠት የፓርቲው የቁጥጥር ሥርዓት የፓርቲውን ደንነት፣

Digitized by Google

ጥሬትና ጥንካሬ የሚያረጋግጡን ተገባር ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ተሳትፎ ጭምር ያጠናክራል ።[19]

የኢሠፓ መመሪያና ፖሊሲ በተግባር ሊተረጐም የሚችለው በሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች አማካኝነት ሰፊውን ሕዝብ በማሳተፍ ነው ። ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶችም በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የአሠራር መርህ የሚመሩና ይህን በጥብቅ የመከተላቸው ሁኔታ ከፓርቲው አመራር የሚመነጭና በፓርቲው አመራር አማካይነት መረጋገጥ ያለበት አስፈላጊ ጉዳይ ነው ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

በሶሻሊስት ግንባታ ሂደት ውስጥ በኢኮኖሚውና ማኅበራዊ ክንዋኔ ረገድ የሕዝብ ተሳትፎ እያደገ መሄድ የማስፈለጉን ያህል ይህ ዕድገት በጠንካራ ወዛደራዊ ዲሲፕሊን መመሥረት ይኖርበታል ። ለዚህ ጠንካራ ሕዝባዊ ዲሲፕሊን መገኘት ምንጩና መሠረቱ ደግሞ በመሪው ድርጅት ውስጥ የሚመሠረተው ጽኑ የፓርቲ ውስጣዊ ዲሲፕሊን ነው ።

በተለይ ፓርቲውን ከሕዝብ ፣ ሕዝቡን ከፓርቲው በማገናኘትና ለኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ለጠቅላላ ማኅበራዊ ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ የሚያበረክቱት የሠራተኛው ማኅበራትና ሌሎችም ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሊመሠረት የሚገባው ጠንካራ ወዛደራዊ ዲሲፕሊን ከመሪው ድርጅት ቀጥሎ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ።

በመንግሥታዊ ተቋሞችም ውስጥ የብዙኃን ድርጅቶች ተሳትፎ እያደገ መሄድ ፣ በዚያው መጠን የሶሻሊስት ዲሞክራሲን እየዳበረ መሄድ የሚያሳይ ነው ። ቢፓርቲውና በሕዝቡ መካከል የአንድነት መዳበርን፣ የሰፊው ከሕዝብ ፍላጐት በፓርቲው አመራር ትክክለኛ አቅጣጫ መያዙንና የሕዝቡ ፍላጐትና የፓርቲው አመራር መጣጣሙን የፓርቲው ፖሊሲና መንግሥታዊ ዕቅዶች በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ተግባራዊነት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ከሰፊው ሕዝብ ንቃተ ኅሊና መዳበር ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። የተነደፈውን ፕሮግራም፣ የተቀየሰውን ፖሊሲና ዕቅድ ተገንዝቦ በተግባር የመተርጐሙ ጉዳይ ግዴታን ሳይሆን ውዴታን ፣ ፍላጐትንና ፈቃደኛነትን አጥብቆ የሚጠይቅ ነው ። ይህ ደግሞ ከማወቅና ከመረዳት የሚመነጭ ነው ። ስለዚህም ማስተማር ፣ ማደራጀትና ማዘጋጀት የመሪ ድርጅቱ ተቀዳሚ ተግባር ሲሆን ፣ በቅድሚያ የመሪ ድርጅቱ ውስጣዊ አንድነትና ጠንካራ ዲሲፕሊን መኖር ለዚህ ሁሉ መሠረት ነው ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. የግሌ መዝገበ ቃላት ፣ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተ ዓለም መምሪያ የተዘጋጀ ረቂቅ ፣ ገጽ 422 ።
2. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 8, P. 288.
3. *Ibid.*, P. 289.
4. Lenin, Collected Works, Vol. 11, P. 320.
5. Great Soviet Encyclopaedia, Vol. 8, P. 288.
6. *Ibid.*' P. 288.
7. Marxist Glossary, P. 42.
8. Lenin, Collected Works, Vol. 11, P. 320,
9. Lenin Vol. 31, PP. 24-28.
10. Lenin, Collected Works, Vol. 31, P. 23.
11. *Ibid.*, Collected Works, Vol. 31, PP. 24-28.
12. Lenin, Collected Works, Vol. 32, P. 241
13. *Ibid.*, P. 246.
14. Lenin, Against Revisionism, P. 40
15. የውስጠ ፓርቲ ሕይወት ቁጥጥር ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበ የማዕከላዊ ቁጥጥር ኮሚሽንስ ሪፖርት መጋቢት 1977 ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ) ገጽ 14 ።
16. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 19 ።
17. ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 28 ።
18 ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 29—30 ።
19 ከላይ የተጠቀሰው ገጽ 14 ።

Digitized by Google

ከዝግጅት
መስከረም
ለአንባቢያን

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ሥራውን ከሚያካሂድባቸው መሣሪያዎች አንዱ የፓርቲው የንድፈሐሳብ መጽሔት ነው ። የዚህ ዓይነቱ መጽሔት እንቅስቃሴዎችን በጥልቀት ለመመርመር ፣ በፓርቲውም ውስጥ ሆነ በሕዝቡ መካከል ሳይንሳዊ አስተሳሰብን ለማሥረፅና ለአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ አስተዋጽኦ ለማድረግ ጠቃሚ መሣሪያ መሆኑ ይታወቃል ።

ከመስከረም 1973 ጀምሮ ባለፉት አምስት ዓመታት በየሦስት ወሩ የሚታተመው የፓርቲያችን የንድፈ ሐሳብ መጽሔት፣የ«መስከረም» የሥራ አቅጣጫና አስተዋጽኦም ከዚሁ አንፃር የሚታይ ነው ። በታኅሣሥ ወር 1973 በወጣው ሁለተኛ እትማችን እንደተጠቀሰው ፣

የ"መስከረም" አጠቃላይ ዓላማ የኢትዮጵያን አብዮት በማሌ ንድፈ ሐሳብ ማጠናከርና የማሌን ሳይንስ በኢትዮጵያና በዓለምአቀፍ ሁኔታዎች ትንታኔ ማዳበር ነው ። በዚህም ውስጥ ወቅታዊና አከራካሪ የርዕዮተዓለም ጉዳዮችን መመርመር የኢትዮጵያን አብዮት ባሕርይ ከልዩልዩ አቅጣጫዎች መተንተን ፣ የልዩ ልዩ አብዮቶችን ታሪክና የጊዜውን የአርነትና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል መገምገም ፣ ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነትን ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች መተንተንና የሶሻሊስት ጎራ የሚጠናከርበትን መንገድ መጠቆም ፣ ወዘተ . . . ከመጽሔቱ ተግባራት ውስጥ አንዳንዶቹ ናቸው ።

መጽሔቱ በሚያወጣቸው ልዩ ልዩ ጽሑፎች የሠራተኛውንና የሌሎችንም ሠርቶ አደሮች ጥቅም የሚያስከብሩና የሚያዳብሩ፣ እንዲሁም አድኃሪ ርዕዮተ ዓለምን የሚዋጉ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ለማሠራጨት ጥረት አድርጓል ። ከኃላፊነቱ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ አኳያም በሁለቱ ሥርዓቶች ፣ ማለትም በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል ስለሚካሄደው ፍልሚያ ፣ ስለዓለምአቀፍ ኮሚኒዝም ፣ ስለሠራተኛው መደብና

Digitized by Google

ለብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ፣ በአጠቃላይ
ለዓለም ሰላምና ለማኅበራዊ ዕድገት ስለሚ
ካሂዱት ትግሎች ተገቢ ትንተናና ማብራ
ሪያ ለመስጠት ሞክሯል ። በዚህ ረገድ በተ
ለይ እየተባባሰ የመጣውን የኢምፔሪያሊ
ዝምን ፀረ ሶሻሊዝምና ፀረ ሰላም ፕሮፓጋ
ንዳ ለማጋለጥ መጽሔቱ የበኩሉን አስተ
ዋጽኦ ለማድረግ ይታገላል ።

ዛሬ በምንገኝበት ዓለምአቀፍ ሁ ኔ ታ
ውስጥ በሚካሄደው ትግል አኳያ የተለያየ
ቅርጽ ቢኖራቸውም ተፃራሪ አቋሞች የሚ
ያራምዱ ሁለት የፕሮፓጋንዳ ግንባሮች
እንዳሉ ግልጽ ነው ። አንደኛው የኢምፔሪ
ያሊዝምን ዓላማ የሚያራምድ ፀረ ሶሻሊ
ዝም ፣ ፀረ ብሔራዊ አርነትና ፀረሰላም
አቋም ያለው ፣ ለብዝበዛና ለሕዝቦች ባር
ነት የቆመ ነው ። ሁለተኛው የሶሻሊስት
ሥርዓትንና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የዚህ
ሥርዓት አጠናካሪ ኃይሎችን ጥቅም የሚ
ወክል ነው ። ይህ ሁለተኛው ዓይነት ፕሮ
ፓጋንዳ በአጠቃላይ ለዓለም ሰላምና ለማ
ኅበራዊ ዕድገት ፣ ለሰው ልጆች ነፃነትና
መብት መከበር የሚታገል ነው ። የፓርቲ
ያችን የንድፈ ሐሳብ መጽሔትም አሰላለፉ
በዚህ የታሪክን ሂደት በሚያንፀባርቀው
ወገን ውስጥ የሚጠቃለል ነው ።

የ«መስከረም» ባሕርይ የሚገለጸው በጥ
ቅሉ ለሠራተኛው መደብ ወገናዊ በመሆ
ንና በዓለምአቀፋዊነት ብቻም አይደለም ።
ወቅታዊነትና ተጨባጭነት ያላቸው ጽሑ
ፎች ማውጣትም የመጽሔቱ ሌላው ባሕ
ርይ ነው ። በዚህ መሠረት የሕዝቡን የት
ግል ልምድና ፍላጎት ለማንፀባረቅና ሕዝ
ቡን ለበለጠ ታሪክ ሠሪነት ለማነሣሣት
በተቻለ መጠን ትኩረት ይሰጣል ። የሠርቶ
አደሩን ሕዝብ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ የሚ
ያዳብሩ ፣ ሕዝባችን በኢኮኖሚና በማኅበ
ራዊ ግንባታ ፣ በፖለቲካ ትግል የቀሰማቸ
ውን ልምዶች የሚያብራሩና ሌሎችም
ከዚሁ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጽሑፎች
ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ያወጣል።

በመጽሔቱ ተልዕኮ አፈጻጸም ው ስ ጥ
ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለምን የሚያን
ፀባርቁ አባባሎችን በጅምላ ማንፀባረቅ
ሳይሆን ተጨባጭ ብሔራዊ ፣ አካባቢያዊና
ዓለም አቀፋዊ ችግሮችን በትክክል ለመረ
ዳትና ለመፍታት ፣ በንድፈ ሐሳብም ሆነ
በተግባር የሚታዩ ድክመቶችን ለማስወ
ገድ የሚረዱ የመፍትሔ ሐሳቦችን ማቅ
ረብ እጅግ አስፈላጊ ነው ። ስለተገኙ ድሎች
ብቻ ማውሳት ፣ ችግርና ድክመቶችን ማድ
በስበስም የመጽሔቱን የትግል መሣሪያነት
እንደሚቀንሰው እሙን ነው ። መጽሔቱ
በፓርቲያችን ፕሮግራም መሠረት ስለሚ
ካሄደው የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ሕዝቡ
ተገንዝቦ በተግባር እንዲተረጉም ማስተ
ማር ፣ ለመመሪያዎች ተፈጻሚነት መታገ
ልና ማታገል ተግባሩ በመሆኑ የሚታተ
ሙት ጽሑፎች የሚያወሱት በተግባር ከሚ
ታየው ጋር መጣጣም እንዳለባቸው አያጠ
ያይቅም ። ይህ ካልሆነ በስተቀር መጽሔቱ
በሕዝቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ዝቅተኛ
ሊሆንና የቆመለትን ዓላማ የመወጣት ዓቅ
ሙም ደካማ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ የሚ
ያወጣቸው ጽሑፎች ሕዝቡን ለበለጠ
ትግል የሚጋብዙና የትግሉንም ስልትና
ዘዴ የሚጠቁሙ መሆን አለባቸው ።

«መስከረም» በዚህ ግንዛቤ ላይ በመመ
ሥረት ባለፉት አምስት ዓመታት ድርሻ
ውን ሲያበረክት ቆይቷል ፤ ለወደፊቱም
በዚሁ እምነት ላይ በመመርኮዝ አስተዋጽ
ኦውን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ጥረት
ይደረጋል ። የመጽሔታችን የመጀመሪያው
እትም ፣ ቅጽ 1 ፣ ቁጥር 1 ከአምስት ዓመ
ታት በፊት በመስከረም ወር 1973 የወ
ጣው በ17ሺህ ቅጂዎች ነበር ። የቅጂዎች
ተፈላጊነት በየጊዜው እየጨመረ መጥቶ
ዛሬ ይህ ቅጽ 6 ፣ ቁጥር 23 በ121,773
ቅጂዎች ታትሟል ። ከቁጥር 1 እስከ 23
ድረስ 21 መደበኛና 2 ልዩ እትሞች የወጡ
ሲሆን ፣ በጠቅላላው 2,101,546 ቅጂዎች
ታትመዋል ።

Digitized by Google

ከየአቅጣጫው በተደረጉ ተሳትፎዎች ለአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታው ትግል የሚረዱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ድርጅታዊ፣ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በዓለምአቀፍ ደረጃ በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል ስለሚካሄደው ትግል የሚያወሱ እንዲሁም በሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ አያሌ ጽሑፎች ወጥተዋል። ይህ ሲባል ግን መጽሔቱ የሚጠበቅበትን ሁሉ አሟልቷል፣ ችግር የለበትም ማለት አይደለም።

ለምሳሌ በመጽሔቱ የሚወጡ ጽሑፎች የተጨባጭነት ደረጃ በተለይ የአገራችንን ሁኔታና የሕዝቡን ፍላጎት በማንፀባረቅ፣ በየትግሉ መስክ የሚገጥሙ ችግሮችን ለማቃለል የሚረዱ መፍትሔዎችን በመጠቆም እንዲሁም ለአንባብያን የሚፈልጉትን ያህል ቅጂዎች በማቅረብ ረገድ አሁንም ብዙ መሥራት እንዳለብን እንገነዘባለን። በሌላ በኩልም ለመጽሔቱ ዝግጅት የሚያስፈልጉ በልዩ ልዩ ጉዳዮችና ልምዶች ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎችን በማግኘት ረገድም ተሳትፎ መጠናከር ይኖርበታል።

እንደሚታወቀው በኅብረተሰባችን ውስጥ የጽሑፍና የምርምር ባህል ገና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው። በዚህ ረገድ ባህሉ በዳበረ ኅብረተሰብም ውስጥ ቢሆን ውስብስብ የኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በትክክል የሚገልጽ፣ ሕዝቡን ሊያሳምን የሚችልና ተቀባይነት የሚኖረው ጽሑፍ ማቅረብ ቀላል አይደለም። ዕውቀትና ጠንክሮ መሥራትን ይጠይቃል። ከዚህ አንፃር ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ለመጽሔታችን የተቻላቸውን ያህል የጽሑፍ አስተዋጽኦ ያደረጉትን በዚህ አጋጣሚ እያመሰገንን ለወደፊቱም የእነሱና አርአያነታቸውን የሚከተሉ ሁሉ ተሳትፎአቸውን እንደሚያዳብሩ እንተማመናለን። ለንድፈ ሐሳብ መጽሔታችን ለ«መስከረም» እና በተመሳሳይ ሁኔታ ለማዕከላዊ ልሳናችን ለ«ሠርቶ አደር» የማያቋርጥ የጽሑፍ አስተዋጽኦ ማድረግ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጠቃሚ የትግል ልምድ ማካፈል ከመሆኑም ሌላ በርዕዮተ ዓለም ትግሉ ግንባር ዓቢይ ኃላፊነትን መወጣት ነውና የበለጠ ትኩረት ልንሰጥ ይገባል።

በፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ተጨባጭ ተሳትፎ ማድረግ ከፓርቲ አባላት ከሚጠበቁት ዐበይት ግዴታዎች አንዱ ነው። አሠራራችንም በግልና በጋራ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ሌሎች ለመጽሔቱ ጽሑፎችን ሊያቀርቡ የሚችሉ ጓዶችን፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችን፣ የምርምር ተቋሞችን፣ ትምህርት ቤቶችንና ሌሎችንም ሥራውን ሊያከናውኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ አካሎችን በማስተባበርና አመራር በመስጠት ሊካሄድ ይችላል።

በተጨማሪም እጥረትን ለማስወገድ በፓርቲው በኩል የመጽሔቱ የቅጂ ብዛት በየጊዜው እያደገ እንዲሄድ ታቅዷል። በዕቅዱም መሠረት ዛሬ የተደረሰበትን 121,773 የቅጂ ብዛት ደረጃ በደረጃ በማሳደግ በ1978 መጨረሻ የሚታተመው መጽሔት በ130,000 ቅጂዎች ይወጣል። ሌላው የመጽሔቱን እጥረት የማስወገጃ ዘዴ አንብቦ የማስነበብ ባህልን፣ መዋዋስን በሰፊው እንዲካሄድ ማድረግ፣ በተለያዩ አብያተ መጻሕፍት፣ በክበቦችና በመሳሰሉት ንባብ የሚካሄድባቸው ቦታዎች የመጽሔቱ ቅጂዎች በተቻለ መጠን እንዲዳረሱ ማድረግ ነው። በተጨማሪም የመጽሔቱ ቅጂዎች ለሕዝቡ እንዲዳረሱ ለማድረግ በየክፍለ ሀገሩ እስከ አሁን የሚላኩት ቅጂዎች ብዛት በምን ያህል መጨመር እንዳለበት ማጥናትና መጠኑንም ወደመጽሔቱ ማዕከላዊ የሥርጭት ክፍል በአስቸኳይ ማስተላለፍ ከፓርቲው አካላት የሚጠበቅ የሥራ ኃላፊነት ነው።

በአጠቃላይ የፓርቲያችን የንድፈ ሐሳብ መጽሔት፣ «መስከረም» የሚያካሂደውን ርዕዮተ ዓለማዊ የትግል አስተዋጽኦ ለማጠናከርና ከፍ ለማድረግ ከኢሠፓ አባላትና ከሌሎችም ተራማጆች የጽሑፍ አስተዋጽኦ እጅግ አስፈላጊ ነው።

Digitized by Google

የአርዕስት ማውጫ

ስምዖን ተክለ ሃይማኖት

ሀ

ሀሳብ (የ—) ሥርጭት ቁጥጥር ። 4 ፡ * 15 ፡ 13—20 ፣ '76

ለ

ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ። 4 ፡ 15 ፡ 59—71 ፣ '76

ሐ

ሕዝባዊ ቁጥጥርና አንዳንድ ችግሮቹ ። 5 ፡ 20 ፡ 34—53 ፣ '77

ሕዝብ (የ—) መገናኛ ዘዴዎች ተግባርና በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ወስጥ የተጫወቱት ሚና ። 3 ፣ 11 ፡ 15—32 ፣ '75

ሕግ በሽግግር ወቅት ። 4 ፡ 17 ፡ 62—73 ፣ '76

ሕጋዊ ምርምሮችና አመለካከቶች—ሕግና ዕድገት (ክፍል አንድ) 3 ፣ 10 ፡ 35—47 ፣ '75

መ

መልዕክት (የዝግጅት ገጽ) 1 ፡ 2 ፡ 3 ፣ '73

መሪ (የ—) ፓርቲ ፕሮግራምና ደንብ ሚና (የዝግጅት ገጽ) ። 5 ፡ 19 ፡ 3—4 ፣ '77

መሪ ፓርቲና መሪ ዕቅድ — ሁለት የአብዮታችን አበይት ድሉች (የአስተያየት ገጽ) ። 5 ፡ 19 ፡ 76—80 ፣ '77

መስከረም (የ—) መጽሔት ማወጫ ከቁጥር 19 እስከ 22 ። 5 ፡ 22 ፡ 76—88 ፣ '77

መስከረም (የ—) መጽሔት ማወጫ ከቁጥር 1 እ/ከ 18 ። 4 ፡ 18 ፡ 78—88 ፣ '76

መስከረም (የ—) መጽሔት ስድስተኛ ዕትም ሽፋን ዲዛይን ትርጉም ። 2 ፡ 6 ፡ 96 ፣ '74

ማሌ ርዕዮተ ዓለም — የአዝማች ፓርቲ የትግል መመሪያ (የዝግጅት ገጽ) ። 4 ፡ 18 ፡ 3—6 ፣ '76

ማሌ (የ—) ፓርቲ ንድፈ ሐሳባዊ መሠረት—ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር (የዝግጅት ገጽ) ። 3 ፡ 11 ፡ 3—14 ፣ '75

ማሌ (የ—) ፓርቲ — አማራጭ የማይገኝለት የትግል መሣሪያ (የዝግጅት ገጽ) ። 4 ፡ 15 ፡ 3—12 ፣ '76

* ቍጥሮቹ በቅደም ተከተላቸው መሠረት—ቅጽን ፣ ቍጥርን ፣ ገጽን ፣ ዓ. ምን የሚያመለክቱ ናቸው ።

Digitized by Google

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በጦርነትና በሰላም ጥያቄ ላይ ። 3 ፡ 13 ፡ 85—96 ፡ '75
ማርክሲዝምና የወቅታችን የሕዝቦች ትግል ። 3 ፡ 13 ፡ 13—40 ፡ '75
ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሥነ ዘዴ 6 ፡ 23 ፡ 47—58 ፡ '75
ማርክሳዊ(የ—) የፖለቲካ ኢኮኖሚ ግንዛቤ ። 1 ፡ 3 ፡ 27—36 ፡ '73
ማኅበራዊ ችግሮችና መፍትሔአቸው በአብዮት ሂደት ። 2 ፡ 12 ፡ 89—104 ፡ '75
ማዕከላዊ(የ—) አሜሪካና የካሪቢያን ሕዝቦች ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል (የዝግጅት ገጽ) ። 2 ፡ 9 ፡ 3—13 ፡ '74
ሜይ(የ—) ዴይ ታሪካዊ አመጣጥ ። 1 ፡ 4 ፡ 9—19 ፡ '73
ምሀርና አብዮታዊ ሚናው (ክፍል አንድ) ። 1 ፡ 5 ፡ 32—37 ፡ '73
ምሁርና አብዮታዊ ሚናው—የኢትዮጵያ ምሁር መደባዊ ጠባይና ሚናው (ክፍል ሁለት) ። 2 ፡ 6 ፡ 53—67 ፡ '74
ምዕራብ ሰሐራና የኢንተርናሽናል ሕግ (ክፍል አንድ) ። 2 ፡ 16 ፡ 9—20 ፡ '76
ምግባር(የ—) ግንዛቤ — በግሌ አመለካከት 5 ፡ 22 ፡ 50—61 ፡ '77
ምግብ(በ—) እራሳችንን እንድንችል (የዝግጅት ገጽ) ። 2 ፡ 22 ፡ 3—5 ፡ '77

ሠ

ሠራተኛው(የ—) መደብ ዕድገት በአፍሪካ ። 5 ፡ 21 ፡ 9—32 ፡ '77
ሥራ(የ—) ምርታማነት ። 1 ፡ 4 ፡ 36—44 ፡ '73
ርዕዮተዓለም(የ—) ትግል—አንዳንድ አጠቃላይ ገጽታዎች ። 1 ፡ 2 ፡ 5—10 ፡ '73
ርዕዮተዓለም(የ—) ይዘት ፡ ዕድገትና ሥርጭት (የግዝጅት ገጽ) ። 2 ፡ 6 ፡ 3—6 ፡ '74

ሰ

ሰላም ጥያቄና ዴታንት ። 2 ፡ 8 ፡ 13—23 ፡ '74
ሰላምና (ለ—) ለጦር መሣሪያ ቅነሳ የሚደረገው ትግል ። 5 ፡ 21 ፡ 47—64 ፡ '77
ሰብአዊ (ስለ—) መብቶች (የሐተታ ገጽ) ። 4 ፡ 16 ፡ 70—80 ፡ '76
ሳይንስም ወደ መስክ (የዝግጅት ገጽ) ። 6 ፡ 23 ፡ 3—4 ፡ '78
ሶሻሊስት(የ—) ትምህርት ሥርዓት ግንባታ ሂደት በኢትዮጵያ ። 3 ፡ 11 54—79 ፡ '75
ሶሻሊስት (በ—) አገሮች ላይ የሚካሄድ የኢምፔሪያሊዝም ደባ — አንዳንድ ገጽታዎች ። 3 ፡ 10 ፡ 90—96 ፡ '75
ሶሻሊስት(በ—) ኢኮኖሚ ግንባታ የመንግሥትና የኅብረት ሥራ ማኅበርራት ሚና ። 1 ፡ 5 ፡ 20—31 ፡ '73
ሶሻሊስት(የ—) የዕድገት ፈለግና ችግሮቹ ። 3 ፡ 14 ፡ 15—33 ፡ '75

Digitized by Google

ሶሻሊስታዊ አርበኝነት ። 1 ፥ 1 ፥ 41—49 ፥ ‘73

ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነትን የማስፋፋት ሂደት በኢትዮጵያ ። 3 ፥ 12 ፥ 15—30 ፤ ‘75

ሸ

ሽብር ፈጣሪነት—የኢምፔሪያሊዝም ዓይነተኛ መሣሪያ ። 4 ፥ 15 ፥ 72—88 ፤ ‘76

ሽግግር (በ—) ወቅት በኢኮኖሚና በፖለቲካ መካከል መኖር
ስለሚገባው ግንኙነት (የዝግጅት ገጽ) ። 3 ፥ 12 ፥ 3—14 ፤ ‘75

ሽግግር (በ—) ወቅት የሕግ ሚና ። 5 ፥ 21 ፥ 33—46 ፤ ‘77

ሽግግር (በ—) ወቅት የኢኮኖሚ አስተዳደርና አመራር — አንዳንድ
ነጥቦች ። 5 ፥ 19 ፥ 5—13 ፤ ‘77

ቀ

ቀይ (በ—) ካባ ሽፋን የሚከናወን ፀረ—ማርክሲስት ደባ—የመንዝሊ
ሬሺውና የበረከተአብ ሀብተ ሥላሴ ፀረ—ኢትዮጵያ
አብዮት ኅብረት ። 3 ፥ 10 ፥ 48—63 ፤ ‘75

ቅኝ(የ—) አገዛዝ የመጨረሻዎቹ ቅሪቶች ። 2 ፥ 9 ፥ 91—96 ፤ ‘74

ቁጥጥርና ሶሻሊዝም (የዝግጅት ገጽ) ። 2 ፥ 7 ፥ 3—5 ፤ ‘74

በ

ቢሮክራሲና ሕዝባዊ አስተዳደር ። 4 ፥ 17 ፥ 50—61 ፤ ‘76

ባህልና ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤው ። 2 ፥ 7 ፥ 64—84 ፤ ‘77

ባህልና ንድፈ ሀሳባዊ ግንዛቤው (ክፍል ሁለት) ። 2 ፥ 8 ፥ 52—63 ፤ ‘74

ባህልና አብዮታችን ። 3 ፥ 10 ፥ 80—89 ፤ ‘75

ባህልና (የ—) የቴክኒክ መሠረት ግንባታ በአብዮቱ ሂደት ። 3 ፥ 12 ፥ 50—73 ፤ ‘75

ብሔራዊ (የ—)ሀብት ቁጥጥር አንዳንድ መሠረታዊ ሐሳቦች ። 2 ፥ 9 ፥ 35—45 ፤ ‘74

ብሔራዊ (የ—) የኢኖኮሚ ግንዛቤና የኋላቀር አገሮች ዕውነታ ። 4 ፥ 15 ፥ 44—58 ፤ ‘76

ቦልሼቪክ (የ—)ፓርቲ ታሪካዊ ልምድና ዓለም—አቀፍ
አስተዋጽኦው ። 1 ፥ 2 ፥ 21—34 ፤ ‘73

ተ

ተስፋፊነትና ጠባብነት ፤ የሶማሊያ ገዥ መደብ ዓይነተኛ ገጽታ ። 2 ፥ 7 ፥ 50—63 ፤ ‘74

ኅ

ኅብረተሰብና (የ—) የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር ። 5 ፥ 22 ፥ 7—35 ፤ ‘77

ኅብረት (የ—) ሥራ ማኅበር ታሪካዊ አመጣጥ ። 4 ፥ 18 ፥ 23—44 ፤ ‘76

Digitized by Google

ኋላቀር (የ—) አገሮች የውጭ ዕዳ ሸክምና የኢምፔሪያሊዝም
የፋይናንስ ስትራቴጂ ። 3 ፡ 14 ፡ 81—96 ፤ ‘75

ኋላቀርነትና መፍትሔው በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ
ግንባታ ግንዛቤ ። 1 ፡ 1 ፡ 28—39 ፤ ‘73

ነ

ነጋድራስ(የ-) ገ/ ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካ ኢኮኖሚ
አስተሳሰብ ። 1 ፡ 3 ፡ 84—96 ፤ ‘73

ነጋድራስ (የ—) ገ/ ሕይወት ባይከዳኝ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ
(ክፍል ሁለት) ። 1 ፡ 5 ፡ 38—63 ፤ ‘73

ንግዱን (የ—) ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ ። 3 ፡ 12 ፡ 31—49 ፤ ‘75

አ

አሜሪካን (የ—) ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ
(ክፍል አንድ) ። 1 ፡ 3 ፡ 55—69 ፤ ‘73

አሜሪካን (የ—) ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ
(ክፍል ሁለት) ። 2 ፡ 6 ፡ 28—52 ፤ ‘74

አለ (የ—) አብዮታዊ ንድፈ ሐሳብ አብዮት አይኖርም ። 1 ፡ 1 ፡ 4—5 ፤ ‘73

አንድ የዓለም ቋንቋ እንዴት ይፈጠራል ? 5 ፡ 20 ፡ 70—80 ፤ ‘77

አርዕአደሩና (የ—)የተፈጥሮ ግንኙነት ችግር በኢትዮጵያ አንዳንድ 6 ፡ 23 ፡ 35—46 ፤ ‘78
ገጽታዎች

አዲሱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት —በጽንሰ ሀሳቡ ይዘት
ላይ አንዳንድ አመለካከቶች (የዝግጅት ገጽ) ። 3 ፡ 14 ፡ 3—14 ፤ ‘75

አዲሱ (በ—) የትግል ምዕራፍ የሠራተኛው መደብ ሚና
(የዝግጅት ገጽ) ። 1 ፡ 4 ፡ 3—8 ፤ ‘73

አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት (የዝግጅት ገጽ) ። 4 ፡ 17 ፡ 3—6 ፤ ‘76

አፓርታይድና የአርነት እንቅስቃሴ በደቡብ አፍሪካ ። 2 ፡ 9 ፡ 66—90 ፤ ‘74

ኢምፔሪያሊዝም (የ—) ሥነ ልቦና ጦርነት —ሥልትና መድረኮች
(የአስተያየት ገጽ) ። 5 ፡ 22 ፡ 62—75 ፤ ‘77

ኢምፔሪያሊዝም (የ—) ጠብ አጫሪነት ባሕሪ መባባስ
(የዝግጅት ገጽ) ። 2 ፡ 8 ፡ 3—11 ፤ ‘74

ኢምፔሪያሊዝም (የ—) ጦርኝነትና የሰላም ጥያቄ (የሐተታ ገጽ) ። 3 ፡ 11 ፡ 92—96 ፤ ‘75

ኢትዮጵያ (የ—) ሕዝብ ነፃነት ትግልና የኢጣልያን
ፋሽሽት ወረራ ። 1 ፡ 3 ፡ 37—54 ፤ ‘73

ኢትዮጵያ (የ—) ሠራተኛ መደብ ከትላንት እስከ ዛሬ ። 3 ፡ 13 ፡ 41—67 ፤ ‘75

ኢትዮጵያ (የ—) ሠራተኞች የትግል ታሪክ ። 1 ፡ 4 ፡ 21—35 ፤ ‘73

Digitized by Google

ኢትዮጵያ(በ—) አብዮት ሂደት የርዕዮተ ዓለም ሚና
(የዝግጅት ገጽ)። 3፡10፡3—10፤ ’75

ኢትዮጵያ (የ—) አብዮት ሂደትና የኢምፔሪያሊዝም ደባ። 2፡9፡14—34፤ ’74

ኢትዮጵያ(የ—) አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ። 1፡2፡11—20፤ ’73

ኢትዮጵያ (የ—) አብዮት ከዓለም አቀፍ አብዮታዊ ትግል አንፃር። 2፡7፡31—49፤ ’74

ኢትዮጵያ (የ—) አብዮት ከግብታዊነት ወደተቀናጀ አመራር
(የዝግጅት ገጽ) 1፡5፡3—5፤ ’73

ኢትዮጵያ(የ—) አብዮት የዓለም ሶሻሊስት አብዮት አካል ነው። 1፡2፡35—46፤ ’73

ኢትዮጵያ (የ—) አብዮት የዕድገት ደረጃ። 2፡7፡6—30፤ ’74

ኢትዮጵያ (የ—) አብዮትና የሴቶች ጥያቄ። 4፡17፡7—28፤ ’76

ኢትዮጵያ(የ—) አንድነት ታሪክ፤ በኤርትራ ክፍለ ሀገር የመገንጠል
እንቅስቃሴ አነሳስና የደረሰበት ደረጃ (ክፍል አንድ)። 1፡5፡64—75፤ ’73

ኢትዮጵያ(የ—) አንድነት ታሪክ፤ በኤርትራ ክፍለ ሀገር የመገንጠል
እንቅስቃሴ አነሳስና የደረሰበት ደረጃ (ክፍል ሁለት) 2፡6፡68—95፤ ’74

ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው
ታሪካዊ ትግል። ከ18ኛው ምዕተ ዓመት እስከ 1950ዎቹ
(ክፍል አንድ) 2፡9፡46—65፤ ’74

ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያደረገችው
ታሪካዊ ትግል (ክፍል ሁለት)። 3፡14፡58—80፤ ’75

ኢትዮጵያ(በ—) የድርጅት ጥያቄ እስከ ኢሠፓአኮ። 1፡1፡6—17፤ ’73

ኢትዮጵያና(የ—) የምዕራቡ ዓለም ግንኙነት—አንዳንድ ነጥቦች
(እስከ 1950ዎቹ)። 4፡15፡45—56፤ ’76

ኢንዱስትሪ(የ—) የዕድገት አቅጣጫ—ከምንከተለው የዕድገት
ፈለግ አንፃር። 5፡19፡14—34፤ ’77

ኢኮኖሚ(የ—) ማኔጅሜንት ጽንሰ ሐሳብ አስተዳደግና መሠረተ
ሐሳቦች። 6፡23፡5—34፤ ’78

ኢኮኖሚ(የ—) ዕቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም በአብዮቱ ሂደት። 3፡14፡34—57፤ ’75

ኢኮኖሚያዊ የውጭ ግንኙነት ከምንከተለው የዕድገት
ፈለግ አንፃር። 3፡12፡74—88፤ ’75

እምነት(የ—) በዓላት ብዛት—በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ኑሮና
የሥራ ዕቅድ ላይ ያስከተለው ችግር። 4፡17፡57—77፤ 76

አብሪተኞች(የ—) ባዶ ጩኸትና የራስን ዕድል በራስ
የመወሰን ዕውነታ። 2፡8፡24—36፤ ’74

Digitized by Google

ከ

ኪነጥበብና ርዕዮተ ዓለም በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ። 3 ፡ 11 ፡ 33—53 ፤ ‘75

ካርል ማርክስና የሠራተኛው መደብ ተልዕኮ (የዝግጅት ገጽ) ። 3 ፡ 13 ፡ 5—12 ፤ ‘75

ካድሬ(የ—) ስያሜና ተግባር በኢትዮጵያ አብዮት—ካለፍንበት ልምድ ። 5 ፡ 22 ፡ 36—49 ፤ ‘77

ካፒታሊዝም(የ—) ቀውስና የወዛደሩ መደብ የኑሮ ሁኔታ ። 3 ፡ 13 ፡ 68—84 ፤ ‘75

ኮምኒስት ማለት ምንም ማለት ነው ? ። 1 ፡ 3 ፡ 7—26 ፤ ‘73

ኮንትሮባንድ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ
ደኅንነት ላይ ያስከተለው ችግር ። 4 ፡ 16 ፡ 38—52 ፤ ‘76

ወ

ወቅቱ(የ—) የኢምፔሪያሊዝም ፀረ—ሰላም አቋምና
የዓለም ሰላም ኃይሎች ሚና ። 4 ፡ 16 ፡ 21—37 ፤ ‘76

ወቅቱ(የ—) የወዛደር ዓለም አቀፋዊ ትግል 1 ፡ 4 ፡ 45—64 ፤ ‘73
የወቅቱ ጥሪ (የዝግጅት ገጽ) 5 ፡ 20 ፡ 3—5 ፤ ‘77

ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ። 1 ፡ 1 ፡ 50—56 ፤ ‘73

ዐ

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) —የወል የእጅ አዙር
ቅኝ አገዛዝ መሣሪያ ። 3 ፡ 10 ፡ 11—34 ፤ ‘75

ዕውቀት(የ—) ንድፍፈ ሐሳብ ። 1 ፡ 2 ፡ 47—71 ፤ ‘73

ዘ

ዘላቂው(ለ—) ድል አስተማማኝ መሠረት (የዝግጅት ገጽ) ። 1 ፡ 3 ፡ 3—6 ፤ ‘73

ዘመኑ(የ—) ዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች ። 4 ፡ 17 ፡ 29—49 ፤ ‘76

ዘመናችን (የ—) የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ—
አንዳንድ ነጥቦች 4 ፡ 15 ፡ 21—43 ፤ ‘76

ዘመናችን(የ—) የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ—
አንዳንድ ነጥቦች (ክፍል ሁለት) 4 ፡ 16 ፡ 53—69 ፤ ‘76

ዜጎች(የ—) መሠረታዊ መብቶች ፤ ነፃነቶችና ግዴታዎች—ብሔራዊና
ዓለም አቀፋዊ ገጽታዎች (ክፍል አንድ) ። 4 ፡ 18 ፡ 7—22 ፤ ‘76

ዜጎች (የ—) መሠረታዊ መብቶች፣ነፃነቶችና ግዴታዎች—ብሔራዊና
ዓለም አቀፋዊ ገጽታዎች (ክፍል ሁለት) ። 5 ፡ 19 ፡ 35—60 ፤ ‘77

Digitized by Google

የ

የባስ(የ—)ትራንስፖርትን ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ የተደረገ ጥረት ። 5፡20፡54—69፤‘77

ደ

ዲሞክራሲያዊና የብሔረሰብ ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት ። 3፡11፡80—91፤‘75

ዳበሩ (ከ—) ካፒታሊስት አገሮች ወደኋላቀር አገሮች ካፒታል የሚዛመትባቸው መልኮች ። 2፡8፡37—51፤‘74

ዝግጅት (ከ—) ለአንባብያን 6፡23፡71—73፤‘78

ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶችና (ባንኮች) የኋላቀር አገሮች ሁኔታ ። 3፡10፡64—79፤‘75

ገ

ጊዜው (የ—) የፀረ—ኮሚኒዝም ዋንኛው ገፅታ ። 2፡6፡7—27፤‘74

ጊዜያችን(የ—) ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል— የላቲን አሜሪካ ሕዝብ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ። 1፡3፡70—83፤‘73

ጊዜያችን(የ—) ፀረ—ኢምፔሪያሊስትና ፀረ— አድኅሮት ትግል ። 1፡1፡18—27፤‘77

ጋብቻ(የ—) ጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ — አጠቃላይ ነጥቦች ። 4፡17፡74—80፤‘76

ግብርና(በ—) ክፍለ ኢኮኖሚ የሶሻሊዝም መሠረት ግንባታ 5፡20፡6—33፤‘77

ጠ

ጠረኝነት—የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ ዓይነተኛ ገጽታ (የዝግጅት ገጽ) ። 4፡16፡3—8፤‘76

ፈ

ፊውዳሊዝም(የ—) ገጽታዎች በኢትዮጵያ (ክፍል አንድ) ። 1፡5፡6—19፤‘73

ፊውዳሊዝም(የ—) ገጽታዎች በኢትዮጵያ (ክፍል ሁለት) ። 2፡7፡85—96፤‘74

ፐ

ፓርቲ(የ—) ዲሲፕሊን ። 6፡23፡59–70፤‘78

ፓርቲውን (የ—) የመሪነት ሚና ማሳደግ (የዝግጅት ገጽ) ። 5፡21፡3—7፤‘77

ፖለቲካ(የ—) ሥርዓትና ተግባሩ ። 5፡19፡61—75፤‘77

Digitized by Google

Hoover Institution Library
3 6105 070 925 578

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google